# ምዕራፍ ፺፡

## በዓል::

### በዓል የምናከብርበት ምክንያትና ዓላማ::

*ጥያቄ:-* *ከጸሎት ጋር የሚኼድ: ማለትም: እንደጸሎቱና ሥርዓቱ: የኢትዮጵያዊነት ሕይወታችንን የሚያሟላ: ሌላ ተጨማሪ ወይም ተመሳሳይ መመሪያ የሚኾን እውቀት ካለ: ብትገልጽልን?*

መልስ:- አዎን! ከጸሎቱና ሥርዓቱ ጋር: እንደነፍስና ሥጋ ተዋሕዶና ተያይዞ የሚኼድ: ሃይማኖታዊ ምግባር አለ፣ እርሱም: በዓልንና በዓላትን የሚመለከት ነው::

*ጥያቄ:-* *"ከጸሎት ጋር የተያያዘ ነው!" ስላልኸው: ስለበዓልና የበዓላት ነገርማ: ልናውቅ የሚገባን: እኛም የምንፈልገው በመኾኑ: ስለዚሁ ምሥጢርና ሥርዓት የሚያብራራውን ሐተታ ብታሰማን: እጅግ ደስ ይለናል:: ለመኾኑ: "በዓል" ምንድር ነው?*

መልስ:- "በዓል": ቀን ተወስኖለት: በመታሰቢያነት የሚፈጸም ሥርዓት ነው:: የመታሰቢያነቱ ዝርዝር: አያሌ ነገሮችን ያጠቃልላል፤ ከእነዚህ መካከል: የሚከተሉት ይገኛሉ:-

-ሰው: ከፈጣሪው: ወይም: ከእርሱ ከተሻለውና ከሚበልጠው የተፈጥሮ ወገኑ: ስለተደረገለትና ስለደረሰለት በጎ ነገር: ወይም ስለተደረገበትና ስለደረሰበት ክፉ ነገር: በግል እና/ወይም በጋራ: እያሰበና እያስታወሰ: ስለበጎው ነገር: ላድራጊው ፈጣሪ: ምስጋናን በማቅረብ፥ ፍጡር ሲኾን: ውለታውን: በደስታ ስሜቱ በመግለጽ: ያን በጎ ነገር ወይም ድርጊት: በበለጠ ለመቀጠል: ዝግጅቱንና ድርጅቱን ያጠናክርበታል፤

-በዚህ አንጻር: ስለደረሰበት ክፉ ነገር ወይም ድርጊት ደግሞ: ጥፋቱን በመገንዘብና ንስሓ በመግባት: እምነቱንና ምግባሩን አስተካክሎ: የወደፊት ህልውናውን በመልካሙ መንገድ ለመምራት ይዘጋጅበታል፤

-አንድን ልዩ ነገር: ወይም ልዩ ድርጊት: ወደኋላ መለስ ብሎ: ለመመርመርና ለመመዘን: በደስታ ወይም በኃዘን ለማስታወስ፥ ለማመስገን እና/ወይም ለማክበር ይጠቀምበታል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

"በዓል ማክበር" ማለት፡ እጅና እግርን አጣምሮ መቀመጥ፥ ወይም በልብስና በጌጣጌጥ መሽለም፥ ወይም፡ በማኅሌትና በሽብሸባ ማርገድ፡ ወይም፡ በሰልፍ መታየት፣ ወይም፡ መዝፈንና መጨፈር፡ ወይም መብላትና መጠጣት ብቻ አይደለም፡ መሠረቱ፡ ምንጩ፡ በተለይ፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን፡ በይበልጥ፡ በዓሉን መንሥዔ፡ ወይም፡ ምክንያት በማድረግ፡ ኹለንተናችንን፡ <u>በእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት አከናውነን፡ በመንፈስ መመሰጥ፥ በነፍስ፡ መንቃትና በሥጋ መዘጋጀት</u> ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ከጥንት ጀምረን፡ በዚህ መልክ፡ በዓል የምናደርገው፡ ለእየራሳችን፡ በግል፡ ወይም በጋራ፡ ለሌላ ሰብአዊ ፍጡር ሳይኾን፡ ለፈጣሪያችን፡ ለልዑል እግዚአብሔርና ከእርሱ ጋር ለተያያዘ ምክንያት ብቻ መኾኑ፡ ከሌሎቹ የዓለም አሕዛብ ኹሉ፡ የተለየ አድርጎን ኖርዋል። በዓሎቻችን ኹሉ፡ ሰው ከመኾኑ በፊት፡ በመልኩ ፈጥሮ ለሚመግበንና ለሚጠብቀን ፈጣሪያችን፡ ሰው ከኾነ በኋላም፡ ከመጥፋት አድኖ፡ ለዘለዓለም ሕይወትና ክብር ላበቃን፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እርሱንም ለወለደች ንግሥት እናታችን ድንግል ማርያም፥ ደግሞም፡ የእነርሱ ታማኞች አገልጋዮችና እውነተኞች ባለሚሎች ለኾኑት፡ ለመላእክት፡ ለጻድቃንና ለሰማዕታት የተሰጡ በመኾናቸው፡ ይህ እውነታ፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ በእርግጥ ጎልቶና ገዝፎ ይታያል።

ጻድቃንና ሰማዕታት የምንላቸውም፡ ከእግዚአብሔር፡ በመለኮት ደም ታትሞ በጸና ቃል ኪዳን ሳገኘናቸው፡ ሃይማኖታችንና መንግሥታችን፡ አገራችንና ወገናችን፡ የታመኑ አገልጋዮችና እውነተኞች አርበኞች በመኾን፡ ለእነዚህ የተቀደሱ ሀብቶቻችን ህልውናና ደኅንነት ሲሉ፡ እየራሳቸውን፡ መሥዋዕት አድርገው ያቀረቡት ' ኹሉ መኾናቸው ይታወቃል። ለእግዚአብሔር ባለሚልነት የሚያበቁት፡ እነዚህ ሙያዎች ናቸውና።

ስለዚህ፡ በዓሎቻችን ኹሉ፡ ለፈጣሪያችንና ለቅድስት እናቱ፡ ያለንን እውነተኛ ፍቅርና መታመን ለማረጋገጥ፡ ምስጋናችንንም፡ በታላቅ ደስታ ለማቅረብ፥ ለባለሚሎቻቸውም፡ ያለንን አክብሮትና አድናቆት፡ በይፋ ለማሳወቅ የሚከበሩ ናቸው፤ እነርሱም፡ በቅድሚያ፡ በጾም ውርደትና ሞት ተዘርቶና በመበስበስ አፈር ላይ በቅሎ፡ በመካከሉ፡ በጸሎት፡ በስግደትና በምጽዋት የገድል ድካም ያደገውን የሃይማኖት ተክላችንን፡ በመጨረሻ፡ ለጣፋጩ የንስሓ ፍሬ አብቅተን፡ ፍጹም ወደኾነው፡ ወደሥጋ ወደሙ የትንሣኤ ሕይወት በምናደርስበት፡ የተድላ ደስታ ሐሤታችን ይገለጻሉ።

፮ ባጭር ቃል፡ እነዚህ በዓላት፡ በእውነትና በመንፈስ ላይ በተመሠረተው አምልኮታችን፡ ሰው ለኾነው ፈጣሪያችንና ለቅድስት እናቱ፡ ያለንን መታመንና ፍቅር፥ ከምስጋና ጋር፥ ለባለሚሎቻቸውም፡ ከአክብሮት ጋር የምንገልጽባቸው መጽሔቶች ናቸው።

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል::
## ስለበዓላት ዝርዝር ሐተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ::

---

*ጥያቄ:- በመሠረቱ: "በዓል: ለምን አስፈለገ?" ከሚለው ጥያቄያችን ጋር:- ስለበዓላት አከባበር: ሃይማኖታዊ መነሻና ጥቅም: የምትሰጠን ተጨማሪ ማብራሪያ ካለ: ብትገልጽልን: ለምድራዊውና ለሥጋዊው ሕይወታችን: በይበልጥ ይረዳናል::*

*መልስ:-* ስለእያንዳንዱ በዓል የምሰጣችሁን ማብራሪያ ከማቅረቤ በፊት: እኛ ኢትዮጵያውያን: በዓሎቻችንን: በየጊዜያቱ የምናከብራቸው: ለምን እንደኾነ: አኹን በመነሻው ከሰጠኋችሁ መግለጫ ጋር: እዚህ ላይ: በተጨማሪ ላብራራላችሁ እወድዳለሁ:: ይኸውም: በዓላትን የምናከብራቸው: ለልማዱ ብለን ወይም ግዳጅ ስላለብን: ወይም ለመዝናናትና ሥጋዊ ዕረፍትን ለማግኘት: ወይም በመብልና መጠጥ: በዘፈንና ጨዋታ: ተድላ ደስታ ለማድረግ ስንል ብቻ አለመኾኑን ነው:: እያንዳንዱ በዓላችን: ከዚህ ኹሉ የላቀ ምክንያትና የተቀደሰ ዓላማ አለው::

ያን በዓል በምናከብርበት ጊዜ: ለምሳሌ: በዓሉ: የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ የኾነ እንደኾነ: በተመስጦ ኾነን: ለየራሳችን ልናቀርባቸውና መልስ ልንሰጥባቸው የሚገቡን መሠረታውያን ጥያቄዎች አሉ፤ እነርሱም:- "ለእኔ ሲል: ሰው የኾነው ፈጣሪዬ: በዚያች ዕለት: ያን ነገር ወይም ሥራ የፈጸመው ለምንድር ነው? እውነተኛ ምክንያቱ: በእርግጥ: ምንድር ነበር? ፈጣሪዬ: በዚያ ድርጊቱ: ለእኔ ሊነግረኝና ከእኔ ሊያገኝ የሚፈልገው ከቶ ምንድር ነው? ያ ፍላጎቱ: የእኔን መዳን ብቻ ሳይኾን: እኔ: ለሌላው ላደርገው የሚገባኝን እንድፈጽም አይደለምን? ታዲያ: ፈጣሪዬ: በዚያ ድርጊቱ: ከእኔ የሚፈልገውን ግዳጅ ወይም ድርሻ: በእኔ በኩል: ፈጽሜአለሁወይ?" የሚሉትን የመሰሉ ናቸው፤ ስለዚህ: ያ በዓል: እያንዳንዳችን: ጊዜያዊውንና ዘለዓለማዊውን: ማለትም: ሥጋዊውን ወይም ምድራዊውን፥ የነፍሱን ወይም የሰማዩን ሕይወታችንን በሚመለከት: በተመስጦ: የየግላችንን ምርምር የምናደርግበትና ቊርጥ ውሳኔን የምንሰጥበት ዕለት ነው ማለት ነው::

እንደዚሁ ኹሉ: ያ በዓል: የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም መታሰቢያ ከኾነ: "እመቤታችን: እኔ ምን እንድኾን፥ ምንስ እንዳደርግ ነው የምትፈልገው? ፍላጎቷን: በእርግጥ ፈጽሜአለሁወይ? እርሷ: ለእኔ ባላት አርአያነቷ: ከእርሷ ሕይወት፥ ሃይማኖትና ምግባር ምን ያህል ተምሬአለሁ? ምን ያህልስ ተጠቅሜአለሁ?" የሚሉትን የመሰሉ ጥያቄዎችን: ለየራሳችን አቅርበን: መልሱን መስጠት አለብን::

ለቅዱሳን መላእክት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት ክብርና መታሰቢያ እንዲኾኑ በተመደቡት በዓሎቻችን ዕለት ደግሞ: እየራሳችን: ለየራሳችን ልንጠይቃቸው፥ መልሳቸውንም: እየራሳችን: ለየራሳችን ልንሰጥባቸው የሚገቡን ጥያቄዎች: እነዚህንና ሌሎች ከዚህ አያይዤ የምዘረዝርላችሁን የመሰሉት ናቸው::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

በእነዚያ የበዓላት ቀኖቻችን፡ "ያ፡ ባለበዓሉ መልአክ፥ ወይም ጻድቅ፥ ወይም ሰማዕት፡ በዚያች ዕለት ምን አደረገ? ለምን፡ ያን ድርጊት ፈጸመ? እኔስ እንደእርሱ፡ ፍጡር አይደለሁምን? ያውም፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠርሁ? ታዲያ፡ እኔም፡ ከእርሱ ባገኘሁት አርአያነት፡ እንደእርሱ ኾኜ ወይም አድርጌ መገኘት ያልተቻለኝ ለምንድር ነው? በእራሴ ጉድለትና ጥፋት ነውን? ወይስ፡ በእኔ አለመፈለግና በቁርጥ አለመወሰን? ወይስ ከፈጣሪዬ የተከለከልሁት ነገር አለ? ከፈጣሪዬ የተከለከልሁት እንደሌለስ አውቃለሁ፡ ታዲያ፡ ከሌለ፡ ከፈጣሪዬ፡ በተፈጥሮና በባሕርይ ባገኘሁት የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣን ተጠቅሜ፡ ያ መልአክ፡ ወይም ያ ጻድቅ፡ ወይም ያ ሰማዕት ከደረሱበት ብቅዓት፡ ለምን፡ እኔም፡ ራሴን አላበቃም? በእኔ በኩል፡ እውነተኛው ፍላጎት ካለኝና ቁርጥ ውሳኔን ለመስጠት ከቻልሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ምክንያት፡ ያገኘሁት የንስሓ ጸጋ፡ የእግዚአብሔር የኾነውን መልካሙን ኹሉ ለማግኘትና ለማድረግ አብቅቶኝ የለምን?! ታዲያ፡ ምን እጠብቃለሁ?" የሚሉትን የመሰሉ ጥያቄዎቻችንን አቅርበን፡ መልስ ልንሰጥባቸው የሚገቡ መኾን አለባቸው ማለት ነው።

እዚህ ላይ፡ እስታውሰን፡ ልንከተለው የሚገባን፡ የማይታበል መለኮታዊ መመሪያና የማይታጠፍ የምሥራች መልእክት አለ፡ ይህም፡ *"እናንተን የሚቀበል፡ እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል፡ የላከኝን ይቀበላል። ነቢይን፡ በነቢይ ስም የሚቀበል፡ የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቅንም፡ በጻድቅ ስም የሚቀበል፡ የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። ማንም፡ ከእነዚህ፡ ከታናናሾቹ፡ ለአንዱ፡ ቀዝቃዛ የጽዋ ውኃ ብቻ፡ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፡ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋው አይጠፋበትም። ...እውነት፥ እውነት እላችኋለሁ! በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፥ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።"* የሚለው፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ነው።

መንፈሳዊ ሕይወታችንን እንዲህ ለማደስና ለማጠንከር፡ እንዲሁም፡ በየዕለቱ፡ ቀንና ሌሊትን፥ በየዓመቱም፡ ክረምትና በጋን የመሰሉትን፡ በሥነ ፍጥረት ሥርዓት እየተዘዋወሩ የሚመጡትን ጊዜያትና ወራት በመከተል፡ ለሥጋዊ ሕይወታችን እንደሚስማሙን አድርገን፡ በልዩ ኹኔታ የምናከብራቸው በዓላት ኹሉ፡ በዚህ መልክ ሊፈጸሙ የሚገባ መኾኑን፡ በትክክል እንድታስተውሉት ያስፈልጋል።

አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ ከእያንዳንዱ በዓላችን አስቀድሞ፡ ኹልጊዜ፡ የጾም ወራት፥ ሰሞን ወይም ዕለት እንዲኖር ያደረጉት፡ ያ በዓል፡ መንፈሳዊ ዓላማውን እንዳይለቅ ለመጠበቅና ለማስታወስ መኾኑን፡ የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓቱ ያስረዳናል፤ ከፋሲካ ትንሣኤ በፊት፡ የሁዳዴ ጾም፥ ከፍልሰታ ትንሣኤ በፊት፡ የሱባዔው ጾም፡ ከትስብእት በፊት፡ የነቢያት ጾም፥ ከጥምቀት በፊት፡ የገሃድ ጾም፥ ከሳምንቱ ሰንበታት በፊት እንኳ፡ የስቅለተ ዓርብ ጾም እየተባሉ፡ የምንጾማቸው አጽዋማት፡ ይህንኑ ያመለክቱናል።

# ምዕራፍ ፮፡ በዓል።
## ስለበዓላት ዝርዝር ሐተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ።

የበዓል አከባበራችን ሥርዓት፡ ሊፈጸም የሚገባው፡ በኪዳነ ልቡና ተመሥርቶና በኪዳነ አሪቱ አልፎ፡ ለአዲሱ ኪዳን በበቃው፡ በእውነትና በመንፈስ አምልኳችን መሠረት መኾኑን፡ ልታውቁት ይገባል። ስለዚሁ እውነታ፥ ስለበዓል አከባበራችን ዓላማና ተግባርም፡ በትክክል ለማወቅና ትርጉሙን፡ በግልጽ ለመገንዘብ የሚረዳን፡ የእውነተኛው መምህራችን መመሪያ ቃል አለ፡ ይኸውም፡ ጠብቀን እንድናከብረው፡ ከእግዚአብሔር ስለተሰጠንና የመጀመሪያው በዓላችን ስለኾነው፡ ስለሰንበት የተናገረው ነው።

`ይህም፡ ሰንበትን የሠራ፡ ራሱ፡ የሰንበት ጌታ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ሰንበት፡ ስለሰው ተፈጥሮአል እንጂ፡ ሰው፡ ስለሰንበት አልተፈጠረም፡"* የሚለውን ቃሉን በሚጠቅሰው፡ ደግሞም፡ በዘመኑ የነበረው የአይሁድ ትውልድ፡ በሰንበት፡ በሥውርም ኾነ በገሃድ፡ ያደርግ የነበረው፡ ክፉውን እንጂ በጎውን፡ ነፍስ ማጥፋትን እንጂ፡ ማዳንን እንዳልነበረ በሚያመለክተው፡ እንዲህ በሚለው፡ በወንጌላውያኑ ጽሑፍ ተብራርቶ እናገኘዋለን፡-

*"በዚያን ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ በሰንበት ቀን፡ በእርሻ መካከል አለፈ፥ ደቀ መዛሙርቱም፡ ስለተራቡ፡ እሸት ይቀጥፉ፥ ይበሉም ጀመር። ፈሪሳውያንም አይተው፡ 'እነሆ፡ ደቀ መዛሙርትህ፡ በሰንበት፡ ማድረግ ያልተፈቀደውን ያደርጋሉ፡' አሉት። እርሱ ግን፡ እንዲህ አላቸው፡- 'ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበሩት፡ በተራቡ ጊዜ፡ እርሱ ያደረገውን፥ ወደእግዚአብሔር ቤት እንደገባ፥ ካህናትም ብቻ እንጂ፡ እርሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት፡ ሊበሉት ያልተፈቀደውን፡ የመሥዋዕቱን ኅብስት እንደበላ አላነበባችሁምን? ካህናትም፡ በሰንበት፡ በመቅደስ፡ ሰንበትን እንዲያረክሱ፡ ኃጢአትም እንዳይኾንባቸው፡ ህብሕጉ አላነበባችሁምን? ነገር ግን እላችኋለሁ፦ ከሰንበት የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ። "ምሕረትን እወድዳለሁ፥ መሥዋዕትንም አይደለም፡" ያለው፡ ምን እንደኾነ፡ ብታውቁስ፡ ኃጢአት የሌለባቸውን፡ ባልኰነናችሁም ነበር። የሰው ልጅ፡ ለሰንበት እንኳ ጌታዋ ነውና።"*

ደግሞም፡ *"በሰንበት፡ በአንድ ምኵራብ ያስተምር ነበር፥ እነሆም፡ ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ፡ የድካም መንፈስ ያደረባት ሴት፡ በዚያ ነበረች፥ እርስዋም፡ ጐባጣ ነበረች፥ ቀንታም ልትቆም ከቶ አልተቻላትም። ኢየሱስም፡ ባያት ጊዜ፡ ጠራትና፡ 'አንቺ ሴት! ከድካምሽ ተፈትተሻል!' አላት፥ እጁንም ጫነባት፥ ያን ጊዜም፡ ቀጥ አለች፥ እግዚአብሔርንም አመሰገነች። የምኵራቡ አለቃ ግን፡ ኢየሱስ፡ በሰንበት ስለፈወሰ ተቆጥቶ፡ መለሰና፡ ሕዝቡን፡ 'ሊሠራባቸው የሚገባ፡ ስድስት ቀኖች አሉ፥ እንግዴህ፡ በእነርሱ መጥታችሁ ተፈወሱ እንጂ፡ በሰንበት አይደለም፥' አለ። ጌታም መልሶ፡ 'በሰንበት፡ በጎ ማድረግ ተፈቅዷልን፥ ወይስ ክፉ? ነፍስ ማዳንን፥ ወይስ መግደል? 'እናንተ ግብዞች! ከእናንተ እያንዳንዱ፡ በግ ያለው፥ ወይም አህያው፥ ወይም በሬው፡ በሰንበት፡ በጕድጓድ ቢወድቅበት፡ ይዞ የማያወጣው ሰው ማን ነው? በሰንበት፡ በሬውን፡ ወይስ አህያውን፡ ከግርግሙ ፈትቶ፡ ውኃ ሊያጠጣው ይወስደው የለምን? እንግዴህ፡ ሰው፡ ከበግ ይልቅ እንደምን አይበልጥም!?*

*"ይህችም፡ የአብርሃም ልጅ ኾና፡ ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ፡ ሰይጣን ያሠራት፡ በሰንበት ቀን፡ ከዚህ እሥራት ልትፈታ አይገባምን?' ስለዚህ፡ በሰንበት፡ መልካም መሥራት ተፈቅዷል::" አለው:: ይህንም ሲናገር ሣለ፡ የተቃወሙት ኹሉ አፈሩ፥ ከእርሱም በተደረገው ድንቅ ኹሉ፡ ሕዝቡ ኹሉ፡ ደስ አላቸው::"*

ስለዚህ፡ የበዓል አከባበራችን ባህልና ሥርዓት፡ እንዲህ፡ ታላቁ መምህራችን፡ በቃሉ በመናገር፡ በሥራም ገልጦ ሕሙማንን በመፈወስ፡ የሰጠንን መመሪያ ሊከተል ይገባል::

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን መለኮታዊ መመሪያ በማጽናት፡ በበዓላችን ቀን፡ ተገቢውን ጠበል ጠዲቅ ከተካፈልን በኋላ፡ በዕለቱ፡ ለራስም ኾነ ለሌላው ሰው፡ መልካም የኾነውን ምግባር፡ ማለትም፡ የተራቡትንና የተጠሙትን በማብላትና በማጠጣት፡ የታመሙትን በመጠየቅና የታሠሩትን በመጎብኘት፡ በልዩ ልዩ ችግር ላይ የሚገኙትንም፡ በመርዳት፡ ተገቢውን አገልግሎት ልንፈጽምበት ይገባል እንጂ፡ እንደአረማውያን፡ ዕለቱን፡ ከንቱውን እንጂ፡ ምንም በጎ ሥራ ሳይሠሩበት፡ በጥጋብና በስካር ብቻ፥ ወይም፡ እንደአረማውያን፡ በጭፈራና በዝሙት ጭምር ቢያሳልፉት፡ በዓሉ፡ "በትክክል ተከበረ!" ሊባል፡ ከቶ አይቻልም::

ስለበዓል አከባበራችን ምክንያትና ዓላማ፡ ይህን ያህል ከገለጽሁላችሁ፡ የቀረውን፡ በእያንዳንዱ በዓል ሓተታ ውስጥ ታገኙታላችሁ:: ከመስከረም ፩ ቀን ጀምረን፡ እስከነሓሴ ፴፥ ወይም፡ ጳጉሜ ፭ ወይም ፮ ቀን ድረስ፡ ዓመቱን ሙሉ በምናደርገው፡ የህልውናና የዕድሜ ጉዞ ላይ፡ እነዚህን፡ ዓቢያንና ንዑሳን በዓላት፡ ከአጽዋማቱና ከማብቂያቸው ጋር አያይዘን በምናዘክራቸውና በምናከብራቸው ጊዜ፡ ለሥጋዊ ኑሮአችንና ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጤናማ ዕድገትና ጽናት፡ የሚያበረክቱልን ጸጋ፡ የቱን ያህል ታላቅ መኾኑን፡ በየራሳችን ሰውነት ውስጥ ከሚሰማን በቀር፡ በቃላት መግለጡ ያስቸግራል:: የበዓላት አከባበር፡ አንዱ ሥጋዊ ጥቅምና ሃይማኖታዊ ረብን፡ ይህ ነው::

## ስለበዓላት ዝርዝር ሓተታ
## እና
## የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ::

**ጥያቄ:-** *በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኮ፡ በትክክል እናከብራቸው ዘንድ፡ እነዚህ በዓላት፡ ስንት እንደኾኑ፥ ማን ማንስ እንደሚባሉ፡ የሚውሉትስ፡ በየትኞቹ ቀኖች እንደኾነ፥ የሚከበሩትስ፡ በምን ምክንያት እንደኾነ፡ እስኪ፡ ዘርዝረህና ተንትነህ አስረዳን?*

**መልስ:-** ደስ ይለኛል:: በዕለትና በሳምንት፥ በወርና በዓመት የተመደበውን የበዓላት አከባበራችንን ሥርዓት፡ በቅደም ተከተሉ መሠረት አቀርብላችኋለሁ:: ሓተታውንም፡ እንዲህ በሚለው የመጽሓፍ ቃል ልጀምርላችሁ:-

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል::

## ስለበዓላት ዝርዝር ሐተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ::

*“እግዚአብሔርም አለ:- 'መዓልትና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ: ብርሃናት: በሰማይ ጠፈር ይኹኑ! ለምልክቶች፥ ለዘመናት፥ ለዕለታት፥ ለዓመታትም መሥፈሪያ ይኹኑ! በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ: በሰማይ ጠፈር: ብርሃናት ይኹኑ!' እንዲሁም ኾነ! እግዚአብሔርም: ኹለት ታላላቅ ብርሃናትን አደረገ፤ ትልቁ ብርሃን: ፀሓይ: በቀን፥ ትንሹም ብርሃን: ጨረቃ: በሌሊት እንዲሠለጥኑ፥ ከዋክብትንም ደግሞ: አደረገ:: እግዚአብሔርም: በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ: በመዓልትም፥ በሌሊትም እንዲሠለጥኑ፥ ብርሃንንና ጨለማን እንዲለዩ: በሰማይ ጠፈር አኖራቸው፤ እግዚአብሔርም: ያ: መልካም እንደኾነ አየ::”*[፲፬]

በዚህ: እምላካዊ ቃል መሠረት: በዘመናትና በዓመታት፥ በወራትና በሳምንታት፥ እንዲሁም: በመዓልትና በሌሊት የተከፈለችው: እያንዳንዷ ቀን፥ የቀኒቱ ሰዓትና ኬክሮስ ሳይቀሩ: ለሰው: መልካም ምድራዊ ሕይወት: የጊዜና የዕድሜ አቈጣጠር ያገለግሉ ዘንድ: ' ከእግዚአብሔር የተገኙ፥ ለእግዚአብሔር የተመደቡና በእግዚአብሔር የሚያልፉ ኾነው: በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሥርዓት ተደርጎላቸው: እየተሠራባቸው ይገኛሉ::

ከዚህ የተነሣ: በእግዚአብሔር ሳይኾን: በሰው የጊዜ አቈጣጠር: ዘመናቱ: ዐውደ ፀሐይ፥ ዐውደ ቀመር፥ ዐውደ ማኅተም፥ ዐውደ አበቅቴ፥ ዐውደ ዓመት፥ ዐውደ ወርኅ እየተባሉ: እስከዐውደ ዕለት በሚደርሱ: ሰባት አዕዋዳት: ማለትም: መሬት: በፀሓይ ዙርያ በምታደርገው ዑደት (ዙረት) ላይ በተመሠረቱ: የጊዜ መሥፈሪያዎች ተቀምረው ይሠራባቸዋል:: ከእነዚህ መሥፈሪያዎች መካከል: በተለይ: ዐውደ ዓመት፥ ዐውደ ወርኅ፥ ዐውደ ዕለት የተባሉትን: የመጨረሻዎቹን አዕዋዳት በመከተል: በየዕለቱና በየሳምንቱ፥ በየወሩና በየዓመቱ የምናከብራቸው በዓላት አሉን::

እነዚህም በዓላት: አራቱ ዓመታት: “አርባዕቱ እንስሳት” በተባሉት: በሰው፥ በአንበሳ፥ በላምና በንሥር በተመሰሉት: በአራቱ ወንጌላውያን: “ዘመነ ማቴዎስ”፥ “ዘመነ ማርቆስ”፥ “ዘመነ ሉቃስ” እና “ዘመነ ዮሐንስ” ተብለው በተሠየሙበት፥ እያንዳንዱም ዓመት: በወራት: ማለትም: ከመስከረም ፳፮ እስከታኅሣሥ ፳፭ ቀን ድረስ ያለው ጊዜ: “መፀው”፥ ወይም: “የጽጌ (የአበባ) ወራት”፥ ከታኅሣሥ ፳፮ እስከመጋቢት ፳፭ ቀን ድረስ ያለው ጊዜ: “ሓጋይ”፥ ወይም: “የበጋ ወራት”፥ ከመጋቢት ፳፮ እስከሰኔ ፳፭ ቀን ያለው ጊዜ: “ጸደይ”፥ ወይም: “የበልግ ወራት”፥ ከሰኔ ፳፮ እስከመስከረም ፳፭ ቀን ያለው ጊዜ: “ክረምት”፥ ወይም: “የዝናም ወራት” ተብሎ በተመደበበት ሥርዓት ይከበራሉ::

ኢትዮጵያውያን: በዓሎቻቸውን: በዚህ መልክ በተደራጀው የጊዜ መደባቸው በማክበር: የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው አገራቸው: ሥጋዊና መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ሲያካኺዱ ኖረዋል፤ አኹንም: እያካኼዱ ናቸው፤ ወደፊትም: በዚሁ ሥርዓት ማካኼዳቸውን ይቀጥላሉ::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ከጥንት ሲያያዝ የመጣውን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ውርስና ያን ተከትሎ፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚል ርእስ፡ በ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. በታተመው መጽሐፍ፡ በተለይም፡ በገጽ ፩፻፴፰-፩፻፵፫ የተሰጠውን ሰፊ ሐተታ መሠረት በማድረግ፡ በየዕለቱ፡ በየሳምንቱ፡ በየወሩና በየዓመቱ የሚያከብሩዋቸው፡ እነዚህ በዓላት፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ ተዘርዝረው ቀርበዋል።

### የዕለቱ በዓላት።

የዕለቱ በዓላት፡ ዘወትር ጧት፡ ጨለማው አልፎ፡ የፀሓይ ብርሃን ሲፈነጥቅ፡ በሞት ምሳሌ፡ በእንቅልፍ ተውጠን፡ ከወደቅንበት መኝታችን ስንነሣ፡ ከየራሳችን ጀምሮ፡ በዚያች በእያንዳንዷ ዕለት፡ የተገኙትን የፍጥረታት ልደት አስታውሰን፡ እግዚአብሔር፡ እኛን፡ ሰዎችን፡ እየራሳችንን፡ በመልኩ ፈጥሮ፡ በመልካሚ የገነት ሕይወት ከማኖሩ ጋር፡ ሌሎቹን ፍጥረታት፡ ለእኛ ተድላና ደስታ፡ ጥቅምና አገልግሎት ይውሉ ዘንድ አስበና ፈጥሮ ስለሰጠን፡ በበዓል መንፈስ ኾነን፡ ዘወትር፡ ለእርሱ ምስጋናችንን፡ በደስታ የምናቀርብባቸው ሰባቱ ቀኖች ናቸው።

### የሳምንቱ በዓላት።

የሳምንቱ በዓላት፡ እግዚአብሔር ወልድ፡-

ሀ. በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ኾኖ፡ ስለእኛ፡ ከዲያብሎስ፡ በሥጋ፡ በነፍስና በመንፈስ፡ በደረሰበት ልዩ ልዩ ፈተናና መከራ፡ የሓሰት ምክርና ውሳኔም ላይ፡ በጾም፡ በጸሎትና በምጽዋት ምግባሩ፡ የዘለዓለም ድልን ለእኛ ያቀዳጀባት፡ *የረቡዕ* ዕለት፡

በ. ስለእኛ ተገርፎና የእሾህ አክሊል ደፍቶ፡ ዕርቃኑን ተሰቅሎና በጦር ተወግቶ፡ ባፈሰሰው ደሙ፡ በኃጢአት የከፋት ቀምበር ላይ፡ የዘለዓለም ነፃነትን፡ ለእኛ ያጎናጸፈባት፡ *የዓርብ* ዕለት፤

ገ. ጥንት፡ ለእኛ መልካም ህልውና ሲል፡ የፍጥረት ሥራዊቱን፡ በስድስቱ የእርሱ ቀኖች አከናውኖ ጨርሶ፡ ያረፈባትንና እኛም፡ የሥጋ ዕረፍትን እናደርግባት ዘንድ ያዘዘን፤ እንደዚችው ትእዛዙም፡ በዕለተ ዓርብ፡ በመስቀል ላይ ነፍሱን፡ በፈቃዱ፡ ለሞት አሳልፎ ከሰጠ በኋላ፡ ራሱም፡ በሥጋው፡ በመቃብር ያረፈባት የቀዳሚት ሰንበት ዕለትና

ደ. በመጨረሻ፡ ስለእኛ፡ ነፍሱን፡ ከሥጋው የለየባትን መራራ የመስቀል ጽዋ ተቀብሎ፡ ከተቀበረ በኋላ፡ ከሙታን ተለይቶ በመነሣቱ፡ በሞት ፍዳና በሙስና መቃብር ላይ፡ የትንሣኤ ድልንና የዘለዓለም ሕይወትን፡ ለእኛ ያስገኘባት፥ "ቀዳሚት" የተባለችውንም፡ አንዲቷን ሰንበት፡ ዘለዓለማዊት ያደረገባት *የእሑድ* ዕለት ናቸው።

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል።
## ስለበዓላት ዝርዝር ሐተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ።
### የዕለቱ በዓላት፡ የሳምንቱ በዓላት።

---

### የወሩ በዓላት።

የየወሩ በዓላት፡ እንደኢትዮጵያ ባህል፡ ትርጉም ባለው፡ በቂ ምክንያት፡ ለእያንዳንዳቸው፡ የተለየ ስያሜ ተሰጥቷቸዋል። በዚህ መሠረት፡-

የየወሩ ፩ኛ ቀን (መባቻ፡ ወይም፡ መግቢያ)፡ "ልደታት" በሚል ስያሜ ታውቆ፡ በአክብሮት ይታሰባል፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ በመጀመሪያው የፍጥረት ዘመን፡ አዳም፡ ቀጥላ፡ ሔዋን፡ በመጨረሻው የፍጥረት ዘመን፡ በቅድሚያ፡ የአምላክ እናት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ኋላም፡ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚሁ ቀን ስለተወለዱ፡ ዕለቱ፡ "ዕለተ ልደታት" ሊባል ሲገባ፡ በልማድ፡ "ልደታት" ተብሏል።

የወሩ ፪ኛ ቀን፡ "መጥምቁ ዮሐንስ" ይባላል፡ የብሉዩና የአዲሱ ኪዳናት ድልድይ፡ የነቢያት መጨረሻና የሰማዕታት መጀመሪያ የኾነው መጥምቁ ዮሐንስ፡ በመስከረም ፪ ቀን የሚውለው ዕረፍቱ ስለሚታሰብበት ነው።

የወሩ ፫ኛ ቀን፡ "በኣታ" በሚል ስያሜ ይታወቃል። ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የስእለት ልጅ እንደመኾኗ፡ ወላጆቿ፡ በሕፃንነቷ፡ ለእግዚአብሔር ሰጥተዋት፡ በታኅሣሥ ፫ ቀን፡ ወደቤተ መቅደስ ስለገባችበት፡ "በኣታ ለማርያም" ተብሎ ይታሰባል፡ "በኣታ ለማርያም" የሚለውን ሐረግ ለማሳጠር፡ "በኣታ" ተባለ። በግእዝ፡ "ቦአ"፡ "ገባ"፡ "በአት"፡ "ገብተው የሚኖሩበት" ማለት ነው፡ "ቤት" ከዚህ መገኘቱን፡ ያስተውሏል።

የወሩ ፬ኛ ቀን፡ "ዮሐንስ፡ ወልደ ነጐድጓድ" ተብሎ፡ የወንጌላዊው ዮሐንስ ዕረፍት፡ በጥር ፬ ቀን ይታሰብበታል።

የወሩ ፭ኛ ቀን፡ "ገብረ መንፈስ ቅዱስ (አቦ)" በሚል ስያሜ፡ የጻድቁ አባ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዕረፍት ይዘከርበታል።

የወሩ ፮ኛ ቀን፡ "ቍስቋም" ይባላል፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ሕፃን ልጇን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዛ፡ ከጻድቃኑ ቅዱስ ዮሴፍና ቅድስት ሰሎሜ ጋር፡ በስደት ይቆዩባት ዘንድ፡ በኅዳር ፮ ቀን፡ ለገቡባት፡ የኢትዮጵያውያን ርስትና ገዳም ለኾነችው፡ ለቍስቋም፡ የተሰጠ መታሰቢያ ነው።

የወሩ ፯ኛ ቀን፡ "ሥላሴ"፡ ወይም፡ "ቅድስት ሥላሴ" ይባላል፡ የእግዚአብሔር ሦስትነትና የሥጋዌ (አምላክ፡ ሰው የመኾኑ) ምሥጢር፡ ታኅሣሥ ፯ ቀን በኾነው፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትስብእት ከተፈጸመ በኋላ፡ በይፋ ከታወቀበት፡ ከጥምቀቱ በፊት፡ በዘመነ አስተርእዮ፡ በጥር ፯ ቀን ይከበርበታል።

የወሩ ፰ኛ ቀን፡ "ግዝረተ ኢየሱስ"፡ ይባላል፡ ሕፃን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በተወለደ፡ በ፰ኛው ዕለት፡ በመስከረም ፰ ቀን፡ ግዝረቱን ስለፈጸመባት ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

የወሩ ፱ኛ ቀን፡ "አጼ ዳዊት" ይባላል፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ግማደ መስቀል፡ በአጼ ዳዊት ዘመን፡ ከኢየሩሳሌም ወደኢትዮጵያ መጥቶ፡ በመስከረም ፱ ቀን፡ መሬቷን የባረከበት፡ ኋላም፡ እርሱ ራሱ፡ አጼው፡ በጥቅምት ፱ ቀን ያረፈበት በመኾኑ፡ ይዘከሩበታል፡፡

የወሩ ፲ኛ ቀን፡ "መስቀለ ኢየሱስ"፡ ወይም፡ "አጼ መስቀል" ይባላል፡ ሕፃኑ ኢየሱስ፡ በ፵ ቀኑ፡ በጥቅምት ፲ ቀን፡ ወደቤተ መቅደስ ሲገባ፡ ወደፊት ስለሚጠብቀው የመስቀል መከራና ከዚሁ ልጇ የተነሣ፡ በእናቱ ድንግል ማርያም ላይ ስለሚደርስባት ሥቃይ፡ ሽማግሌው ነቢይ ስምዖን፡ ትንቢት የተናገረበት፡ ደግሞም፡ ንግሥት ዕሌኒ፡ በመጋቢት ፲ ቀን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል አስቆፍራ ያገኘችበትና ግማደ መስቀሉ፡ ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ፡ በመስከረም ፲ ቀን፡ በኢትዮጵያ ምድር እንደደረሰ፡ አጼ ዳዊት፡ ቤተ ክህነቱን፡ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ሕዝቡን ይዞ፡ በታላቅ ሥርዓት የተቀበለበት ዕለታት ይታሰቡበታል፡፡

የወሩ ፲፩ኛ ቀን፡ "ሐና ማርያም" ይባላል፡ በኅዳር ፲፩ ቀን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም እናት፡ ቅድስት ሐና ያረፈችበት ዕለት ይዘከርበታል፡፡

የወሩ ፲፪ኛ ቀን፡ "ሚካኤል" ተብሎ፡ የሊቀ መላእክት የቅዱስ ሚካኤል የተራዳኢነቱ መታሰቢያ ዕለት ይታሰብበታል፡፡

የወሩ ፲፫ኛ ቀን፡ "ደብረ ታቦር" በሚል ስያሜ ይታወቃል፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በነሐሴ ፲፫ ቀን፡ በታቦር ተራራ ላይ፡ ግርማ መለኮቱን፡ ለተመረጡት ባለሚሎቹ፡ በሰማያዊው ኃይል የገለጸበት ዕለት የሚዘከርበት ስለኾነ ነው፡፡

የወሩ ፲፬ኛ ቀን፡ "አቡነ አረጋዊ"፡ ወይም፡ "ገብረ ክርስቶስ" ተብሎ፡ ከመካከለኛው ምሥራቅ ወደኢትዮጵያ ከመጡት፡ ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ የኾኑትና በደብረ ዳሞ፡ ታላቁን ገዳም የመሠረቱት፡ የአቡነ አረጋዊ (አባ ዘሚካኤል ዘደብረ ዳሞ) መታሰቢያ ይዘከርበታል፡፡

የወሩ ፲፭ኛ ቀን፡ "ቂርቆስ" ተብሎ፡ ገድላቸውን በሰማዕትነት የፈጸሙት፡ የሦስት ዓመቱ ሕፃን፡ ቅዱስ ቂርቆስና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ ይታሰቡበታል፡፡

የወሩ ፲፮ኛ ቀን፡ "ኪዳነ ምሕረት" በሚል ስያሜ ይታወቃል፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ እርሱ፡ በፈጣሪነቱ ተስፋ የሰጠበት፤ ፍጡሩም፡ ለ፭ሺ፭፻ ዓመታት፡ በተስፋ ሲጠብቀው የኖረው፡ የምሕረት ቃል ኪዳኑ፡ በእናቲቱ ቤተ መቅደስነትና በልጇ መሥዋዕትነት ለመፈጸሙ፡ መታሰቢያ ኾኖ ይዘከራል፡፡

የወሩ ፲፯ኛ ቀን፡ "እስጢፋኖስ" ተብሎ፡ ጥቅምት ፲፯ ቀን የሚውለው፡ የአዲስ ኪዳኑ ቀዳሚ ሰማዕት፡ የቅዱስ እስጢፋኖስ በዓለ ሢመት ይታሰብበታል፡፡

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል።

## ስለበዓላት ዝርዝር ሐተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ።

### የወሩ በዓላት።

---

የወሩ ፲፰ኛ ቀን፡ "ጦቢያ"፡ ወይም፡ "ኢትዮጵያ" ይባላል፤ ሐምሌ ፲፰ ቀን የሚውለው የኢትዮጵያውያኑ፡ ጦቢያና ጦቢት (ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት)፡ ዕረፍታቸው ስለሚታሰብበት ነው።

የወሩ ፲፱ኛ ቀን፡ "ገብርኤል" ተብሎ፡ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው፡ ሊቀ መላእክት፡ አብሣሪነቱ ይታሰብበታል።

የወሩ ፳ኛ ቀን፡ "ሕንፀታ" ተብሎ፡ የመጀመሪያዋ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፡ በአንጾኪያ የተሠራበት ዕለት ይዘከርበታል።

የወሩ ፳፩ኛ ቀን፡ "ማርያም" ይባላል፡ የአምላክ እናት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከዚህ ዓለም ሕይወተ ሥጋ፡ በሰላም ባረፈችበት፡ ለጥር ፳፩ ቀን መታሰቢያ በመኾኑ ነው።

የወሩ ፳፪ኛ ቀን፡ "ዑራኤል" ይባላል፡ የአምላክ እናት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ሕፃን ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን አዝላና ታቅፋ፡ በስደት፡ ወደምድረ ግብፅ ከመውረዳቸው በፊት፡ ወደትውልድ አገራቸው፡ ወደኢትዮጵያ ገብተው፡ ከዚያም፡ በኢትዮጵያውያን ገዳም፡ በቍስቋም በቆዩባቸው ዓመታት፡ በጉዟቸው ኹሉ ያልተለያቸው፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ዑራኤል ይታሰብበታል።

የወሩ ፳፫ኛ ቀን፡ "ጊዮርጊስ"፡ ወይም፡ "ጴጥሮስ" ተብሎ፡ ስለእውነተኛዪቱ የክርስትና ሃይማኖት፡ እስከመጨረሻው ጸንተው፡ በሰማዕትነት ተጋድለው ያረፉት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች፡ ቅዱስ ጊዮርጊስና ኢትዮጵያዊው አቡነ ጴጥሮስ ይታሰቡበታል።

የወሩ ፳፬ኛ ቀን፡ "ተክለ ሃይማኖት"፡ ወይም፡ "ክርስቶስ ሠምራ" ይባላል፤ ስለእውነተኛዪቱ የክርስትና ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ እስከመጨረሻው ጸንተው የተጋደሉት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ታማኞች አገልጋዮች፥ ለወንዶች ኢትዮጵያውያን፡ በመልካም አርአያነቱ የሚጠቀሰው፡ ኢትዮጵያዊው ጻድቅ፡ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖትና ለሴቶች ኢትዮጵያውያት፡ በመልካም አርአያነቷ የምትጠቀሰው፡ ኢትዮጵያዊቷ ጻድቅት፡ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ የሚታሰቡበት ዕለት በመኾኑ ነው።

የወሩ ፳፭ኛ ቀን፡ "ሰሎሜ"፥ ወይም፡ "መርቆሬዎስ" ተብሎ፡ ሕፃኑን ኢየሱስ ክርስቶስንና ቅድስት እናቱን፡ ድንግል ማርያምን፡ በስደታቸው ጊዜ ሳትለያቸው ያገለገለችው፡ ቅድስት ሰሎሜና ተጋዳዩ ሰማዕት ቅዱስ መርቆሬዎስ ይዘከሩበታል።

የወሩ ፳፮ኛ ቀን፡ "ዮሴፍ" ተብሎ፡ የአምላክን እናት ቅድስት ድንግል ማርያምንና ሕፃን ልጇን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመጠበቅና ለማገልገል፡ ከእግዚአብሔር፡ በታማኝነት የተጠራው፡ አረጋዊው ጻድቅ ይታሰብበታል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

የወሩ ፳፯ኛ ቀን፡ "መድኃኔ ዓለም" ይባላል፤ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል ላይ ቤዛ ኾኖ መሥዋዕትነትን በመክፈል፡ ፍጡሩ የሰው ዘር፡ በራሱ ፍላጎትና ምርጫ፡ የከፋት ተገዢ፡ የኃጢአት ቀንበር ተሸካሚና የሞት ፍጻ ከፋይ ኾኖ ከሚማቅቅበት ሥቃይ ያዳነበት፡ ወደቀደመ ማዕርጉም የመለሰበት የቸርነቱና የፍቅሩ ድንቅ ሥራ በተመስጦ የሚዘከርበት ዕለት ነው።

የወሩ ፳፰ኛ ቀን፡ "አማኑኤል" ይባላል፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአምላክ እናት በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን ባደረ ጊዜ፡ መለኮታዊ አካሉና ባሕርዩ፡ ከነፍሷ ነፍስን፡ ከሥጋዋም ሥጋን ነሥቶ፡ ከሰውነት አካልና ባሕርይ ጋር በፍጹም ስለተዋሐደ፡ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው!" ለማለት "አማኑኤል" የተባለበት የትርጓሜ ስም፡ ይታሰብበታል።

የወሩ ፳፱ኛ ቀን፡ "በዓለ ወልድ"፡ ወይም፡ "በዓለ እግዚአብሔር" ይባላል፤ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጥንተ ትንሣኤው የተፈጸመው፡ ወሩ መጋቢት ኾኖ፡ በዚህ ቀን በመኾኑ ነው።

የወሩ ፴ኛ ቀን፡ "መልከ ጼዴቅ"፡ ወይም፡ "አመ ሠላሳ" ይባላል፤ ኢትዮጵያዊነትን የመሠረተው መልከ ጼዴቅ የሚዘከርበት፡ እንዲሁም፡ የወሩ መጨረሻ ሠላሳኛ ቀንና የዕለታቱ ማጠቃለያ በመኾኑ ነው።

### የወር በዓላት ስም ዝርዝር።

በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ሰላሣዎቹ የወሮቹ ቀናት፡ ተለይተው የሚታወቁባቸው አጫጭር ስሞች፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፦

የወሩ ፩ኛ ቀን፡ "ልደታት"፤
የወሩ ፪ኛ ቀን፡ "መጥምቀ ዮሐንስ"፤
የወሩ ፫ኛ ቀን፡ "በአታ"፤
የወሩ ፬ኛ ቀን፡ "ዮሐንስ ወንጌላዊ"፤
የወሩ ፭ኛ ቀን፡ "አቡየ"/"አቦ"
የወሩ ፮ኛ ቀን፡ "ቍስቋም"፤
የወሩ ፯ኛ ቀን፡ "ሥላሴ"፤
የወሩ ፰ኛ ቀን፡ "ኢየሱስ"፤
የወሩ ፱ኛ ቀን፡ "አጼ ዳዊት"፤
የወሩ ፲ኛ ቀን፡ "መስቀለ ኢየሱስ"፤
የወሩ ፲፩ኛ ቀን፡ "ሐና"፤
የወሩ ፲፪ኛ ቀን፡ "ሚካኤል"፤
የወሩ ፲፫ኛ ቀን፡ "ደብረ ታቦር"፤
የወሩ ፲፬ኛ ቀን፡ "አረጋዊ"/"ገብረ ክርስቶስ"፤
የወሩ ፲፭ኛ ቀን፡ "ቂርቆስ"፤

# ምዕራፍ ፮፡ በዓል::

## ስለበዓላት ዝርዝር ሓተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ::

### የወር በዓላት ስም ዝርዝር::

---

የወሩ ፲፮ኛ ቀን፡ "ኪዳነ ምሕረት"፡
የወሩ ፲፯ኛ ቀን፡ "እስጢፋኖስ"፡
የወሩ ፲፰ኛ ቀን፡ "ጦቢያ (ኢትዮጵያ)"፡
የወሩ ፲፱ኛ ቀን፡ "ገብርኤል"፡
የወሩ ፳ኛ ቀን፡ "ሕንጸታ"፡
የወሩ ፳፩ኛ ቀን፡ "ማርያም"፡
የወሩ ፳፪ኛ ቀን፡ "ዑራኤል"፡
የወሩ ፳፫ኛ ቀን፡ "ጊዮርጊስ"፡
የወሩ ፳፬ኛ ቀን፡ "ተክልዬ"/"ክርስቶስ ሠምረ"፡
የወሩ ፳፭ኛ ቀን፡ "ሰሎሜ"/"መርቆሬዎስ"፡
የወሩ ፳፮ኛ ቀን፡ "ዮሴፍ"፡
የወሩ ፳፯ኛ ቀን፡ "መድኃኔ ዓለም"፡
የወሩ ፳፰ኛ ቀን፡ "አማኑኤል"፡
የወሩ ፳፱ኛ ቀን፡ "በዓለ ወልድ"፡
የወሩ ፴ኛ ቀን፡ "መልከ ጼዴቅ"/አመ ሠላሳ::

### የዓመቱ በዓላት::

የዓመቱ በዓላት፡ በወሩቱ በዓላት ስያሜና ቅደም ተከተል መሠረት፡ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

፩ኛ፡ "ልደታት"፡- መስከረም ፩ ቀን፡ የዓመቱ በዓል፡ "ዓውደ ዓመት" ተብሎ፡ በዓቢይ በዓልነት ይከበራል:: ይኸውም፡ በመጀመሪያው ይህ ቀን፡ የፈጣሪ ዕፁብ ድንቅ ሥራ የኾነው ሥነ ፍጥረት፡ ከለመኖር ወደመኖር የመጣበት ነው፡" ተብሎ፡ ዝክሩ ስለሚደረግበት፡ የዚሁ ሥነ ፍጥረት ምሥጢራት ኹሉ፡ ምሳሌዋ የኾኑላት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም እና የፈጠረውን ፍጥረት ኹሉ፡ በጥራት አዋህዶ፡ ለፍጹሙ መልካም ሕይወት ያበቃው፡ የዓመተ ምሕረትንም ዘውድ ያቀዳጀው፡ ራሱ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚሁ ቀን፡ ከእርሷ፡ በሰውነት ስለተወለደበት ነው::

ስለዚህ፡ መስከረም ፩ ቀን፡ በአጠቃላይ፡ የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት፡ አዳምና ሔዋን የተፈጠሩበት፡ በእግዚአብሔርና በእነርሱ መካከል ያለው መልካም ግንኙነት ተከብሮ ይኖር ዘንድ፡ እንዲጠብቁት፡ ለምልክት የሠራላቸው፡ የጋብቻ ቃል ኪዳናቸውንም፡ ከፈጣሪያቸው የተቀበሉበት፥ የመጨረሻዎቹና ዘለዓለማውያኑ እውነተኞቹ አዳምና ሔዋን፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም የተወለዱበት፡ ኢትዮጵያም፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነት ተመሥርታ፡ የነጻነት ህልውናዋን የጀመረችበት ዕለት የሚዘከርበት በመኾኑ፡ በየዓመቱ፡ በታላቅ የምስጋና በረከት፥ የደስታ ስሜትና የአክብሮት ድምቀት ይከበራል::

በመጽሓፍ፡ *"መበዛቲ ዕለት፡ ተነፀበ ኢዮብ፡ በማየ ተከዚ፡ መተፈወሰ እምኵሉ ደዌሁ!"* ማለትም፡ *"በዚች ዕለት፡ ኢዮብ፡ በተከዜ ውኃ ታጥቦ፡ ከደዌው ኹሉ ዳነ!"* የሚል አብነት አለ።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህን ቃል መሠረት በማድረግ፡ ጳጕሜ ፫፡ ወይም ፯ ቀን፡ ሌሊት፡ ለመስከረም ፩ ቀን አጥቢያ፡ "ከሥጋ ደዌ፡ ከነፍስ ኃጢአትና ከመንፈስ ርኵሰት የነጻንበት፡ የእግዚአብሔር ጸጋ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም የተገኘበት፡ የምሕረት ዘመን፡ እነሆ ገባልን!" በማለት፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በዚህ ቀን፡ ሌሊት፡ በማለዳ፡ ወደወንዝ ወርደን፡ ወይም፡ በየቤታችን፡ በቀዝቃዛ ውኃ እንታጠባለን፡ ኢዮብ፡ ኢትዮጵያዊ መኾኑ፡ በዚህ፡ "በተከዚ ውኃ" ባለው ቃል ይታወቃል።

በዚሁ በመስከረም ፩ ቀን፡ የዓመት በዓላቸው፡ አብሮ የሚከበርላቸው፡ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ራጉኤል ተራዳኢነትና ከ፲፪ቱ ሐዋርያት፡ ፩ዱ የኾነው፡ የቅዱስ በርተሎሜዎስ ዕረፍት ሲኾኑ፡ በተለያዩት ወራት፡ በወሩ የመጀመሪያ ቀን፡ የዓመት በዓላቸው የሚከበርላቸው ደግሞ፡- በኅዳር ፩ ቀን፡ መንግሥቱን፡ በኢትዮጵያዊው የመልከ ጼዴቅ ሥርዓት፡ ይመራና ያስተዳድር የነበረ፡ የቅዱስ አጼ ነአኵቶ ለአብ ዕረፍት፡ በታኅሣሥ ፩ ቀን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተፀነሰበት፡ የብሥራተ ገብርኤልና የዕለተ ትስብእት ዝክር፡ የነቢዩ ኤልያስም ዕርገተ ሥጋ፡ የንጉሥ ሰሎሞን እናት፡ የቤትሳባ ኢትዮጵያዊትና በጥር ፩ ቀን፡ ለእውነት፡ በይፋ መስክሮ፡ የቀዳሚ ሰማዕትነትን ጽዋ የተቀበለው፡ የዲያቆኑ እስጢፋኖስ ዕረፍት ናቸው።

እንዲሁም፡ በየካቲት ፩ ቀን፡ መቅዶንዮስን ለማውገዝ፡ በ፫፻፹፩ ዓ.ም. በቍስጥንጥንያ የተደረገው የ፻፶ ሊቃውንት ጉባዔ፡ በመጋቢት ፩ ቀን፡ የመተማው ኢትዮጵያዊ ሰማዕት፡ የአጼ ዮሐንስ ፬ኛ ዕረፍት፡ በግንቦት ፩ ቀን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሊባኖስ ተራራ ዛፍ ሥር፡ በሜጸ የመወለዷ መታሰቢያ፡ በሰኔ ፩ ቀን፡ ወንድሞቹ የሸጡት፡ የያዕቆብ ልጅ የዮሴፍና በግብፅ ያገባት ሚስቱ፡ የአስናት መታሰቢያ፡ በነሐሴ ፩ ቀን፡ የጌታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን የሥጋ አካል፡ አይሁድን ሳይፈሩ፡ ጲላጦስንም ደፍረው ጠይቀው፡ ከመስቀል አውርደው የቀበሩት፡ ጻድቃን ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ዓመታዊ በዓላቸው ይከበራል።

፪ኛ፡ "መጥምቁ ዮሐንስ"፡- መስከረም ፪ ቀን፡ መጥምቁ ዮሐንስ፡ "ምትረተ ርእሱ ለዮሐንስ" በተባለችው፡ በዚች ዕለት፡ አንገቱን ተሠይፎ፡ በሰማዕትነት ያረፈባት ስለኾነች፡ የዓመት በዓሉ ይከበርባታል።

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በኹለተኛው ቀን፡ የዕረፍታቸው ዓመታዊ በዓል የሚከበርላቸው፡ በጥቅምት ፪ ቀን፡ የቅዳሴ ማርያም ደራሲ፡ የአባ ሕርያቆስ፥ በጥር ፪ ቀን፡ ወንድሙ ቃኤል የገደለው ጻድቁ አቤል፡ በግንቦት ፪ ቀን፡ ጻድቁ ኢዮብ፥ ሐምሌ ፪ ቀን፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት፡ ፩ዱ የኾነው፡ ቅዱስ ታዴዎስ ናቸው።

፫ኛ፡ "በአታ ለማርያም"፡- ታኅሣሥ ፫ ቀን፡ እናታችንና ንግሥታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የቅዱሳን ወላጆቿ ስዕለት ስለተፈጸመ፡ እግዚአብሔርን ታገለግል ዘንድ፡ በሦስት ዓመታት የሕፃንነት ዕድሜዋ፡ ወደቤተ መቅደስ ገብታ መኖር የጀመረችበት ዕለት ስለኾነ፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል።

# ምዕራፍ ፮፣ በዓል::

## ስለበዓላት ዝርዝር ሐተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ::

### የዓመቱ በዓላት::

---

በዚሁ ዕለት: ከተራዳኢው: ከሊቀ መላእክት ቅዱስ ፋኑኤል ጋር: የዳግማዊ አጼ ምኒልክና የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ: የዕረፍታቸው ዓመታዊ ዝክር: አብሮ ይታሰባል::

በተለያዩት ወራት: ከወሩ: በሦስተኛው ቀን: የዕረፍታቸው ዓመታዊ በዓል የሚከበርላቸው ደግሞ: መስከረም ፫ ቀን: የኢትዮጵያዊው ጻድቅ: የአባ አንበስ: ጥር ፫ ቀን: የኢትዮጵያዊው ጻድቅ የአባ መጣዕ (ሊባኖስ) ሲኾን: በየካቲት ፫ ቀን: በ፲፭፻፳፬ ዓ.ም.: የግሼን ማርያም አምባ: በግራኝ አሕመድ ጦር መበዝበዝ: ጳጉሜ ፫ ቀን: የሊቀ መላእክት ቅዱስ ሩፋኤል ተራዳኢነትና የሃይማኖት ቀናተኛው: የአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዕረፍት ዓመታዊ ዝክር ይታሰቡባቸዋል::

፬ኛ: "ዮሐንስ ወንጌላዊ":- ጥር ፬ ቀን: ከ፲፪ቱ ሐዋርያት: ፩ዱ የኾነው: የወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ : የዕረፍቱ ዓመት በዓል ይከበራል::

በተለያዩት ወራት: ከወሩ: በአራተኛው ቀን: የዕረፍታቸው ዓመታዊ በዓል የሚከበርላቸው: ጥቅምት ፬ ቀን: ክርስትናን ያስፋፉ: ቅዱሳን አብርሃ ወአጽብሐ: የኢትዮጵያ ወንድማማች ነገሥታት: ታኅሣሥ ፬ ቀን: ከ፲፪ቱ ሐዋርያት: ፩ዱ የኾነው: ቅዱስ እንድርያስ: የካቲት ፬ ቀን: የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ሚስትና የአድዋው የድል ጦርነት: ተከታይ አዝማች: እቴጌ ጣይቱ ብጡል: "ብርሃን ዘኢትዮጵያ" ሲኾኑ: ጳጉሜ ፬ ቀን: የቅዱሳን ኹሉ: የመታሰቢያቸው ዓመት በዓል ይደረጋል::

፭ኛ: "አባ ገብረ መንፈስ ቅዱስ":- መጋቢት ፭ ቀን: የጻድቁ ባለገድል: የአባ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዕረፍት: በዓመት በዓልነት ይከበራል::

በተለያዩት ወራት: ከወሩ: በአምስተኛው ቀን: የዕረፍታቸው ዓመታዊ በዓል የሚከበርላቸው: መስከረም ፭ ቀን: በሄሮድስ ትእዛዝ የተሠየፉት: ፻፵፬ሺ ሕፃናትና የአሕመድ ግራኝን ወረራ: በአገር ፍቅርና በሃይማኖት ጽናት ተቋቁሞ የተጋደለ: አጼ ንብለ ድንግል: ኅዳር ፭ ቀን: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን: በመስቀል ላይ ሣለ: ጎኑን: በጦር ወግቶት የነበረውና ኋላ: አምኖ: ሰማዕትነትን የተቀበለው: ቅዱስ ለንጊኖስ: ሚያዝያ ፭ ቀን: ነቢዩ ሕዝቅኤል፥ ግንቦት ፭ ቀን: ታላቁ ኢትዮጵያዊው ነቢይ ኤርምያስ፥ እንዲሁም: ኢትዮጵያውያኑ የብሉዩ ኪዳን ደቀ መዛሙርቱ: አቤሜሌክና ባሮክ፡ ሐምሌ ፭ ቀን: ቅዱሳን ሐዋርያት፥ በተለይም: ከ፲፪ቱ ሐዋርያት: ፩ዱ የኾነውና ሊቀ ሐዋርያት የኾነው ቅዱስ ጴጥሮስ፥ ደግሞም: ቅዱስ ጳውሎስ፥ ነሐሴ ፭ ቀን: ኢትዮጵያዊው አባ ፊልጶስ ዘደብረ ቢዘን ናቸው::

፮ኛ: "ደብረ ቍስቋም":- ኅዳር ፮ ቀን: ቅድስት ድንግል ማርያም: ሕፃን ልጇን: ኢየሱስ ክርስቶስን: ከሄሮድስ ሠይፍ ለማዳን: በሊቀ መላእክት ቅዱስ ዑራኤል መሪነትና ጠባቂነት: ከጻድቁ ቅዱስ ዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር: ሕፃኑን ይዛ: ወደብሔረ ትውልዷ: ወደኢትዮጵያ ሸሽታ የመጣችበት: ቅዱሱ ጉዞዋና ጉብኝቷ ይዘከርበታል::

ከዚህ ተያይዞም፡ *"ልጆን፡ ከግብፅ ጠራሁት!"* የሚለው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ፡ በግብፅ ምድር ወደምትገኘውና የኢትዮጵያውያን ንብረት ወደኾነችው፡ "ደብረ ቊስቋም" ወደምትባለው ገዳም፡ በስደት ኼደውና በዚያ ቆይተው፡ በሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ቃል መሠረት፡ ወደናዝሬት ስለተመለሱ፡ የስደት ጊዜያቸው፡ በቆዩበት ሥፍራ ስም፡ "ደብረ ቊስቋም" ተብሎ፡ የዓመቱ በዓል ይከበራል::

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በስድስተኛው ቀን፡ ዓመታዊ በዓላቸው የሚከበርላቸው፡ መስከረም ፮ ቀን፡ የታላቁ እስራኤላዊ ነቢይ የኢሳይያስ፡ የነቢዩ የሳሙኤል እናት፡ ሐና ነቢይትና በሃይማኖት ምክንያት፡ ከመካከለኛው ምሥራቅ፡ ወደኢትዮጵያ ተሰድደው ከገቡት ከ፬፻ኙ ቅዱሳን ፩ዱ አባ ጰንጠሌዎን ዕረፍት ሲኾን፤ ታኅሣሥ ፮ ቀን፡ በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር፡ በሰማዕትነት የተገደሉት፡ የአዲስ ዓለም ማርያም ካህናት፡ ደግሞም፡ ጥር ፮ ቀን፡ የዕርገተ ኤልያስና የዕረፍተ ኖኅ፡ የካቲት ፮ ቀን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ለመቃብሬ አደረገችው!"* ያለውን የሽቱ ቅባት በራሱ ላይ አፍስሳ፡ በእንባዋ እግሩን ያብበሰችው የማርያም እንተ ዕፍረት፡ እንዲሁም፡ ሚያዝያ ፮ ቀን፡ የ፲፰፻፰ ዓመተ ምሕረቱ፡ የመቅደላው ጀግና፡ የዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ፡ ግንቦት ፮ ቀን፡ የደብረ ሊባኖሷ ቅድስት ስሉሜ ኢትዮጵያዊት ዕረፍት፥ ሰኔ ፮ ቀን፡ በሸዋ ቆላ፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር፡ በራያ እስላሞች እየተሰለቡ ያለቁት የኢትዮጵያውያን ሰማዕታትና ሐምሌ ፮ ቀን፡ የነቢዩ ዕዝራ ዕርገተ ሥጋ መታሰቢያ፡ ነሐሴ ፮ ቀን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ፡ በቅድሚያ አይታ፡ ለሌሎች ለማብሠር የታደለችው፡ የማርያም መግደላዊት ዕረፍት፡ ዓመታዊ መታሰቢያ ይከበራል::

፯ኛ፡ "ቅድስት ሥላሴ"፡- ጥር ፯ ቀን፡ ቀደም ብሎ፡ በብሥራተ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ ታኅሣሥ ፯ ቀን፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን ውስጥ በተፈጸመው ትስብእት (በኢየሱስ ክርስቶስ መፀነስ፡ የወልድ ሰው መኾን)፡ የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ምሥጢር የተገለጸበት ወራት በመኾኑ፡ የቅድስት ሥላሴ ዓመታዊ በዓል ኾኖ ይከበራል::

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በሰባተኛው ቀን፡ የዕረፍታቸው ዓመታዊ በዓል የሚከበርላቸው፡ መስከረም ፯ ቀን፡ የመጥምቁ ዮሐንስ እናት፡ ኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ኤልሣቤጥና ለሥልጣን መጋደሉን ጠልቶ፡ ወደገዳም የገባ፡ መናኔ መንግሥት አጼ ተክለ ሃይማኖት ሲኾኑ፡ ታኅሣሥ ፯ ቀን፡ የዕንስታ ለማርያም፡ ሚያዝያ ፯ ቀን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም አባት፡ ቅዱስ ኢያቄም ዕረፍት፡ ሐምሌ ፯ ቀን፡ ሥላሴ፡ በአብርሃም ቤት ገብተው፡ ስለይስሐቅ መወለድ፡ ተስፋውን፡ ለአዛውንቱ አብርሃምና ሣራ ያሰሙበት ዕለትና በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር፡ በሰማዕትነት የተገደሉት፡ የ፫፻፳ቱ የደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኰሳት መታሰቢያ፥ እንዲሁም፡ ዕረፍታቸው፡ ነሐሴ ፯ ቀን ፲፭፻ ዓ.ም. የኾነው፥ "መልክዓ ማርያምንና መልክዓ ኢየሱስን ደርሰዋል!" የሚባሉት፥ "ለ፫ኛው ሺ አታድርሰኝ!" እያሉ፡ ወደፈጣሪያቸው ይጸልዩ የነበሩት፡ የአጼ ናዖድ ዝክር፡ በዚሁ ቀን ይከበራል::

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል።
## ስለበዓላት ዝርዝር ሐተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ።
### የዓመቱ በዓላት።

---

፮ኛ፡ "ግዝረተ ኢየሱስ"፡- መስከረም ፮ ቀን፡ የሕፃን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የግዝረቱ ዓመት በዓል ይከበርበታል።

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በስምንተኛው ቀን፡ የዕረፍታቸው ዓመታዊ በዓል የሚከበርላቸው፡ መስከረም ፮ ቀን፡ የመጥምቁ ዮሐንስ አባት፡ ካህኑ ዘካርያስና "ርእሰ ነቢያት" የኾነው፡ ሙሴ፡ እርሱም፡ በኢትዮጵያ ኖሮ፥ ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶና ኢትዮጵያውያን ልጆችን ወልዶ፥ በዚያ ሣለም፡ ስለእግዚአብሔርና ስለአምልኮተ እግዚአብሔር አውቆ፥ ከእርሱ፡ ከእግዚአብሔርም፡ ትእዛዝን ተቀብሎ፡ የእስራኤልን ልጆች፡ ከግብፅ መርቶ ያወጣው ሲኾን፥ ኅዳር ፮ ቀን፡ የሥላሴን መንበረ ጸባዖት መለኮታዊ ዙፋን የሚሸከሙት፡ የአርባዕቱ እንስሳ መታሰቢያ፥ ደግሞም፡ ታኅሣሥ ፮ ቀን፡ የኢትዮጵያዊው አባ ኪሮስና መጋቢት ፮ ቀን፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት፡ ፩ዱ የኾነው፡ የቅዱስ ማትያስ የዕረፍታቸው፥ እንዲሁም፡ ግንቦት ፮ ቀን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከትንሣኤው በኋላ፡ የመጀመሪያ ዕርገቱን የፈጸመባት ዕለተ ሐሙስ የምትዘከርባት ዓመት በዓል ይከበራል።

፱ኛ፡ "እጼ ዳዊት"፡- ጥቅምት ፱ ቀን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን ግማደ መስቀል፡ በዘመኑ፡ ከኢየሩሳሌም ወደኢትዮጵያ ያስመጣውና "ዓባይን እገድባለሁ!" እያለ በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ክርስቲያኖችን፡ ከእስላሞች ጥቃት ያዳነ እጼ ዳዊት ያረፈበት በመኾኑ፡ የዓመቱ በዓል ይዘከርበታል።

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በዘጠነኛው ቀን፡ ዓመታዊው በዓል የሚከበርላቸው፡ ኅዳር ፱ ቀን፡ አርዮስን ለማውገዝ፡ በ፫፻፳፭ ዓ.ም. በኒቅያ የተደረገው የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉባኤ መታሰቢያ ሲኾን፡ ታኅሣሥ ፱ ቀን፡ የኢትዮጵያዊው አባ በአሚን፡ ግንቦት ፱ ቀን፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል፡ በኢየሩሳሌም፡ በምሕላ ጸሎት፡ ከተቀበረበት፡ አስገኝታና አስቆፍራ ያስወጣችው፡ የንጉሥ ቈስጠንጢኖስ እናት፡ የንግሥት ዕሌኒና ሰኔ ፱ ቀን፡ የታላቁ የእስራኤል ነቢይ ሳሙኤል፡ የዕረፍታቸው ዓመት በዓል ይከበራል።

፲ኛ፡ "መስቀለ ኢየሱስ"፡- መስከረም ፲ ቀን፡ "እጼ መስቀል"ም ተብሎ፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀል፡ ከኢየሩሳሌም ወደኢትዮጵያ ክልል በመግባት፡ መሬቷን የባረከበት ቀን የሚታሰብበት በዓል ነው። ከዚህ የተነሣ፡ ግማደ መስቀሉን ለማስመጣት ዕድሉን ለማግኘት ከበቃው፡ ከኢትዮጵያዊው እጼ ዳዊት ዘመን ጀምሮ፡ እጼው፡ ከእቴጌዪቱ ጋር በቤተ መንግሥቱ አደባባይ፡ በዙፋኑ በሚታይበት፥ እጨጌው፥ ቢትወደዱና ጸሐፌ ትእዛዙም፡ በየመንበራቸው በተቀመጡበት፥ ከቤተ ሕዝቡ፥ ከቤተ ክህነቱና ከቤተ ምልክናው ወገኖች የተወከሉ ተጠሪዎች፡ በየክብር መለያ ልብሶቻቸው ተሸልመው በተገኙበት፥ ሕዝባውያኑ፡ በአጀባቸው፥ ካህናቱ፡ *"ተቀጸል ጽጌ፥ አጼጌ!"* ማለትም፡ *"አጼ ሆይ! በባለሟሎችህና በሕዝብህ ተከበህ፡ የአበቦችን ዘውድ ተቀዳጅ!"* በሚለው ጣዕመ ዜማቸው፥ መለካውያኑ ብላቴኖችም፡ በጽጌረዳ ጕንጕናቸው፡ የየበኩላቸውን ወርኃዊ በረከት በማቅረብ፡ በዓሉ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ በኢትዮጵያ፡ በየዓመቱ፡ በታላቅ ሥርዓት ይከበራል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በአሥረኛው ቀን፡ ዓመታዊ በዓል የሚደረግላቸው፡ ጥቅምት ፲ ቀን፡ ሕፃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአሪቱ ሥርዓት፡ በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም፡ በአርባ ቀኑ፡ በእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም እቅፍ፡ ከመሥዋዕቱ ጋር፡ ወደቤተ መቅደስ የገባበትና ለአረጋዊው ጻድቅ ስምዖንና ለሐና ነቢይት ተገልጾ የታየበት፡ የ"በዓለ ስምዖን" መታሰቢያ፡ እንዲሁም፡ ካቶሊክነትን ተቋቁሞ፡ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ያጸና፡ የአጼ ፋሲል ዕረፍት፡ ታኅሣሥ ፲ ቀን፡ ፲፭፻፳፬ ዓ.ም.፡ በአሕመድ ግራኝ ጦር የተፈጸመው፡ የደብረ እግዚአብሔርና የሓይቅ መካነ እስጢፋኖስ መበዝበዝና መቃጠል፡ ጥር ፲ ቀን፡ ለጥምቀት የሚያገለግል ውኃ፡ ከወንዝ የሚከተርበት፡ "ከተራ" የሚባለው የጥምቀት በዓል ዋዜማ፡ የካቲት ፲ ቀን፡ "የእልፍዮስ ልጅ" የሚባለውና ከ፲፪ቱ ሐዋርያት፡ ፩ዱ የኾነው፡ የቅዱስ ያዕቆብ፡ ግንቦት ፲ ቀን፡ በሃይማኖታቸው፡ ከባቢሎን እሳት የዳኑት፡ የአናንያ፡ የአዛርያና የሚሳኤል፡ ዕረፍት በሚውሉባቸው ዕለታት፡ የዓመት በዓሎቻቸው ይከበራሉ።

፲፩ኛ፡ "ቅድስት ሐና"፡- ኅዳር ፲፩ ቀን፡ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም እናት የኾነችው፡ የኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ሓና፡ የዕረፍቷ የዓመት በዓል፡ ይልቁንም፡ ከዓመቱ ዓበይት በዓላት አንዱ የኾነው፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትና በሓዋርያው ፊልጶስ እጅ የተጠመቀው፡ "አቤሜሌክ" የተባለው፡ የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መታሰቢያ፡ ጥር ፲፩ ቀን፡ በታላቅ ብሔራዊ ሥነ ሥርዓት ይከበራል።

በዚሁ በበዓለ ጥምቀት ዕለት፡ ካህናቱና ሕዝቡ፡ ታቦታቸውን ባሳረፉበት ድንኳን ውስጥና ዙርያ ቆመው ሲያስቀድሱ ሣሉ፡ ሠራዒው ቄስ፡ *"አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፡ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ!"* የሚለውን መግቢያ፡ በልዑል ዜማ ጀምሮ፡ "ሃሌ ሉያ" ብሎ እስከፈጸመበት ጊዜ ድረስ፡ በፊት ለፊታቸው፡ እንደፏፏቴ ይወርድ የነበረው የወንዙ ውኃ፡ ቀጥ ብሎ ቆመላቸው! ይህ ተአምር የተፈጸመለት፡ በመንፈሳዊ ብቅዓቱ ይታወቅ የነበረው፡ ቤተሰቡን፡ ከአማራ ሳይንት ይዞ፡ በተጉለት አውራጃ፡ ልዩ ስሙ፡ "ታቦት ዋሻ" በሚባለው ሥፍራ፡ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን በመትከል፡ በዚያ ሲያገለግል የኖረው፡ የኋላ ኋላም፡ በአጼ ምኒልክ ዘመን፡ አዲስ አበባ ስትመሠረት፡ በተወላጆቹ አማካይነት፡ አብዛኛዎቹን አድባራት በመቈርቈር፡ በማስተማርና በማገልገል፡ ከአምላክ ኢትዮጵያ የተጠራበትን ክህነታዊ ተልእኮ እስካኹን ያላቋረጠው፡ የትልቁ ካህን ወልደ ኢየሱስ ዝክር፡ በበዓሉ ላይ ይታሰባል።

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በአሥራ አንደኛው ቀን፡ ለየዕረፍታቸው፡ ዓመታዊ በዓል የሚደረግላቸው፡ መስከረም ፲፩ ቀን፡ ስመ ጥሩው ምሁር፡ አጼ በካፋ፥ መጋቢት ፲፩ ቀን፡ በሃይማኖት ስደት፡ ከመካከለኛው ምሥራቅ፡ ወደኢትዮጵያ ከገቡት ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ፡ አባ አሌፍ፥ ግንቦት ፲፩ ቀን፡ ገናናው ኢትዮጵያዊው ደራሲና ማኅሌታይ ካህን፡ ቅዱስ ያሬድና የባሌው መምህር፡ አባ አሴር ናቸው።

፲፪ኛ፡ "ቅዱስ ሚካኤል"፡- ኅዳር ፲፪ ቀን፡ "መልአከ ምሕረት" የሚባለው፡ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል፡ የተራዳኢነቱ፡ የዓመት በዓል መታሰቢያ፡ በጥር ፲፪ እና በሰኔ ፲፪ ቀኖች ጭምር ይከበራል።

# ምዕራፍ ፤፤ በዓል።

## ስለበዓላት ዝርዝር ሐተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ።

### የዓመቱ በዓላት።

---

በተለያዩት ወራት: ከወሩ: በአሥራ ኹለተኛው ቀን: ዓመታዊ በዓል የሚደረግላቸው: መስከረም ፲፪ ቀን: ንስጥሮስን ለማውገዝ: በ፬፻፴፩ ዓ.ም. በኤፌሶን የተደረገው: የ፪፻ ሊቃውንት ጉባዔ መታሰቢያ: ለየዕረፍታቸውም: ጥቅምት ፲፪ ቀን: ከ፲፪ቱ ሐዋርያት: ፩ዱ የኾነው: ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስና የባሕረ ሐሳቡ ሊቅ: ቅዱስ ድሜጥሮስ: ኅዳር ፲፪ ቀን: የሃይማኖት ተጋዳዩ: አጼ በእደ ማርያም: ታኅሣሥ ፲፪ ቀን: ኢትዮጵያዊው አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ ሲኾኑ: ጥር ፲፪ ቀን የሚውለው: ከፀበይት የዓመቱ በዓላት አንዱ የኾነው: አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ: በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ ተገኝቶ: የእናቱን የቅድስት ድንግል ማርያምን ፈቃድ በመፈጸም: አማላጅነቷን ያሳወቀበት: ውኃውንም ወደጠጅነት በለወጠበት ተአምራቱ: አምላክነቱን የገለጠበት ዕለት: የካቲት ፲፪ ቀን በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም.: በፋሺስት ኢጣልያን ጦር: በሰላማዊው ሕዝብ ላይ: በአዲስ አበባና በመላዋ ኢትዮጵያ ከተካኼደው አሠቃቂ እልቂት: ሚያዝያ ፲፪ ቀን: ፲፭፻፳፫ ዓ.ም.: በግራኝ አሕመድ ከተፈጸመው: የደብረ ብርሃን ከተማ ቃጠሎ መታሰቢያ ጋር: ዕረፍታቸው: የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅና በ፲፬፻፵፮ ዓ.ም. የእስላምን ወራሪ ጦር ሲከላከል: ሰማዕትነትን: በወጣትነቱ የተቀበለ: የአጼ እስክንድር: ግንቦት ፲፪ ቀን: እንዲሁም: ፲፪ቱን አብያተ ክርስቲያን: በላስታ: ከዓለት ፈልፍሎ ያሳነፀ: የቅዱስ አጼ ላልይበላል (ላሊበላ): ሰኔ ፲፪ ቀን: ፲፩፻፸፫ ዓ.ም. የሚውለው ይከበራል።

፲፫ኛ: "ደብረ ታቦር":- ነሐሴ ፲፫ ቀን: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: "ታቦር" በተባለው ተራራ ላይ: ግርማ መለኮቱን: ለተመረጡት ባለሟሎቹ የገለጸበትና በእውን ያሳየበት መታሰቢያ ሲኾን: ኢትዮጵያውያን: ችቦ እያበሩና ጅራፍ እያጮኹ: የሙልሙል ዳቦም እየጋገሩ: ስጦታን በማርከትና በመለዋወጥ: "ቡሄ" ብለው: በዓመት በዓልነት ያከብሩታል።

በተለያዩት ወራት: ከወሩ: በአሥራ ሦስተኛው ቀን: ዓመታዊ በዓል የሚደረግላቸው: ዝክራቸው: በዘመኗ: የክርስትናን ሃይማኖት: በአገርዋ የተቀበለች: የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሕንደኬ: ጥር ፲፫ ቀን: የአእላፍ መላእክት: ኅዳር ፲፫ ቀን: በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. የፋሺስት ጣልያን ጦር: የማኅበረ ሥላሴን ገዳም: ከአየር: በፈንጂ የደበደበበት ሚያዝያ ፲፫ ቀንና በፋሺስት ኢጣልያን ጦር: በሰማዕትነት የተሠየፉት የደብረ ሊባኖስ መነኩሳት: ግንቦት ፲፫ ቀን: ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. የሚውለው ናቸው።

፲፬ኛ: "አባ አረጋዊ":- ጥቅምት ፲፬ ቀን: ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ የኾኑትና በደብረ ዳሞ: ታላቁን ገዳም የመሠረቱት: የአቡነ አረጋዊ (አባ ዘሚካኤል ዘደብረ ዳሞ): የዕረፍታቸው ዓመት በዓል ይከበራል።

በተለያዩት ወራት: ከወሩ: በአሥራ አራተኛው ቀን: ዓመታዊ በዓል የሚደረግላቸው: ዕረፍታቸው: በዚሁ: በጥቅምት ፲፬ ቀን የሚውለው: ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ: አቤሜሌክን ያጠመቀው: ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ: ደግሞም: የአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቃል በመከተል: ትዳሩን: ዙፋኑንና ሀብቱን ትቶ በመመነን: አካሉንም: ለደዌ ሥጋ አሳልፎ በመስጠት: ለእግዚአብሔር እውነትና መንግሥት: እስከሞት የታመነው: ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ናቸው።[፻፶፱]

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ከእነዚህ ጋር፡ ኅዳር ፲፬ ቀን፡ ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. በደርግ የዓመፅና የክህደት ዘመን፡ በኢትዮጵያ በተጀመረው እልቂት የተገደሉት ኢትዮጵያውያን፡ ታኅሣሥ ፲፬ ቀን፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. የኢጣልያ ፋሺስት ጦር፡ በኢትዮጵያ ተከላካይ ሠራዊትና ሰላማዊው ሕዝብ ላይ፡ በተዋጊ ጥያሮቹ አማካይነት፡ የመርዝ ጢስ ማዝነብ የጀመረበት ዕለት፤ ጥር ፲፬ ቀን፡ በ፫፻፴፫ ዓ.ም. ግድም፡ ሥርዓተ ክርስትናን፡ ወደኢትዮጵያ ያስመጣ፡ አንበረም፡ ሊቀ ካህናት ዘአክሱም ዝክር፡ በዓመት በዓልነት ይታሰባሉ።

፲፩ኛ፡ "ሕፃን ቂርቆስ "፡- ጥር ፲፩ ቀን፡ የሦስት ዓመቱ ሕፃን ሰማዕት፡ ቅዱስ ቂርቆስ፡ ከእናቱ ከቅድስት ኢየሉጣ ጋር፡ በሠይፍ ተከልሎ፡ በሰማዕትነት ያረፈበት ዕለት ኾኖ፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል።

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በአሥራ አምስተኛው ቀን፡ የዕረፍታቸው ዓመታዊ በዓል የሚከበርላቸው፡ ሚያዝያ ፲፩ ቀን፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በፋሺስት ኢጣልያን ጦር የተገደሉት፡ የማኅበረ ሥላሴ ሦስት መነኮሳት ሰማዕታት፡ ግንቦት ፲፩ ቀን፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት፡ ፩ዱ፡ ቅዱስ ናትናኤል፥ ሐምሌ ፲፩ ቀን፡ ውዳሴ ማርያምን፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ የደረሰው፡ ቅዱስ ኤፍሬም ሲኾኑ፡ ነሐሴ ፲፩ ቀን፡ የሐዋርያት፡ የፍልሰታ ለማርያም፣ ሱባዔ ፍጻሜም፡ በዓመት በዓልነት ይታሰባል።

፲፮ኛ፡ "ኪዳነ ምሕረት"፡- የካቲት ፲፮ ቀን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ እርሱ፡ በፈጣሪነቱ ተስፋ የሰጠበት፡ ፍጡሩም፡ ለ፭ሺ፭፻ ዓመታት፡ በተስፋ ሲጠብቀው የኖረው፡ የምሕረት ቃል ኪዳኑ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ በእናቲቱና በልጇ ቤዛነት ለተገኘበት ቀን መታሰቢያ ኾኖ፡ የዓመቱ በዓል ይከበራል።

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በአሥራ ስድስተኛው ቀን፡ ዓመታዊ በዓል የሚደረግላቸው፡ መስከረም ፲፮ ቀን፡ ኪዳነ ኖኅ እና የመስቀል ደመራ ሲኾኑ፥ ጥር ፲፮ ቀን፡ የሕፃኑ ሰማዕት የቅዱስ ቂርቆስ እናት፡ የሰማዕቲቱ ቅድስት ኢየሉጣ ዕረፍት፥ ከኹሉም ይልቅ፡ ነሐሴ ፲፮ ቀን፡ በታላቅ ሥርዓት የሚካኼደው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም ትንሣኤ፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል።

፲፯ኛ፡ "ቅዱስ እስጢፋኖስ"፡ ጥቅምት ፲፯ ቀን፡- ለአዲስ ኪዳኑ፡ የመጀመሪያው ሰማዕት የኾነው፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ፡ ገና በሕይወተ ሥጋ ሳለ፡ በቤተ ሕዝቡ ተመርጦና የቤተ ክህነቱ ወገኖች በኾኑት በሐዋርያት፡ "ሊቀ ዲያቆናት" ተብሎ ተሠይሞ፡ ለቤተ ምልክናው፡ የአገልግሎት ሹመት የበቃበት፥ ኋላም፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥትና እውነት፡ በድፍረትና በይፋ ባሰማው፡ የሰማዕትነት ቃሉ የተነሣ፡ ገዳዮቹ አይሁድ፡ ሲወግሩት ሳለ፡ *"ተንበርክኮ፡ 'ጌታ ሆይ፥ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው!' ብሎ፡ በታላቅ ድምፅ ሲጮህና 'ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ነፍሴን ተቀበል!' ብሎ ሲጠራ፡ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ፡ ወደሰማይ ትኵር ብሎ ይመለከት ነበር፤ የእግዚአብሔርን ክብር፥ ኢየሱስንም፡ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና፡- 'እነሆ፡ ሰማያት ተከፍተው፥ የሰው ልጅም፡ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ!'"* ባለ ጊዜ፡ በሕይወተ ነፍስ የተሰጠውን ሰማያዊ ሹመት[፲፰] የተቀዳጀበት መታሰቢያ፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል።

## ምዕራፍ ፮፤ በዓል።
### ስለበዓላት ዝርዝር ሓተታዋ የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ።
#### የዓመቱ በዓላት።

---

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በአሥራ ሰባተኛው ቀን፡ ዓመታዊ በዓል የሚደረግላቸው፡ መስከረም ፲፯ ቀን፡ በታላቅ ሥርዓት የሚከበረው፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል፡ በንግሥት ዕሌኒ ሃይማኖታዊ ቅንዓት፡ በኢየሩሳሌም ከተቀበረበት ቦታ፡ በምሕላ ጸሎት፡ ተቆፍሮ የተገኘበትና የወጣበት ዕለት፡ ጥቅምት ፲፯ ቀን፡ የተዋሕዶ ሃይማኖት ተጋዳዩ፡ የቅዱስ ዲዮስቆሮስ ዕረፍት፡ ኅዳር ፲፯ ቀን፡ በሥላሴ፡ በመድኃኔ ዓለም፡ በድንግል ማርያም፡ በመላእክት፡ በጻድቃንና ሰማዕታት አብያተ ክርስቲያን የተከበበችውና የተመላችው፡ የአዲስ አበባ መናገሻ ከተማ፡ በ፲፰፻፹፱ ዓ.ም. የተቈረቈረችበት መታሰቢያ፡ እንዲሁም፡ የዕረፍታቸው ዝክር፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት፡ ፩ዱ የኾነው፡ የቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ፡ ሚያዝያ ፲፯ ቀን፡ ከመካከለኛው ምሥራቅ፡ በሃይማኖት ስደት፡ ወደኢትዮጵያ ከገቡት፡ ከዘጠኙ ቅዱሳን፡ የአንዱ፡ የአባ ገሪማ፡ ሰኔ ፲፯ ቀን፡ በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የነበረው፡ የእጨጌ እንድርያስም፡ ሐምሌ ፲፯ ቀን ሲኾኑ፡ ነቢዩ ዮናስ፡ ከዓሣ አንበሪው ሆድ ወጥቶ፡ የነነዌን ባሕር ዳር ከተረገጠበት፡ ከዚኹው ዕለት ጋር፡ በዓመት በዓልነት ይከበራሉ።

፲፯ኛ፡ "ጦብያ"፡ "ኢትዮጵያ"፡ ሐምሌ ፲፯ ቀን፡- የኢትዮጵያውያኑ፡ ጦብያና ጦቢት (ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት)፡ የዕረፍታቸው መታሰቢያ ዕለት የሚውልበት በመኾኑ፡ በዓመት በዓልነት ይከበራሉ።

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በአሥራ ስምንተኛው ቀን፡ ስለዕረፍታቸው ዓመታዊ በዓል የሚደረግላቸው፡ መስከረም ፲፰ ቀን፡ ስለቅዳሜ፡ ቀዳሚ ሰንበትንነት እስከመጨረሻው የተከራከረ፡ ኢትዮጵያዊው አባ ኤዎስጣቴዎስ፡ ዘደብረ ቢዘን፡ ኅዳር ፲፰ ቀን፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት፡ ፩ዱ የኾነው፡ ቅዱስ ፊልጶስ፡ ታኅሣሥ ፲፰፡ በአኮስሙ ሊቀ ካህናት እንበረም ተልኮ፡ በግብፃዊው አባ አትናቴዎስ፡ ጵጵስናን፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሾመው፡ ኢትዮጵያዊው አባ ሰላማ፡ የካቲት ፲፰ ቀን፡ የግራኝ አሕመድን የእስልምና ጦርነት፡ ከ፲፭፻፲፱ ዓ.ም. ጀምሮ በተከታታይ ሲከላከል፡ በሰማዕትነት የተሠዋው፡ የኢትዮጵያ ጦር ጠቅላይ አዝማች ደገልሃ ሲኾኑ፥ መንፈስ ቅዱስ፡ በሐዋርያት ላይ የወረደበት፡ የመጀመሪያው በዓለ ጰራቅሊጦስ የዋለበት፡ ግንቦት ፲፰ ቀን፡ ደግሞም፡ የመጀመሪያው የኢየሩሳሌም ኤጲስቆጶስ ኾኖ የተሾመው፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም፡ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ያረፈበት፡ ሐምሌ ፲፰ ቀን፡ እንዲሁም፡ የባሌው ገዢና የኢትዮጵያ ጦር አዛዥ፡ አዝማች አዳሉ (አዳል ሰገድ)፡ የግራኝ አሕመድን የእስልምና ጦርነት እንቅስቃሴ፡ በባሌ ግንባር፡ በጀግንነት ሲከላከል ቆይቶ፡ በመጨረሻ፡ ለቤተሰቦቹና ለሠራዊቱ፡ "ዛሬ፡ እስከዕለተ ምጽአት ድረስ የሚነገር ሥራ የምንሠራበት፡ ታላቅ የተከበረ ቀን ነውና፡ የክት ልብሶቻችሁን ልበሱ! ጌጣችሁንም አጊጡ!" የሚል የኑዛዜ ቃልን አውጆ፡ በ፲፭፻፳፩ ዓ.ም. በሰማዕትነት የተሠዋበት፡ ነሐሴ ፲፰ ቀን፡ በዓመት በዓልነት ይታሰቡበታል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

፲፱ኛ፡ "ቅዱስ ገብርኤል"፡ ታኅሣሥ ፲፱ ቀን፡ "መልአከ ብሥራት"፡ ወይም፡ "ዜናዊ ፍሡሓ ገጽ" የሚባለውና ለካህኑ ዘካርያስ፡ ሚስቱ ኤልሳቤጥ፡ መጥምቁ ዮሓንስን የፀነሰች መኾኗን፡ *"እኔ፡ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ! ይህችንም የምሥራች እነግርህ ዘንድ ተልኬ መጣሁ!"* ሲል፡ በቤተ መቅደስ ያበሠረው፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ "ሠለስቱ ደቂቅ" ወይም፡ በስማቸው፡ አናንያ፡ አዛርያና ሚሳኤል የተባሉትንና ተማርከው፡ በባቢሎን ይኖሩ የነበሩትን፡ የኪዳን አሪት ሃይማኖታውያን አርበኞች፡ ከናቡከደነፆር የባቢሎን እሳት ያዳነበት[፳፮] መታሰቢያ ዕለት ኾኖ፡ በዓመት በዓልነት ይከበርበታል፡፡

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በአሥራ ዘጠነኛው ቀን፡ ዓመታዊው በዓላቸው የሚከበርላቸው፡ ጥገኝነትን ፍለጋ፡ ከእስልምና መሥራቹ፡ ከመሓመድ፡ በስደት ወደኢትዮጵያ የተላኩትን፡ የመጀመሪያዎቹን እስላሞች ስደተኞች፡ በአክሱም ተቀብሎና አስተናግዶ የሸኛቸው፡ ጥቅምት ፲፱ ቀን የሚውለው፡ የአጼ አርማሕ ዕረፍትና ግንቦት ፲፱ ቀን የሚውለው፡ የኢትዮጵያዊው አቡነ ዓቢየ እግዚእ ዕረፍት ሲኾኑ፡ ሐምሌ ፲፱ ቀን የሚውለው፡ በሊቀ መላእክት፡ ቅዱስ ገብርኤል የተልእኮ ዕርፈ መስቀልና ተራዳኢነት፡ ከዲዮቅልጥያኖስ የሮማ እሳት የዳኑት፡ የአዲስ ኪዳኑ ሰማዕታት፡ የሦስት ዓመቱ ሕፃን፡ የቅዱስ ቂርቆስና የእናቱ ቅድስት ኢየሉጣ ዓመታዊ ዝክር ይከበራል፡፡

፳ኛ፡ "ሕንፀታ፡ ዘቤተ ክርስቲያን"፡ ሰኔ ፳ ቀን፡- የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፡ በአንጾኪያ የተሠራችበትን ዕለት ለማስታወስ፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል፡፡

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በሃያኛው ዕለት፡ ዓመታዊ የዕረፍት በዓላቸው የሚከበርላቸው፡ ግንቦት ፳ ቀን የሚውለው፡ ወደናግራን (የመን) ግዛቱ፡ በመርከብ ዘምቶ፡ በዚያ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ የተነሣባቸውን አይሁዳዊ ጠላት፡ ድል ያደረገውና በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ያረፈው ቅዱስ አፄ ካሌብ እና ሰኔ ፳ ቀን የሚውለው፡ ነቢዩ ኤልሳዕ ናቸው፡፡

፳፩ኛ፡ "ቅድስት ማርያም"፡ ጥር ፳፩ ቀን፡- የአምላክ እናት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከዚህ ዓለም ሕይወተ ሥጋ ያረፈችበት ዕለት መታሰቢያ በመኾኑ፡ በታላቅ ክብር፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል፡፡

በተለያዩት ወራት፥ ከወሩ፡ በሃያ አንደኛው ዕለት የሚውሉት፡ በቅድሚያ፡ የቅድስት ድንግል ማርያም የዕርገቷ፥ ከዚያም፡ ግማደ መስቀሉ፡ በግሼን ማርያም የሚገኘው፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ቤዛ ኾኖ የተሠዋበት የመስቀሉ ነገር የሚነገርባት፥ እንዲሁም፡ በዓመቱ ውስጥ ያሉት የእመቤታችን በዓላት ተጠቃልለው ስለሚታሰቡባት፡ "ብዙኃን ማርያም" የተባለችው፡ መስከረም ፳፩ ቀን፥ "ኪዳነ ሙሴ፥ ጽላት ዘሙሴ፥ ታቦተ ጽዮን፥ ታቦተ ሕጉ" የተባለችው የቅድስት ድንግል ማርያም፥ እንዲሁም፡ የማክዳ ንግሥትና የልጇ የቀዳማዊ ምኒልክ መታሰቢያ የሚዘከሩባት፡ ኅዳር ፳፩ ቀን፥ ደግሞም፡ የእጨጌ ዕንባቆም ዕረፍት የሚውልበት፡ ሚያዝያ ፳፩ ቀን የዓመት በዓሎቻቸው ኾነው ይከበሩላቸዋል፡፡

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል።

## ስለበዓላት ዝርዝር ሐተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ።

### የዓመቱ በዓላት።

---

እንዲሁም፡ በ፰፻፸ ዓ.ም. ግድም፡ ከፈላሾች ወገን የተነሣችው፡ "ጉዲት"፡ ወይም፡ "እሳቶ" የምትባለው የይሁዲቷ ዮዲት የጭካኔ አገዛዝ አብቅቶ፡ በ፱፻፲፪ ዓ.ም. የላስታው (ዘአገው) መራሓ ተክለ ሃይማኖት የተተካበት፡ የካቲት ፳፩ ቀን፡ በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. የደርግ ክህደተ እግዚአብሔር አገዛዝ የተገረሰሰበት፡ ግንቦት ፳፩ ቀን፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ ክህደትን፡ አመንዝራነና ዓመፅን የፈጸመውን ትውልድ ሊቀጣ፡ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. የተላከው፡ ግፈኛው ደርግ የተቋቋመበት፡ ሰኔ ፳፩ ቀን፡ በመጨረሻም፡ በ፲፭፻፹፩ ዓ.ም. ሃይማኖታዊው ተጋዳይ፡ አጼ ሡርፀ ድንግል ያረፈበት፡ ሐምሌ ፳፩ ቀን፡ በዓመት በዓልነት ይከበራሉ።

፳፪ኛ፡ "ቅዱስ ዑራኤል"፡ ሐምሌ ፳፪ ቀን፡- ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ሕፃን ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን አዝላና ታቅፋ፡ በስደት፡ ወደምድረ ግብፅ ከመውረዳቸው በፊት፡ ወደትውልድ አገራቸው፡ ወደኢትዮጵያ ገብተው በቆዩባቸው ዓመታት፡ በጉዟቸው ኹሉ ያልተለያቸው፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ዑራኤል የሚታሰብበት ዕለት ኾኖ፡ የዓመቱ በዓል ይከበራል።

በተለይዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በሃያ ኹለተኛው ዕለት፡ ዕረፍታቸው፡ የወንጌላዊው ሉቃስ፡ ጥቅምት ፳፪ ቀን፡ የኢየሱ ወልደ ነዌ፡ ሰኔ ፳፪ ቀን የሚውል ኾኖ፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል።

፳፫ኛ፡ "ቅዱስ ጊዮርጊስ"፡ ሚያዝያ ፳፫ ቀን፡- ስለእውነተኛዪቱ የክርስትና ሃይማኖት፡ እስከመጨረሻው ጸንቶ የተጋደለውና መስክሮ በሰማዕትነት ያረፈው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አርበኛ፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ፡ የሚታሰብበት ዕለት ኾኖ፡ የዓመቱ በዓል ይከበራል።

በተለይዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በሃያ ሦስተኛው ዕለት፡ ከትውልዱ ሐረግ ለሚወለደው ዘሩ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ የዘለዓለማዊት መንግሥቱን ዘውድ የሚያቀዳጀው መኾኑን፡ እግዚአብሔር፡ ቃሉን፡ በመሓላ ያጸናለት፡ ነቢዩ ንጉሥ፡ ቅዱስ ዳዊትና ቃል ኪዳኑ፡ በታኅሣሥ ፳፫ ቀን፡ ኢትዮጵያ፡ በወራሪ ጠላቶቿ ላይ ያላት አስተማማኝ አሸናፊነት፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑን ያረጋገጠው፡ በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም. በኢጣልያ ጦር ላይ፡ በአድዋ ከተማ የተቀዳጀችው ድል፡ በየካቲት ፳፫ ቀን፡ የነቢዩ ዳንኤል ዕረፍት፡ በመጋቢት ፳፫ ቀን፥ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ናት! ለማንም ባዕድ መንግሥት አትገዛም!" በሚለው የኢትዮጵያውያን ሃይማኖታዊ አቋም፡ በመጽናቱ፥ ምድሪቱና ሕዝቡም፡ በዚሁ እንዲጸኑ በማውገዙ፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በፋሺስት ኢጣልያ ጦር፡ በአዲስ አበባ ከተማ ላይ፡ በአደባባይ የተሠዋው፡ የኢትዮጵያዊው ሰማዕት፡ የቅዱሱ አቡነ ጴጥሮስ ዕረፍት፡ ሐምሌ ፳፫ ቀን፥ መዓዛ ቅዳሴን፡ ሰዓታትንና ሌሎችን ጸሎታት፡ በዜማ ጭምር የደረሰው፡ የኢትዮጵያዊው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ዕረፍት፡ በነሐሴ ፳፫ ቀን፡ የሚውል ኾኖ፡ ዓመታዊ በዓላቸው ይከበርላቸዋል።

፳፬ኛ፡ "እጨጌ ተክለ ሃይማኖት"፡ ነሐሴ ፳፬ ቀን፡- በ፲፪ኛው ፻ ዓመት፡ ስለክርስትና ተዋሕዶ ሃይማኖቱ፡ እስከመጨረሻው ጸንቶ የተጋደለውና የኢትዮጵያን ሥርዓተ መንግሥት ያስከበረ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ፡ የእቲሳው እጨጌ ተክለ ሃይማኖትና ኢትዮጵያዊቷ ጻድቅት፡ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ የሚታሰቡበት ዕለት ኾኖ፡ የዓመቱ በዓላቸው፡ ይከበራል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

በተለያዩት ወራት፥ ከወሩ፡ በሃያ አራተኛው ዕለት፡ የኢትዮጵያዊነት ግንድ፡ የኢትዮጵያውያንም "አባት" የኾነው መልከ ጼዴቅና ከፈጣሪው ጋር ያደረገው ቃል ኪዳኑ፡ መስከረም ፳፬.ቀን፥ የሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ዝክርና የንግሥት ዘውዲቱ ዕረፍት፡ መጋቢት ፳፬ ቀን፥ እንዲሁም፡ የነቢዩ ዕንባቆም ዕረፍት፡ ግንቦት ፳፬ ቀን፥ የኢትዮጵያዊው ሙሴ ዕረፍት፡ ሰኔ ፳፬ ቀን፡ እንዲሁም፡ በ፲፭፻፳፫ ዓ.ም. በግራኝ አሕመድ ወረራ፡ የደብረ ሊባኖስ ገዳም መቃጠልና መነኩሳቱ፡ እየራሳቸውን፡ በነበልባሉ ውስጥ እየወረወሩ የተሠዉበት ሐምሌ ፳፬ ቀን፡ የሚውል ኾኖ፡ ዓመታዊ በዓላቸው ይከበርላቸዋል።

፳፫ኛ፡ "ቅድስት ሰሎሜ"፡ ግንቦት ፳፫ ቀን፦ ሕፃኑን ኢየሱስ ክርስቶስንና ቅድስት እናቱን፡ ድንግል ማርያምን፡ በስደታቸው ጊዜ ሳትለያቸው ያገለገለችው፡ ቅድስት ሰሎሜ፡ የዕረፍቷ ዓመታዊ በዓል ይከበራል።

በተለያዩት ወራት፥ ከወሩ፡ በሃያ አምስተኛው ዕለት፡ ነቢዩ ዮናስ፡ በመስከረም ፳፭ ቀን፡ ሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ፡ በኅዳር ፳፭ ቀን፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመድ የኾነው፡ ሐዋርያው ይሁዳ፡ ሰኔ ፳፭ ቀን እና ኢትዮጵያዊው አባ ሕፃን ሞአ፡ ሐምሌ ፳፭ ቀን፡ የዕረፍታቸው ዓመት በዓል ይከበርላቸዋል።

፳፭ኛ፡ "ቅዱስ ዮሴፍ"፡ ሐምሌ ፳፮ ቀን፦ የአምላክን እናት ቅድስት ድንግል ማርያምንና ሕፃን ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በንጽሕና ለመጠበቅና ለማገልገል፡ በታማኝነቱ፡ በእግዚአብሔር ተመርጦ የተጠራው አረጋዊ ጻድቅ፡ ቅዱስ ዮሴፍ፡ የዕረፍቱ መታሰቢያ ኾኖ፡ የዓመቱ በዓል ይከበራል።

በተለያዩት ወራት፥ ከወሩ፡ በሃያ ስድስተኛው ዕለት፡ መስከረም ፳፮ ቀን፡ የጽጌ ወራት መግቢያ፥ ኅዳር ፳፮ ቀን፡ በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም. በናግራን (የመን)፡ በአይሁዳውያን እጅ የተፈጁት ኢትዮጵያውያን ሰማዕታትና ቅዱስ አጼ ካሌብ፡ በአጥቂዎቹ ላይ ድልን ተቀዳጅቶ፡ የቀሩትን ኢትዮጵያውያን ነጻ ያወጣበት መታሰቢያ፥ እንዲሁም፡ የኢየሱስ ሞዐ ኢትዮጵያዊ ዘሐይቅና ግንቦት ፳፮ ቀን፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት፡ ፩ዱ የኾነው፡ የቅዱስ ቶማስ ዕረፍት፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል።

፳፮ኛ፡ "መድኃኔ ዓለም"፡ መጋቢት ፳፯ ቀን፦ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ፍጡሩ ሰው፡ የሕይወተ ሥጋ ምድራዊ ኑሮውንና የሕይወተ ነፍሱን ዘለዓለማዊ ህልውና፡ በራሱ ፍላጎትና ምርጫ፡ በክፋት አገዛዝ፥ በኃጢአት ቀንበርና በሞት ፍዳ ሥር መጣሉን፡ በርኅራኄና በምሕረት ዓይኑ ተመልክቶ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት ከተፀነሰ በኋላ፡ በብሪት ተወልዶ፥ ተጠምቆም፡ ማንነቱን አስመሰከረ።

# ምዕራፍ ፲፮፤ በዓል፡፡

## ስለበዓላት ዝርዝር ሐተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ፡፡

### የዓመቱ በዓላት፡፡

---

ከዚያም፡ ከዲያብሎስ ተፈትኖና ከሰዎች መከራን ተቀብሎ፥ ተሰቅሎና ደሙን አፍስሶ፥ ሙቶና ተቀብሮ፥ በድል አድራጊነት፡ ከሙታን ተለይቶ በመነሣት፥ በክብር በምስጋናም፡ ወደሰማይ በማረግ፡ ሰውን ወደቀደመ ማዕርጉ መለሰው፡፡ ይህ ቀን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ እንዲህ አድርጎ፡ የመጨረሻ ማዳኑንና የቸርነት ድርጊቱን በማሰብ፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል፡፡ በሰሙነ ሕማማት የስቅለት ዓርብ ዕለት፡ የመስቀሉ መከራ፡ በታላቅ መንፈሳዊ ተመስጦና በጽኑ ሥጋዊ ትህርምት ስለሚታሰብ፥ መጋቢት ፳፱ ቀንም፡ የሚውለው፡ በዓቢይ ጾም ወራት በመኾኑ፡ ለአከባበሩ አመቺ ይኾን ዘንድ፡ ዓመታዊ በዓሉ፡ በጥቅምት ፳፱ ቀን እንዲከበር ተደርጓል፡፡

በዚሁ በመጋቢት ፳፱ ቀን፡ የካቶሊክን የሃይማኖት ወረራ አክሽፎ፥ የግራኝ አሕመድንም የጦር ወረራ በሰማዕትነት ሞቱ ድል አድርጎ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱ ኃይል፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን፡ ከመጥፋት ያዳነው፡ የአጼ ገላውዴዎስ ዕረፍት፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል፡፡

በተለያዩት ወራት፥ ከወሩ፡ በሃያ ሰባተኛው ዕለት፡ የዓመት በዓላቸው የሚከበርላቸው፡ ኅዳር ፳፱ ቀን፡ የአባ ሊቃኖስ ኢትዮጵያዊ፡ ዘደብረ ቍንጽልና ታኅሣሥ ፳፱ ቀን፡ የ"ብርሃን ሰገድ" አጼ ኢያሱ ዕረፍት ሲኾኑ፥ ጥር ፳፱ ቀን፡ አካኄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ፡ ሞትን ሳያይ ወደሰማይ ያረገው፡ የቅዱስ ሄኖክ ዝክር፥ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ ኢትዮጵያዊ የኾነውን ሕዝቧን ይዛ የምትኖረውን የኢትዮጵያዊነት አገር ለማጥፋት፡ በ፲፭፻፲፱ ዓ.ም. በጦር ኃይል፡ ለቅጣት የተላከው፡ አሕመድ ግራኝ፡ በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. በድል የተደመሰሰበት፡ የካቲት ፳፱ ቀንና ኢትዮጵያ፡ በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም. ለቅጣት የመጣባትን፡ የፋሺስት ኢጣልያ ወራሪ ጠላት፡ በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. መልሳ በማስወጣት፡ ነጻነቷ፡ ምንጊዜም፡ በአሸናፊነት ተጠብቆ የሚኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ ብቻ መኾኑን በማረጋገጥ፡ ድሏን የምታስታውስበት፡ ሚያዝያ ፳፱ ቀን፥ እንዲሁም፡ አጼ ዓምደ ጽዮን፡ ጋብቻን በሚመለከት በሠራው ኃጢአት፡ ንስሓ እንዲገባ በመገሠፁ፡ በጽኑ መከራ የተሠቃየው፡ የታላቁ ሐዋርያ፡ የደብረ ሊባኖሱ እጨጌ ፊልጶስ ዕረፍት፡ ሐምሌ ፳፱ ቀን፡ በዓመት በዓልነት ይከበራሉ፡፡

፳፱ኛ፡- "አማኑኤል"፡ ጥቅምት ፳፱ ቀን፡- የዓመቱ በዓል ይከበራል፡፡ የሚከበረውም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ "የአምላክ እናት" ከኾነችው፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በመለኮታዊ አካሉና ባሕርዩ፡ ከነፍሷ ነፍስን፥ ከሥጋዋም ሥጋን ነሥቶ፡ ከእርሷ የሰውነት አካልና ባሕርይ ጋር፡ እንዲህ፡ በፍጹም ስለተዋሐደ፡ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው!" ለማለት "አማኑኤል" የተባለበት የትርጓሜ ስም፡ የሚታሰብበት ዕለት በመኾኑ ነው፡፡

እንደዚሁ ኹሉ፡ በመስቀል ላይ ሣለ፡ ነፍሱን ከሥጋው ከለየ በኋላ፡ በነፍሱ፡ ወደሲዖል ወርዶ፡ የነፃነትንና የንስሓን ምሥራች፡ በዚያ ለነበሩት ነፍሳት ባሰማበት ጊዜ፡ በሥጋው ደግሞ፡ ሙስና መቃብርን ያጠፋ ዘንድ፡ ወደመቃብር ወርዶ፡ በምድር ማሕፀን፡ ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት፡ ያደረበት ወቅት ይዘከርበታል፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*በዚህም፡ "እግዚአብሔር አምላክህ እንዳዘዘህ፡ የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ!"* የሚለው፡ ከትእዛዛቱ አንዱ የኾነው ቃል፡ በመቃብር እንኳ ሳይቀር፡ እንዲሁም፡ *"ክፉዎችና ዓመፀኛ፡ አመንዝራም ትውልድ ምልክትን ይሻል፡ ከነቢዩ ከዮናስ በቀር ምልክት አይሰጠውም፡ ዮናስ፡ በዓሣ አንበሪ ሆድ፡ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት እንደነበረ፡ እንዲሁ፡ የሰው ልጅ፡ በምድር ልብ፡ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት ይኖራል።"* የተባለው የጌታ ቃል መፈጸሙ፡ በዚህ ዕለት እየተረጋገጠበት ይታወስበታል።

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በሃያ ስምንተኛው ዕለት፡ የዓመት በዓላቸው የሚከበርላቸው፡ መስከረም ፳፰ ቀን የሚውለው፡ አብርሃም፡ በሃይማኖቱ በተፈተነባቸው ምግባራት ኹሉ ስላለፈ፡ ከፈጣሪው የተሰጠው የግርዛት ቃል ኪዳን ዝክር፡ ኅዳር ፳፰ ቀን የሚውለው፡ ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ የኾነው፡ የአባ ሊቃኖስና መጋቢት ፳፰ ቀን የሚውለው፡ ስለሃይማኖትና ስለፍትሐ ነገሥት ዝግጅት፡ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉባኤን በኒቅያ ያሰባሰበ የንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ዕረፍት፡ እንዲሁም፡ ነሐሴ ፳፰ ቀን የሚውለው፡ የአብርሃም፡ የይስሐቅና የያዕቆብ ዝክር ናቸው።

፳፱ኛ፡ "በዓለ ወልድ"፡ መጋቢት ፳፱ ቀን፦ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጥንተ ትንሣኤው የተፈጸመበት ስለኾነ፡ ዕለቱ፡ በዓመት በዓልነቱ ይዘከራል። ነገር ግን፡ ዕለቱ፡ ምንጊዜም፡ በዓቢይ ጾም ውስጥ ስለሚውልና በሚቀጥለው የሚያዝያ ወር ውስጥ ከሚዘከረው፡ የዓመቱ የትንሣኤ በዓል ጋር አብሮ ስለሚከበር፡ እንደሌሎቹ የዓመት በዓላት፡ የተለመደው ልዩ ሥርዓትና ድምቀት አይታይበትም።

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በሃያ ዘጠነኛው ዕለት፡ የዕረፍታቸው ዓመት በዓል የሚከበርላቸው፡ ኅዳር ፳፱ ቀን የሚውለው፡ የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር፡ የቀሌምንጦስ፡ በ፫፻፲ ዓ.ም. "ተፍጻሜተ ሰማዕት" ተብሎ፡ በሰማዕትነት ያረፈው፡ የመጨረሻው ሰማዕት ጴጥሮስ÷ ሰኔ ፳፱ ቀን የሚውለው፡ በዘመኑ፡ ሰላምና ፍቅር፡ ጽድቅና ትሩፋት የሰፈኑበት ከመኾኑ የተነሣ፡ የራሱን ሀብት ሳይቀር እያወጣ፡ ለሕዝብ የሚያድልና በአንዲት ሚስት የተወሰነ ጻድቅ፡ እንዲያውም፡ "የሕዝብን ገንዘብ አልነካም!" በማለት፡ ለግሉ መተዳደሪያ፡ ሰሌን እየሠራና እየሰፋ፡ በዚያ ሽያጭ ይኖር የነበረው፡ በ፲፰፻፷ ዓ.ም. የነገሠው፡ ቀዳማዊ አጼ ቴዎድሮስ ናቸው።

እንዲሁም፡ አያሌ እስላሞችን እያስተማረ፡ በጥምቀት፡ ወደክርስትና ከመለሰ በኋላ፡ ራሱ፡ "ንዋየ ክርስቶስ" ተብሎ ተጠምቆ፡ በነሐሴ ፳፱ ቀን÷ ፲፱፻፲፪ ዓ. ም. በበጌምድር ክፍለ ሀገር÷ በሊቦ አውራጃ÷ በነገላ ወረዳ ባስሠራው፡ የቅዱሳን ሐዋርያት (አቦ) ቤተ ክርስቲያን ያረፈው፡ "አለቃ ዘካርያስ" የተባለው ቅዱስ ሐዋርያ፡ መታሰቢያው፡ በዚሁ፡ በነሐሴ ፳፱ ቀን፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል። ይህ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ፡ በግራኝ አሕመድ ጊዜ፡ ተገድደው ከሰለሙ ኢትዮጵያውያን ወላጆቹ፡ በ፲፰፻፵፯ ዓ.ም. በላስታ ተወልዶ፡ በምሁርነቱ፡ " ሸህ ዘከርያ ጅብሪል" በሚል ስም ይታወቅ ነበር።

# ምዕራፍ ፯፤ በዓል::

## ስለበዓላት ዝርዝር ሓተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ::

### የዓመቱ በዓላት::

---

አምላኩ ኢትዮጵያ እግዚአብሔር፡ እውነተኛውን ሃይማኖት እንዲገልጽለት፡ ሱባዔ ገብቶ፡ ላቀረበው ጥያቄ፡ መልሱን፡ ከመንፈስ ቅዱስ፡ በራእይ ስላገኘ፡ ቍርዓኑን፡ በኦሪትና በነቢያት፡ በወንጌልም ቃል መሠረት እየተረጐመ፡ ለእስላም ወገኖቹ ኹሉ ማስተማር ጀመረ፡ ከዚህ የተነሣ፡ በአገር ውስጥ ባሉ፡ የእስልምና መሪዎች እየተከሰሰና እየረታ፡ ከክሱ ኹሉ ነጻ በመውጣቱ፡ በመጨረሻ፡ ከሳሾቹ፡ ለአጼ ምኒልክ "ይግባኝ!" ብለው፡ ከውጭ አገር ያስመጧቸውን ምሁራኖቻቸውን ሳይቀር፡ እዙፋን ችሎት እየያዙ ቀርበው፡ እነዚህንም ኹሉ፡ በተከታታይ፡ ሦስት ጊዜያት፡ በጉባኤ ስለረታቸው፡ ይህን ትምህርቱን፡ በመላ ኢትዮጵያ፡ በነጻነት እየተዘዋወረ ለማስተማር የሚያስችለውን የአዋጅ ጽሑፍ፡ ከመንግሥት አግኝቶ፡ ኢትዮጵያዊና ሓዋርያዊ ተልእኮውን ለመፈጸም በቅቷል::

፴ኛ፡ "መልከ ጼዴቅ"፡ ወይም፡ "አመ ሠላሳ"፡ ነሐሴ ፴ ቀን፦ ሕይወት ያለው ፍጥረት ኹሉ፡ በሰው ዘር የክፋት ጠንቅ፡ በጥፋት ውኃ፡ ከተደመሰሰ በኋላ፡ ያው የሰው ዘር፡ በአንድ ቤተሰብ የሃይማኖት ጽናትና የጽድቅ ምግባር ተርፎ፡ አዲሱን መልካም ሕይወት ለመቀጠል ያስቻለውን፡ ቅዱሱን ኪዳን፡ ከኖኅ የተረከበውና አብርሃምን የባረከው፡ የኢትዮጵያዊነት አብነት፡ ድልድይና ባለአደራ ለመኾን የበቃው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስም ምሳሌው፡ ጥላውና አርአያው ኾኖ የተገለጠው፡ "የኢትዮጵያውያን አባት፡ የልዑል እግዚአብሔር ካህንና የሳሌም ንጉሥ" የተባለው፡ መልከ ጼዴቅ የሚዘከርበት ኾኖ፡ በዓመት በዓልነት ይከበራል::

በተለያዩት ወራት፡ ከወሩ፡ በሠላሳኛው ዕለት፡ ዩዕረፍታቸው ዓመት በዓል የሚከበርላቸው፡ ሚያዝያ ፴ ቀን የሚውለው፡ የወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ፥ ኅዳር ፴ ቀን የሚውለው፡ በዘመኑ፡ የቅዱስ ያሬድ፡ የሥነ ትምህርትና የዜማ ሙያው፥ የ፱ቱ ቅዱሳን ዜና የገነነበትና የደብረ ዳሞ ገዳም ቤተ ክርስቲያን የታነፀበት፡ የአጼ ገብረ መስቀል ዕረፍት ሲኾኑ፥ ሰኔ ፴ ቀን የሚውለው፡ በ፲፭፻፳፭ ዓ.ም. በግራኝ አሕመድ ወራሪ ጦር የተካኼደው፡ የላስታ ቅዱስ ላልይበላል (ላሊበላ) አብያተ ክርስቲያን መበዝበዝ ዝክርና ሓምሌ ፴ ቀን የሚውለው፡ "ማርያም ክብራ" የተባለችው፡ የአጼ ናዖድ ሚስትና የአጼ ልብነ ድንግል እናት፡ የእቴጌ ናዖድ ሞገሳ ዕረፍት፡ በዓመት በዓልነት ይታሰብበታል::

በዚህ፡ የዕለታቱና የየሳምንቱ፥ የየወሩና የዓመቱ በዓላት፡ የተጨመቀ ዝርዝር ያበቃል::

## የጌታ የልደት በዓል፡ መስከረም ፩ ቀን ስለመኾኑ::

*ጥያቄ:- ወደሌላ ርእስ ከመኼድህ በፊት፡ እዚህ ላይ እንድታስረዳን የምንፈልገው፡ አንድ ዓቢይ ጉዳይ አለ፤ ይኸውም፡ "የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል፡ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን ይውላል!" ተብሎ፡ እስከዛሬ፡ በዚህ መልክ ሲከበር ቆይቷል፤ አሁን፡ ይኸው፡ የአምላካችን የልደት ቀን፡ "መስከረም ፩ ቀን ሊኾን ይገባል!" ስለሚያሰኘው ምክንያት፡ ጠለቅና ሰፋ አድርገህ ብትገልጽልን?*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

መልስ:- ኢትዮጵያውያን፡ “ዓመተ ምሕረት ገባ! ተጀመረ!” ብለው፡ በታላቅ ደስታና ምስጋና፡ የሚያከብሩት ዋናው የዐውደ ዓመት በዓላቸው፡ እስከዛሬ፡ እስከ፲፱፻፺፰ ዓመተ ምሕረት ድረስ፡ ይኸው፡ መስከረም ፩ ቀን መኾኑ፥ ዘመኑንም፡ ዓመተ ፍዳ ተወግዶ፡ ዓመተ ምሕረት መተካቱን ለማጠየቅ፡ “ዓመተ ምሕረት” አሰኝቶ፥ ዓመቱን፡ ፩ ብሎ እንዲጀመር ያደረገው፡ ይኸው የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት መኾኑ፡ ሊታበል የማይቻልና ሕያው ኾኖ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እስከዛሬ ድረስ፡ በገሃድ ሲፈጸም የኖረ፥ ዛሬም እየተፈጸመ ያለ፡ ቋሚ እውነታ ነው።

የቤተ ክህነት ሊቆቻችንም፡ በረቡዕ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ማብቂያ ላይ፡ *“አድኃነ ነፍሳቲነ በምጽአቱ ቅዱስ”*፡ ማለትም፡ እግዚአብሔር፡ *“በልዩ አመጣጡ መጥቶ አዳነን”* ለሚለው ቃል፡ *“የቀደመው የረድዔት፡ ማለትም፡* በመንፈስ፡ *ነው፤ የዛሬው የኩነት፡ ማለትም፡* ራሱ፡ ሰው ኾኖ *ነውና!”* የሚል አጭር ሐተታን ከሰጡ በኋላ፡ በቀጠለው አንድምታቸው፡ *“በጽኑ ቀጠሮው መጥቶ አዳነን፤ ‘በጽኑ ቀጠሮው አለ!’ አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም፡”* ቀጠሮውን፡ ማለትም፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን ተፀንሶ፡ ከእርሷ የተወለደባትን ጊዜ፡ *“ለአንዲት ሰዓት እንኳ አላሳለፈምና!” ብለው የምሥጢር* ፍቻቸውን ያቆማሉ።

በዚህ ቃልና እስካሁን ጸንቶ በቀጠለው፡ በኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት፥ እንዲሁም፡ “ጽኑ ቀጠሮውን፡ ለአንዲት ሰዓት እንኳ አላሳለፈም” በሚለው፡ በውዳሴ ማርያሙ ትርጓሜ መሠረት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም የተወለደባት ጊዜ፡ በጳጉሜ ፭ ቀን፥ ፭ሺ፭፻ ዓመተ ዓለም፡ ከሌሊቱ ልክ ፮ ሰዓት ሞልቶ፡ አንዲት ካልዕት ለማትሞላ አፍታ፡ ጥቂት እልፍ ብላ በነበረችው ቅጽበት ውስጥ መኾኑ ነው። መስከረም ፩ ቀን፥ ፩ ዓመተ ምሕረት ተብሎ፡ የዓመተ ምሕረት ዘመን አቆጣጠር የጀመረውም፡ ከዚያች፡ የዓመተ ኩነኔ፡ ወይም የዓመተ ፍዳ ማብቂያ ከኾነችው፡ ከጳጉሜዋ ፭ ቀን፥ ፭ሺ፭፻ ዓመተ ዓለም፡ ከሌሊቱ ፮ ሰዓት በኋላ ከነበረችው ቅጽበት ጀምሮ ኾኗል!

*ጥያቄ:- “ለአንዲት ሰዓት እንኳ አላሳለፋትም” የተባለችው ጊዜ፡ የትኛዋ ናት? መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል፡ “ትጸንሻለሽ” ብሎ ድንግል ማርያምን አብሥሩዋት፥ እርሷም፡ “እንደቃልህ ይኹንልኝ” ብላ ብሥራቱን እንደተቀበለች፡ ወዲያው፡ በዚያች አፍታ፡ ጽንሰቱ የተፈጸመባት ናት? ወይስ የተወለደባት?*

መልስ:- “ለአንዲት ሰዓት እንኳ አላሳለፋትም” የተባለችው ጊዜ፡ ከጽንሰቱ ይልቅ፡ ልደቱን ይመለከታል ማለቱ ትክክል ይኾናል፤ ምክንያቱም፡ ብሥራቱ፡ የእመቤታችንን፡ ለአምላክ እናትነት መመረጥ ለማስታወቅ፡ በመልአኩና በእርሷ መካከል፡ በምሥጢር የተካኼደ ንግግር ሲኾን፡ ልደቱ ግን፡ የሰማይ መላእክትና የምድር ሠራዊት በይፋ የተነጋገሩበትና *“ለዓለሙ ኹሉ የሚኾን ታላቅ የደስታ ምሥራችን”* የተሳተፉበት በዓል ስለኾነ ነው።

# ምዕራፍ ፯፡ በዓል።
## የጌታ የልደት በዓል፡ መስከረም ፩ ቀን ስለመኾኑ።

*ይህም፡ "በዚያም ምድር፡ መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ፡ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ። እነሆም የእግዚአብሔር መልአክ፡ ወደእነርሱ ቀረበ! የእግዚአብሔር ክብርም በዙሪያቸው አበራ! ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ! መልአኩም እንዲህ አላቸው፡- 'እነሆ፥ ለእናንተና ለዓለሙ ኹሉ የሚኾን፡ ታላቅ የደስታ ምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ! ዛሬ በዳዊት ከተማ፡ መድኀኒት፡ እርሱም ቡሩክ ክርስቶስ፡ ጌታ የኾነ፡ ተወልዶላችኋልና!'* በሚለው የመልአኩ ቃል ተረጋገጠ ይታወቃል።[፻፳፫]

*ጥያቄ፡- ለዓመተ ምሕረት የጊዜ አቈጣጠራችን፡ መሠረቱና መጀመሪያው፥ ለዓመተ ፍዳም፡ ድምድማቱና መጨረሻው፡ "ቃል፡ ሥጋ ኾነ!" ማለትም፡ "አምላክ ሰው ኾነ!" የተባለበት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን ከኾነ፡ የተወለደባት ቀን ደግሞ፡ በጳጉሜ ፭ ቀን፥ ፭ሺ፭፻ ዓመተ ዓለም፡ ከሌሊቱ ልክ ፮ ሰዓት ላይ ከኾነ፥ እለዚያ፡ መቼም ሳይወለድ፡ "ዓመተ ምሕረት ገባ! ወይም ተጀመረ!" ማለት ስለማይቻል፥ በአጠቃላይ፡ እውነታው፡ ይህ ሲኾን ሳለ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ተወልዶበታል! እርሱም፡ በየዓመቱ ታኅሣሥ ፳፱፥ በየአራት ዓመቱ ደግሞ፡ በታኅሣሥ ፳፰ ቀን ይውላል!" ተብለን እንድናከብረው የተደረግነው፡ ይህ፡ የገና ወይም የልደት በዓል፡ ታዲያ ከየት መጣ? "በጽኑ ቀጠሮው፡ አንዲት ሰዓት እንኳ ሳያሳልፍ፡ ልክ፡ የ፭ሺ፭፻ው ዓመተ ፍዳ ሲያበቃ ተወለደ!" ብለን እየወጅን፡ እንዴት፡ ከመስከረም ፩ ቀን በኋላ፡ አራት ወሮችን ቈይተንና አሳልፈን፡ "በታኅሣሥ ፳፰ ወይም ፳፱ ቀን ተወለደ!" ብለን፡ እንደገና በዓሉን እናከብራለን?*

**መልስ፡-** ይህን ግዙፍ ስሕተት ያደረሰው ማን መኾኑን ለማወቅ፡ እምብዛም አያዳግትም። ግብፃውያን፡ በዚህ ረገድ ብቻ ሳይኾን፡ የልደቱን ቀን፡ በየአራት ዓመቱ፡ በዘመነ ዮሓንስ፡ ከታኅሣሥ ፳፱፡ ወደኋላ፡ ወደታኅሣሥ ፳፰ ቀን "ይመለስ" ብለው በፈጠሩብን ውዝግብ የተነሣ፡ ችግሩ እየጨመረ እንዲኼድ ተደርጓል፤ ይህን ድርጊት "ትክክል ነው" ብለው አምነው የተቀበሉ ወገኖች ካሉ፡ "ታዲያ ለምንድነው፡ በዚያው ዓመት ውስጥ ተቀምረው የተወሰኑትን፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ የጌታንና የእመቤታችንን በዓላት፡ በየአራት ዓመቱ፡ ወደኋላ፡ በአንድ ቀን እንዲቀነሱ ያላደረጉት?" ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል። ከኹሉም ይልቅ፡ "የጌታ የልደት በዓል ቀን፡ እንዲህ፡ በአንድ ቀን ተቀንሶ፡ ከታኅሣሥ ፳፱፡ ወደኋላ፡ ወደታኅሣሥ ፳፰ ቀን ከተመለሰ እኮ፡ ሌሎቹ ኹሉ፡ የዓመቱ በዓላትና አጽዋማት፡ እንዲሁ፡ በአንድ ቀን፡ በግድ፡ ወደኋላ መሽጋሸግ አለባቸው።

ስለዚህ፡ ከዚህ ኹሉ የማያስፈልግ ውዝግብና ችግር መዳን የሚቻለው፡ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው፡ አንድ ጊዜ ብቻ ስለኾነ፥ ተወልዶም፡ ተልእኮውን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ስለፈጸመ፥ በየዓመቱ የሚከበረው፡ የልደት በዓሉም፡ በመታሰቢያነትና ለመታሰቢያነት ብቻ በመኾኑ፡ በየአራት ዓመቱ፡ አንድ ቀን እየተቀነሰ እንዲከበር ማድረጉን ትተን፡ በዚያው በታኅሣሥ ፳፱ ቀን እንጽና" ማለት ይችሉ ነበር።

ነገር ግን፡ ይህ ሳይኾን፡ እስካሁን ተኑርዋል። ስለዚህ፡ ለዚህ ቀላል ችግር፡ ይህ ውሳኔ፡ ጊዜያዊ መፍትሔ ሲኾን፡ ለዘለቄታው የሚኾነው መፍትሔ ግን፡ የጌታ የልደቱ በዓል፡ ወደጥንታዊው እውነተኛ ዕለት ተመልሶ፡ በመስከረም ፩ ቀን እንዲውል ማድረግ ብቻ ነው።

ታዲያ፡ የቤተ ክህነት ሊቆቻችን፡ "የልደት በዓል፡ በየአራት ዓመቱ፡ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን ሊውል ይገባዋል" በሚለው፡ አወዛጋቢ ውሳኔ ምክንያት፡ የተፈጠረውን፡ ይህን ትንሹንና ቀላሉን ጉዳይ፡ ቀደም ብሎ በተገለጸው መልክ፡ ለባዕዳኑ ግብፃውያን አለቆቻቸው፡ በትክክል አስረድተው መቋቋም ሲችሉ፡ ይህን ማድረግ ያቃታቸው ከኾነ፡ ይህን ትልቁን፡ የዘመን መለወጫ የኾነው የልደቱ ቀን፡ እንደጥንቱ፡ "እንደኢትዮጵያኑ ሥርዓት፡ በመስከረም ፩ ቀን መጽናት አለበት" ብለው፡ እንዴት ሊያስረዱና ሊያስተካክሉ ይችላሉ? ሳይችሉ ቀርተዋል።

እንግዲህ፡ እግዚአብሔር የሠራውንና ኢትዮጵያውያን፡ በቃል ኪዳን ታማኝነታቸው ጠብቀው ያኖሩትን ሥርዓት ለማናጋት መሞከር፡ ውጤቱ ይህን የመሰለውን ዝብርቅርቅ ኹኔታን ማስከተል ነው፤ ስለዚህ ነው፡ ይህ ችግር የተፈጠረው። ይህንም ችግር የፈጠሩት፡ የወዳጅ ጠላቶቻችን፡ ግብፃውያን መኾናቸው፡ ስለባሕረ ሓሳቡ፡ በዋቢነት የሚጠቀሰው ድሜጥሮስ፡ ራሱ ያስረዳል። ይኹን እንጂ፡ እርሱም ቢኾን፡ በተለይ፡ የጌታን የልደት ቀን በሚመለከት፡ በተፈጸመው ስሕተት፡ ራሱን፡ ከተጠያቂነት፡ ነጻ ማድረጉን፡ ጥቂት ቆይተን እንገነዘባለን።

ዐውደ ዓመት በኾነው፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ የእግዚአብሔር ሥነ ፍጥረት፡ ተዘርዝሮና ተጠቃልሎ የሚነገርበት፥ ከራብዒትና ከኬክሮስ ተነሥቶ፡ እስከዓመትና ዘመናት የሚደርሰው የጊዜ አቆጣጠር፡ በሒሳብ ተሰልቶ የሚወጣበት፡ ባሕረ ሓሳብ የሚባለው ሥነ እውቀት በይፋ ይቀርባል። በዚህ ዕለት፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚደረግ፡ የካህናትና የምእመናን ጉባዔ ላይ፡ በየዓመቱ፡ ምድር ከምታበቅለው፡ የአትክልት፥ የአዝርእትና የዕፀዋት ዓይነት መካከል፡ ከፈጣሪ ለተገኘው በረከትና ለእርሱ ለሚቀርበው ምስጋና፡ ምልክት ይኾን ዘንድ፡ ስንዴና የወይን ፍሬ (ዘቢብ)፡ ጧፍና ዕጣን፥ በመሶበ ወርቅ ኾኖ፥ የእንቍጣጣሽ አበባ ጉንጉን ጭምር፡ ተዘጋጅቶ በሚታይበት፡ የቤተ ክህነት ሊቃውንት፡ የዚያን አዲስ ዓመት፡ የበዓላትና የአጽዋማት ውሳኔ፡ በዚሁ ባሕረ ሓሳብ አማካይነት፡ በአዋጅ ያሰሙበታል።

ለዚህ ባሕረ ሓሳብ ቀመራ፡ መሠረትና መነሻ ኾኖ፡ የዘመኑ፡ የሰዓትና የዕለት፥ የመዓልትና የሌሊት፥ የወርና የዓመት አቆጣጠር፥ እንዲሁም፡ የአጽዋማትና የበዓላት ቀኖች አመዳደብ የሚወሰንበት፡ የመጀመሪያው መግቢያ፡ "መስከረም ፩ ቀን" ነው።

## ምዕራፍ ፮፡ በዓል።
## የጌታ የልደት በዓል፡ መስከረም ፩ ቀን ስለመኾኑ።

---

የየአንዳንዱ ቀን፡ የመዓልትና የሌሊት ልክ ታውቆ የሚወጣበት መቀመሪያ፡ "አበቅቴ" የሚባለው መሥፈሪያ፡ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትንም ዕለት የሚወስነው፡ "መጥቅዕ" የሚባለው መቀመሪያ፡ ኹለቱም መሥፈሪያዎች፡ በየመልካቸው ተሰልተው የሚወጡት፡ ይህንኑ፡ "መስከረም ፩ ቀን" መደብ አድርገው ነው። ከዚህ በኋላ ነው፡ የቀኑና የሌሊቱ ቁጥር፡ እንዲሁም፡ የዓመቱ የጾም መግቢያዎችና ማብቂያዎች ዕለታት የሚታወቁት።

በዚህ አዋጅ ላይ፡ ከሰባቱ አጽዋማት መካከል፡ የገና ጾም የሚባለው፡ ጾመ ነቢያትና ከእርሱ ጋር የተያያዘው፡ "ጾመ ገሃድ" የሚባለው፡ የጥምቀት ዋዜማ ጾም፡ እንዲሁም፡ ጾመ ፍልሰታ፡ ደግሞ፡ ከዓበይት በዓላት መካከል፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የጽንሰቱና የልደቱ፡ የጥምቀቱም ዕለታት ብቻ ተለይተው ይቀራሉ።

**የጌታ ልደት፡ ከነአጽዋማቱና በዓላቱ፡ ከቀመሩ አዋጅ ተለይቶ ስለመኖሩ።**

ጥያቄ:- *እነዚህ የጠቀስሃቸው አጽዋማትና በዓላት ብቻ፡ ከሌሎቹ ተለይተው የሚቀሩት፡ ከቶ ለምንድር ነው? ምክንያቱን ገልጸህ ብታስረዳን!?*

መልስ:- በባሕረ ሓሳቡ ተቀምረው ወጥተው የሚታወጁት አጽዋማት፡ ጾመ ኢትዮጵያ (ጾመ ነነዌ)፡ ዓቢይ ጾም፡ ጾመ ሐዋርያት (የሰኔ ጾም)፡ ጾመ ድኅነት (ረቡዕና ዓርብ) ሲኾኑ፡ የጌታችን በዓላት ደግሞ፡ ደብረ ዘይት፡ ሆሣዕና፥ ስቅለት፥ ትንሣኤ፡ ዕርገትና በዓለ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። ዳሩ ግን፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የትስብእቱ (የጽንሰቱ) እና የልደቱ፡ የጥምቀቱም በዓላት ቀኖች፥ ከእነርሱም ጋር የተያያዘው፡ የነቢያት ጾምና ጾመ ገሃድ፡ በዚህ በባሕረ ሓሳቡ ቅመራ ውስጥ ሊገቡ ያልቻሉት፡ ለምንድር ነው? ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱ፡ አጭር ነው፥ ይኸውም፡ በቅድሚያ፡ "የጌታ፡ የልደቱ ቀን፡ ከመስከረም ፩ ቀን ተነሥቶ፡ ወደሌላ ዕለት ሊዛወር የማይቻል በመኾኑ ነው፥ ቀጥሎም፡ እነዚህ፡ ጥቂት አጽዋማትና በዓላት፡ ከዚህ የተነሣ፡ በባሕረ ሓሳቡ ውስጥ እንደተያዙት፡ እንደሌሎቹ አጽዋማትና በዓላት፡ መግቢያቸውና ማብቂያቸው፥ በዓላቱም፡ የሚውሉባቸው ቀናት፡ ወደላይ የማይወጡና ወደታች የማይወርዱ፡ ማለትም፡ ለምንጊዜውም፡ ሳይንቀሳቀሱ፡ በቋሚነት ተወስነው የተመደቡ በመኾናቸው ነው!" የሚል ይኾናል።

ወይስ፡ ይህን የመሰለው ቀውስ የተፈጠረው፡ ይኸው፡ የጌታ፡ የልደቱ ቀን፡ ከእውነተኛው፡ ከመስከረም ፩ ቀን ተነሥቶ፡ አላገባብ፡ ወደ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን በመቀየሩ ይኾን? ለዚህ ጥያቄ፡ መልስ ለመስጠት፡ በኢትዮጵያውያን ባሕረ ሓሳብ ውስጥ፡ ስማቸው የሚጠቀሰውን፡ ግብፃውያኑን ድሜጥሮስንና አቡሻኽርን፡ እንደተለመደው፡ እንደዋቢ አድርጌ ላቀርባቸው ያዳግተኛል።

ምክንያቱም፡ የጌታን፡ የጽንሰቱንና የልደቱን የበዓላት ቀኖች፡ ከእነርሱ ጋር የተያያዙትንም የአጽዋማት ቀኖች፡ ማለትም፡ ጾመ ነቢያትንና ጾመ ገሃድን፡ እንዲሁም፡ ጾመ ፍልሰታን ጨምረው፡ ከቀመራቸው ውጪ ስላደረጓቸው ነው። እነርሱም ቢኾኑ፡ "እየራሳቸውን፡ ከስሕተቱ ነጻ ያደረጉ ይመስላል!" ብዬ፡ ከዚህ በማስቀደም የጠቆምሁት፡ ከዚህ የተነሣ መኾኑን፡ እንድገና ላስገነዝባችሁ እወድዳለሁ።

ታዲያ፡ ይኼ ኹሉ ምንን ያስረዳል? ወደምንስ ያመለክታል? ለራሱ፡ ለኢትዮጵያውያኑ ባሕረ ሐሳብና ለአቆጣጠሩ፡ እንደመስከረሙ ወር፡ መሠረቱ እና መነሻው እርሱ፡ የጌታ፡ የልደቱ ቀን በመኾኑ አይደለምን? መሠረት ከተነዋወጸ ደግሞ፡ በእርሱ ላይ የቆመው ኹሉ ይፈርሳል።

ስለዚህ፡ መሠረቱ፡ የግብፅ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ፡ በባዕዳኑ ዘንድ ሲፋለስ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እስከዛሬ አልተነዋወጸም ማለት ነው። አዎን! እርሱ፡ ራሱ፡ መሠረቱ፡ ባለቤቱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዓለሙን በፈጠረባትና በተወለደባት ቀን፡ ራሱ ተመልሶ መጥቶ፡ ዓለሙን እስከሚያሳልፍባት ዕለት ድረስ፡ መስከረም ፩ ቀንን፡ የጌታን የልደት በዓል የሚያደርገው፡ ይህ፡ የጊዜ አቆጣጠር ሥርዓት፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተጠብቆ፡ ወደፊትም፡ ሳይነዋወጽ ጸንቶ ይቆያል።

የጌታ የልደቱ ቀን፡ በመስከረም ፩ ቀን መኾኑን ከሚያረጋግጡት ድርጊቶች መካከል፡ እናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እርሱን፡ ሕፃን ልጇን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ከሄሮድስ ሠይፍ ለማዳን፡ በሊቀ መላእክቱ፡ በቅዱስ ገብርኤል ቃል፡ መሠረት፡ አቅፋና አዝላ፡ ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር፡ ወደምድረ ግብፅ የተሰደደችበት ጊዜ፡ እንደኦሪቱ ሥርዓት፡ በተወለደ በአርባኛው ቀን፡ አስፈላጊውን ቍርባን ይዛ፡ በእግዚአብሔር ፊት ሊታቀርበው፡ ወደቤተ መቅደስ እንዲገባ ካደረገችበት፡ ከጥቅምት ፲ ቀን በኋላ፡ እስከኅዳር ፮ ቀን፡ ባለው ወራት ውስጥ መኾኑ፡ ሌላው ተጨባጭ እውነታ ኾኖ ይገኛል። በዚህ መሠረትኮ ነው፡ እመቤታችን፡ ሕፃን ልጇንና ተከታዮቿን ይዛ፡ ከኢየሩሳሌም ተነሥታ፡ የኢትዮጵያውያን ርስት እኾነችው፡ ቍስቋም ገዳም፡ በኅዳር ፮ ቀን፡ በደኅና የደረሰችው። ይኸው፡ ዛሬ፡ እኛ ኢትዮጵያውያንም፡ በወርኃ ጽጌ የሚውለውን፡ የስደትን ጾም ፈጽመን፡ የቍስቋምን በዓል፡ በዚሁ፡ በኅዳር ፮ ቀን የምናከብረው።

እንግዴህ፡ እውነታው፡ እንዲህ መኾኑ ከተረጋገጠ፡ የትስብእቱ (የጽንሰቱና የብሥራቱ) ወርና ዕለት፡ ልደቱ ከዋለበት ከመስከረም ፩ ቀን፡ ወደኋላ፡ ፱ ወር ከ፭ ቀን ሲቆጠር፡ ጽንሰቱ፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን መኾኑ ይረጋገጣል፤ ከዚህ የተነሣ፡ የብሥራቱ፥ የጾመ ነቢያትና የጥምቀቱ ወራትና ዕለታት፡ አኹን የሚውሉበትን ትክክለኛ ጊዜያት እንደያዙ ይቀጥላሉ።

በሌሎቹ ሥራዎቻቸው የምናደንቃቸው፡ የእኛ ሊቃውንት ግን፡ የዛሬዎቹ ጭምር፡ ይህንኑ ስሕተት ተቀብለው፡ እንዲህ ሥር ሰድዶ ይኖር ዘንድ፡ ዝም ብለው መመልከታቸው፡ ያስገርማል፤ ከተጠያቂነት ሊያመልጡ የሚችሉም አይመስለኝም።

# ምዕራፍ ፲፤ በዓል::

## የጌታ ልደት፡ ከነአጽዋማቱና በዓላቱ፡ ከቀመሩ አዋጅ ተለይቶ ስለመኖሩ::

ኢትዮጵያውያን፡ ከፈጣሪያቸው የተቀበሉት፡ በቃል ኪዳን የጸናውንና በቅዱሳት መጻሕፍት የተረጋገጠውን ሃይማኖታቸውን ብቻ ሳይኾን፡ ሥርዓታቸውን ጭምር ስለኾነ፡ እኒህን፡ ሕያዋን ቅርሶቻቸውን፡ በሰውኛ እውቀትና ብልሃት ሊያሻሽሉ፡ ወይም ሊለውጡ ቀርቶ፡ ከቶ ሊያስቡትም አይሞክሩትም:: እንደህልውናቸው ኹሉ፡ በዘመን አቆጣጠር ስሌታቸውም፡ በሌሎቹና በጥንቶቹ ግብፃውያን ላይ ሳይቀር፡ ቅድሚያ ያላቸው መኾኑ፡ ጠብቀው በኖሩት፡ የትውፊትና የቅርስ ይዞታቸው ይታወቃል:: ለዚህም፡ ግዙፉ ማስረጃ፡ የጥንቶቹ ግብፃውያን፡ የዘመን አቆጣጠራቸውን ባህል፡ የመሠረቱት፡ በታላቁ የዓባይ ወንዝ ውሃ ምልዓትና ጉድለት ላይ መኾኑ ነው::

የዓባይ ወንዝ ምንጭ ባለይዞታዎች፡ ጠባቂዎችና ባለአደራዎች የኾኑት ኢትዮጵያውያን፡ በአዳምና ሔዋን ከሚጀምረውና በኖኅ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ ከድምሳሴ ተርፎ ከቀጠለው ህልውናቸው አንሥቶ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም በመወለዱ፡ ፭ሺ፭፻ኛው ዓመተ ኵነኔ እስከተፈጸመባት፡ አዲሱም ዓመተ ምሕረት እስከተተካባት ቅጽበት ድረስ፡ ከዚያም ወዲህ፡ ሰዓታቸውን፡ ቀናቸውን፡ ሳምንታቸውን፡ ወራቸውንና ዓመታቸውን ለመቁጠር፡ አንድ ብለው የሚነሡበት ምልክት፡ የዓባይ ውኃ፡ በክረምቱ ዝናብ ምክንያት፡ ከመጨረሻው ምልዓቱ ደርሶ፡ የመቀነስ ርደቱን ማሳየት የሚጀምርበትን ዕለት ነበር:: ያንንም ዕለት፡ "መስከረም ፩ ቀን" ብለው ሠይመው፡ ዓመቱና ወሩ፡ ዕለቱና ሰዓቱ የሚብቱበት (የሚጀምሩበት) እንዲኾን ወስነውታል::

በግብፃውያን ምድረ በዳ እየፈሰሰ፡ በሲናይ ሰጩነቱ፡ ሕዝቡን የሚመግበው፡ ይኸው፡ በኢትዮጵያ ድልብ አፈርና የዝናብ ውኃ የሞላው፡ የዓባይ ወንዝ፡ ከመልካው አፍ አልፎ መፍሰሱን፡ መቀነስ የሚጀምርበት ጊዜ፡ ይኸው ቀን በመኾኑ፡ እነርሱም፡ ከኢትዮጵያውያን ባገኙት እውቀት፡ የአዲስ ዓመታቸው መግቢያ፡ በዚሁ ዕለት እንዲኾን አድርገዋል::

እዚህ ላይ፡ ኢትዮጵያ፡ እንደዛሬው ሳይኾን፡ በዚያን በጥንቱ ጊዜ፡ ስፋትዋ፡ እስከአስዋን ደርሶ፡ የዛሬዪቱን ግብፅ የምትዋሰን፡ ድንበረተኛ ብቻ ሳትኾን፡ ራስዋን፡ ግብፅንም ጭምር ጠቅልላ ታስተዳድር እንደነበረ፡ ማስታወስ ያሻል፤ የኢትዮጵያ አካል የነበረችው ኑብያ፡ ጥንታዊ ስሟን ለውጣ፡ በቅርቡ የተፈጠረችውን ሱዳንን ትቶ ማለት ነው:: ስለዚህ፡ ከዚያ ወዲህ የደረሰውን፥ በዛሬዎቹ የሃይማኖት ወገኖች በተባሉት ግብፃውያንም የተፈጸመውን እንተወውና፡ በዚህ፡ በዘመን አቆጣጠር ሥርዓት ረገድ፡ ኢትዮጵያውያን፡ በግብፃውያን ላይ ቅድሚያ እንደነበራቸው፡ ቀደም ብሎ የተገለጸው ቃል ያመለክታል::

ይህ፡ የኢትዮጵያውያን አቋም፡ እስከዛሬ ጸንቶ የኖረውና ዛሬም የማይናወጸው፡ ምክንያቱ፡ ይኸው፡ የሰዓትና የቀን፡ የሳምንትና የወር፡ የዓመትና የዘመን አቆጣጠራቸው፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቦ የሚገኘውን፡ የእግዚአብሔርን የተፈጥሮ ሥርዓት ሳይለቅ በመቀጠሉ ነው::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት፡ ከዚህ አቋሙ እንዲነዋወጽ ለምን ተደረገ? ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱ፡ ያው የታወቀውና የተለመደው፡ “ኢትዮጵያን፡ ከእነርሱ ይልቅ፡ ቀደምት የሚያደርጓትን የማስረጃ ምልክቶች ኹሉ፡ ደብዛቸውን ሳይቀር፡ ጨርሶ ለማጥፋት ነው!” በሚል፡ አጭር ቃል ይጠቃለላል።

ይህን እውነት ለማረጋገጥ፡ አንድ፡ ሊያስተሐቅሩት የማይቻለውን፡ ዛሬም ቆሞ የሚጮኸውን ምስክር ማቅረብ ይቻላል። ያም፡ በኢየሩሳሌም፡ ዐፅመ ርስት የኾነውን፡ የኢትዮጵያውያን ይዞታ፡ በኃይልና በሐሰት ነጥቀው ወስደው፡ ለሚሞግቱን፡ የሃይማኖት ወገኖች ለተባሉት አብያተ ክርስቲያን፡ ቀንደኛ መሪ የኾኑት እነማን ናቸው? እኒሁ፡ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ካህናት፡ ጳጳሳትና መሪዎቻቸው አይደሉምን?

ስለዚህ፡ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተጠሪዎች፡ ኢትዮጵያ፡ በኢየሩሳሌም የዓጽመ ርስት ይዞታዎቿና በዚያ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ፡ እስካሁን ሲፈጽሙት የኖሩትን፤ አሁንም፡ እየፈጸሙት ያለውን ክፋት፡ ጥፋትና በደል፡ በማስተዋል ለሚያየውና አትኩሮ ለሚያመዛዝነው እውነተኛ ታዛቢ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት፡ በየሌሎቹ ዘርፎች፡፣ በየመልኩ ካደረሱት በላይ፡ ይህንም የዘመን አቆጣጠራችንን ሥርዓት ለማፋለስ፡ በተፈጸመው ስሕተት፡ ዓይነተኛውን የተፅዕኖ አስተዋጽዖ “አላደረጉም!” ሊባል ከቶ አይቻልም።

### ስለስሕተቱ፥ ስሕተቱ መኖሩንም ስለማወቅና ስላለማወቅ፡፡

*ጥያቄ፦ ይህ ስሕተት፡ የኢትዮጵያዊነት መሠረታዊ አቋማችንን ለማናጋት፡ ኾን ተብሎ፡ በጥናትና በዕቅድ የተፈጸመ መስሎ ስለሚታይ፡ እኛም፡ በከፍተኛ ሃይማኖታዊና ብሔራዊ ደረጃ ይዘን፡ ብርቱ ጉዳያችንም አድርገን እንከታተለው ዘንድ፡ እስኪ፡ በበለጠ አስፋፍተህና አብራርተህ አስረዳን!?*

መልስ፦ መቼም፡ ይህ ስሕተት፡ ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ በመኾኑ፡ በቀላል ታይቶ፡ ሊታለፍ የሚገባው አይደለም፤ የስሕተቱን መኖር ለማያውቀው ወገን፡ “እኔ፡ መቼ፡ ይህን አወቅሁ!?”፥ ለሚያውቀውም፡ “እኔ፡ መቼ እንዲህ መሰለኝ” ብሎ፡ ኋላ፡ ምክንያት እንዳያቀርብ፡ ከእናንተና ከእኔ ጀምሮ፡ ኹሉም፡ ስለዚሁ፡ ዓቢይ ጉዳይ፡ እውነቱን እንዲያውቅ ማድረግ፡ ኹላችንም፡ ኃላፊነት አለብን። እኔም፡ ይህንኑ ጉዳይ በሚመለከት፡ ያለውን ትክክለኛ መረጃ፡ ምንም እንኳ፡ ቀደም አድርጌ፡ በተለያየ መንገድ ገልጬው የነበረ ቢኾንም፡ አኹንም፡ እንደገና፥ ወደፊትም፡ እንዲሁ እያብራራሁ ማስረዳቴ አይቋረጥም።

በዚህ መሠረት፡ እዚህ ላይ፡ ስለጌታ የልደት በዓል ቀን፡ ለጊዜው፡ በኹለት ቁም ነገሮች ተወስኜ፡ ከዚህ የሚከተለውን ሐተታ፡ በመልክ በመልኩ አቀርብላችኋለሁ።

## ምዕራፍ ፯፤ በዓል::
### ስለስሕተቱ፥ ስሕተቱ መኖሩንም ስለማወቅና ስላለማወቅ::

---

*ጥያቄ:- ይህን የመሰለው አቀራረብህማ: ስለርእስ ጉዳዩ: እውነቱን: በጥልቀት ለማወቅ ለምንጥረው: ለእኛና እንደእኛ ላሉት ኹሉ: በጣም ያስፈልገናል፥ ስለዚህ: እንሰማው ዘንድ: እስኪ: በአንደኛው ቀም ነገር ጀምርልን?!*

መልስ:- እኛ ኢትዮጵያውያን: የዓለሙ መድኃኒት: ኢየሱስ ክርስቶስ: በእውነተኛው: የኢትዮጵያውያን ቀን: ይኸውም: መስከረም ፩ ቀን: ከድንግል ማርያም ስለተወለደ: "ዓመተ ፍዳ ተሸሮ: ዓመተ ምሕረት ተተካ!" ብለን: ታላቅ የዐውደ ዓመት በዓል እናደርጋለን::

ለዚህ ላበቃን አምላክም: ከእራሲቱ ቅድስት እናቱና ከጠባቂዋ ጻድቅ ዮሴፍ: ከመላእክትና ከእረኞች: ከሰብአ ሰገልና ከእንስሶች ጋር: በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኮ ኾነን: በምሥራች ዝማሬና በሓሴት ቃል: የደስታ ምስጋናችንን እናቀርባለን:: ነገር ግን: ይህ ኹሉ ከኾነ በኋላ: ለአራት ወራት ቆይተን: በታኅሣሥ ፳፱ ቀን: እንደገና እንድናከብረው ሲደረግ ቆይቷል:: ለምን? ምክንያቶቹ ምንድር ናቸው: እስኪ: እነዚህኑ: ጥቂት ጠለቅ ብለን እንመልከታቸው?!

በአኹኑ ጊዜ: የጌታ የልደት በዓል: በመላው ዓለምና በቤተ ልሔም የሚከበረው: በታኅሣሥ ወር በአንድ: በተወሰነ ቀን ሳይኾን: በዚሁ ወር መጨረሻና በጥር ወር መጀመሪያ ባሉት ቀኖች አካባቢ: በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት: ቢያንስ ቢያንስ: በአራት የተለያዩ ዕለታት ነው:: በዚህም: የሃይማኖት ወደረኞቻችን: አይሁድም: እስላሞችም፥ አረማውያንም፥ ሃይማኖተ቎ቢሶችም እንደሚያፌዙብን ይነገራል፥ ይታያልም::

ምዕራባውያንና አብዛኛዎቹ ምሥራቃውያን ክርስቲያኖች: የልደትን በዓል የሚያከብሩት: በእነርሱ የዘመን አቆጣጠር: በDecember 25 (ዲሴምበር ፳፭): (በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር: በታኅሣሥ ፲፮) ሲኾን: ኢትዮጵያውያንና ጥቂቶች ምሥራቃውያን ክርስቲያኖች ደግሞ: ያው: በታኅሣሥ ፳፱ ቀን: በእነርሱ አቆጣጠር: በJanuary 7 (ጃንዋሪ ፯)፥ ሌሎቹም የቀሩት አናሳ ወገኖች: በእነዚህ ቀኖች መካከል ባሉ: የተለያዩ ኹለት ዕለታት ያከብራሉ::

በምዕራባውያን፥ ማለትም: በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሥነ ከዋክብት ሊቃውንት ዘንድ: የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን: "በትክክል አይታወቅም" የሚለው የግምት አስተሳሰብ: እስከዛሬም እንደጸና ይገኛል:: ከዚህ የተነሣ: ከቀድሞ ጀምሮ: የልደቱ ቀን: "በዚህ ዕለትና ዓመተ ይኹን!" እያሉ የወሰኑት: በሥጋ ፍልስፍናና በዘፈቀደ፥ በምናልባትና በመላምት ብቻ መኾኑ ተረጋግጧል:: እነሆ: የምዕራባውያን ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት: የጥሮውን የሮማውያንን አረማዊ ባህል አስወግደው: በእርሱ ምትክ: B.C. (Before the Birth of Christ) "ከክርስቶስ ልደት በፊት" እና A.D. (Anno Domini) "ከክርስቶስ ልደት በኋላ" የሚለውን የዘመናት መከፈያ ሥርዓትን ለመተካትና ለመመሥረት ተገድደዋል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ይህም የኾነው፡ ትክክለኛውን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ቀን፡ ማለትም፡ በዓመተ ኵነኔውና በዓመተ ምሕረቱ መገናኛ ላይ፡ አልቦ (zero ዜሮ) ቁጥር የሚኾነውን ጊዜ፡ በቁርጥ ለማግኘት ስላቃታቸው፡ ይህን ዕለት ፈጥረው፡ በዘፈቀደ እንደወሰኑት ታውቋል፡ ለዚህም፡ በዋቢነት፡ ስሙ የሚጠቀሰው፡ Dionysius Exiguus ዲዮኒሲዩስ ኤክሲጉዑስ የተባለው፡ ጣልያናዊ፡ የካቶሊክ መነኵስ ነው፡፡ እርሱም ይህን አሳብ ያመነጨው፡ እንደእነርሱ አቈጣጠር፡ ከ፭፻ እስከ ፭፻፵፭ ዓመተ ምሕረት ባለው ዘመን ውስጥ ነበር፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በነቢያት ትንቢት መሠረት ይወለድ ዘንድ፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ማሕፀን ኾኖ፡ በጻድቁ ቅዱስ ዮሴፍ ጠባቂነት፡ ከገሊላ ናዝሬት መኖርያቸው፡ ወደቤተ ልሔም በረት የተጓዙት፡ የሮማውያን ገዢ የነበረው፡ አውግሥጦስ ቄሣር፡ በግዛቱ ውስጥ የሚኖረው፡ ሰው ኹሉ፡ በየትውልድ ቦታው እየኼደ እንዲመዘገብ፡ ባወጀው ትእዛዝ መነሻነት መኾኑ ይታወቃል፡፡ ያ ትእዛዝ የታወጀበት ጊዜም፡ ምዕራባውያን፡ "የክርስቶስ የልደት ቀን ነው" ብለው የወሰኑትን፡ የዘመን አቈጣጠራቸውን ቀመር ተከትሎ ሲሰላ፡ "ከክርስቶስ ልደት በኋላ" በ፩ኛው ዓመተ ምሕረት ላይ የዋለ ኾኖ ተገኝቷል፡፡

ከእኒህ ኹሉ ማስረጃዎች ጋር፡ የጌታን የልደት በዓል ለማክበር ሲባል፡ የልደቱ ቀን፡ ቀደም ብለው የተጠቀሱትን ዕለታት በሚያካልለው፡ በዚህ፡ በአንድ ሰሞን፡ በተለይም፡ በእነርሱ የቀን አቆጣጠር፡ በDecember 25 (ዲሴምበር ፳፭)፡ እንዲውል የተደረገበት፡ አንድ፡ ሌላ፡ የታወቀ ዋና ምክንያት ደግሞ አለ! ይኸውም፡ በእምነታቸው፡ ገና አረማውያንና አሕዛብ የነበሩት፡ ሮማውያንና የቀሩት የአውሮጳ ሕዝቦች፡ የጣዖትና የባዕድ አምልኳቸውን ልደት፡ ወይም፡`የመመሥረቻ ቀን ምክንያት በማድረግ፡ በተመሳሳይ.መልክ ይፈጽሙት ከነበረው፡ የፌንጣዚያ በዓላቸው ጋር፡ አዲሱ የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት፡ አብሮ ኾኖ በዚሁ ሰሞን እንዲከበር፡ የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች፡ በቅን ዓላማ መፈለጋቸው ነው፡፡

ከጌታ ልደት ጋር ተመሳሳይነት ነበራቸው የተባሉት፤ በዚያው ዕለት፡ ማለትም፡ በእነርሱ የቀን አቆጣጠር፡ በDecember 25 (ዲሴምበር ፳፭)፥ ወይም በዚያው ሰሞን የሚውሉትና የሚከበሩት፡ እነዚያ፡ የአረማውያኑ በዓላት፡ ለምሳሌ ያህል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ፡- ፩ኛ፡ ሮማውያን፡ ስሙን በመታሰቢያነት፡ January (ጃንዋሪ) ብለው፡ ለዓመቱ የመጀመሪያ ወር የሰጡለት፡ Janus (ጃኑስ) የተባለው ጣዖታቸው በዓል፤ ፪ኛ፡ Natalis Solis Invicti (ናታሊስ ሶሊሲ ኢንቪክቲ)፡ ማለትም፡ “ያልተደፈረችው ፀሓይ የልደት ቀን” የሚለው የልደት በዓል፤ ፫ኛ፡ “ሚዕራ” የምትባለው፡ የኢራናውያን የምሥጢር ጣዖት፡ የልደት በዓል ቀን፤ ፬ኛ፡ የአረማውያኑ በዓል፡ ጥንቱኑ፡ ኾን ተብሎ፡ እንዲውል የተደረገው፡ በበረዶው ወራት መካከል ኾኖ፡ ያም ወቅት፡ አረማውያኑ፡ ለክረምትና ለፀሓይ፡ በጥድ ዛፍ የሚያቀርቡትን የባዕድ አምልኮ ሥርዓታቸውን የሚፈጽሙበት፥ ሐሤት የሚያደርጉበትና የመልካም ምኞት ስጦታን የሚለዋወጡበት ታላቅ በዓል፡፡

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል።

## ስለስሕተቱ፡ ስሕተቱ መኖሩንም ስለማወቅና ስላለማወቅ።

---

እንግዲህ፡ እዚህ ላይ፡ በዚያን ዘመን፡ አረማውያንና አሕዛብ የነበሩት ሮማውያንና አውሮጳውያን፡ የክርስትናን እምነት እንዲቀበሉ በተደረገበት ጊዜ፡ ይህንኑ አዲስ የክርስትና ሃይማኖታቸውን በበለጠ እንዲያጸኑት ለማበረታታት ሲባል፡ በጊዜው የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ልኡካንና መሪዎች፡ የተጠቀሙበትን ዘዴ፡ በቀላሉ መመልከት ይቻላል፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡ ጣዖት አምላኪዎች ለነበሩት ለግሪክ ሰዎች፡ በአቴና ከተማ፡ በአርዮስፋጎስ አደባባይ ተገኝቶ በሰበከላቸው አቀራረብ ዓይነት ማለት ነው። ይኸውም፡ "ያ፡ በዛፍና በልዩ ልዩ ምልክቶች ታመልኩት የነበረው አምላክ፡ እነሆ፡ ሰው ኾኖ ተወልዶ፡ ከሰይጣን ግዞነት፡ ከኃጢአት ቀንበርና ከሞት ዕዳ አዳነን! የእርሱ ልጆች የምንኾንበትን ጸጋን ሰጥቶን፡ የዘለዓለም ሕይወት ወራሾች አደረገን!" በማለት፡ በዚያው፡ የአማልክቶቻቸውን የልደት ወይም የመታሰቢያ በዓላት በሚያከብሩበት ቀንና በዚያው በጥንቱ፡ የአምልኮ ምልክታቸው፡ ባህላቸውና ሥርዓታቸው ተቀይሮ እንዲቀጥል ማድረጋቸው ነው። ይህ ኹሉ፡ በራሳቸው፡[፻፳፱] በምዕራባውያኑ የታከረ ነገር መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግቦ ይገኛል።

በምዕራባውያን ዘንድ፡ ዛሬ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የልደቱ ቀን፡ ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ዕለት እንዲውል የተወሰነው፡ ምልክቱና ሥርዓቱም፡ ባተጌጠ የጥድ ዛፍ እንዲኾን የተደረገው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን፡ በተለይ፡ እናንተና እኔ፡ በኢትዮጵያዊነታችን፡ ልናጤነው ይገባናል። የገናን በዓል፡ በጥድ ዛፍ የማክበሩ ባህል፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን፡ ምናችንም አለመኾኑን፡ በብርቱ ልትገነዘቡት ያስፈልጋችኋል። ይህንም ነገር፡ በቦታው፡ ርእስ አድርገን እንወያይበታለን።

በእነርሱ፡ በምዕራባውያኑ በኩል፡ ይህን ወጋቸውን እንዲጠብቁ የተገደዱበት፡ ቀደም ብዬ የገለጽሁላችሁ ምክንያት፡ ከእኛ ጋር የሚነጻጸርበት ኹኔታ አለ፡ ይኸውም፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ፡ በኪዳነ ልቦናው እምነትና ሥርዓት፡ ጸንቶ የኖረው፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ ቀደም ብሎ፡ ወደኪዳነ ኦሪቱ፤ በመጨረሻም፡ ወደኪዳነ መንፈስ ቅዱሱ እምነትና ሥርዓት በተሸጋገረበት ጊዜ፡ በታቦተ ጽዮን አማካይነት ሲካኼድ የቆየውን አምልኮተ እግዚአብሔር፡ በሠመረ ሽግግር እንዲቀጥል ያስቻለ ስልት፡ በቤተ ክህነቱ ዘርፍ ባሉት ኢትዮጵያውያን አዋቆች ተተልሞ፡ በሥራ ላይ መዋሉ ነው፤ ያም ስልት፡ የቀድሞዋን የሚተካ፡ በአዲሱ ኪዳን መሠረት የተቀረጸ ጽላትና ታቦት ተዘጋጅቶ፡ በየቤተ መቅደሱ እንዲገኝ ማድረጉ ነበረ።

በዚህ፡ የመጀመሪያው ቁም ነገር ይጠናቀቃል።

**ጥያቄ፡-** *አኹን ደግሞ፡ ኹለተኛውን ቁም ነገር እንስማው!*

**መልስ፡-** የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን፡ በምዕራባውያኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ሳይቀር፡ በትክክል ባለመታወቁ፡ እኒሁ መሪዎች፡ ለዚህ ችግር "መፍትሔ ይኾናል!" ብለው የፈጸሙትን ዘዴ፡ እስኪ እንመርምር!

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

አዎን! መፍትሔው፡ ይህንኑ፡ የጌታን የልደት በዓል፡ ወደክርስትና ሃይማኖት የተመለሱት፡ አዲሶቹ ምእመናን፡ ቀድሞ በአረማዊነታቸው ጊዜ፡ የበዓላቸው ዕለት አድርገው ያከብሩት በነበረው፡ በDecember 25 (ዲሴምበር 'ታኅሣሥ' ፳፭) ቀን እንዲውል መወሰን ብቻ ኾኖ ተገኘ። ይህንም ያደረጉት፡ በአዲሶቹ ክርስቲያኖች ዘንድ፡ የቀድሞው የበዓላቸው ቀን ሳይፋለስ መቀጠሉ፡ ለክርስትናው እምነት መጽናትና መስፋፋት፡ ጠቃሚና መልካም ዘዴ ሊኾን እንደሚችል በማመናቸው መኾኑን፡ ቀደም ብዬ ካስማኋችሁ ሐተታ፡ የተረዳችሁት ይመስለኛል።

የዚህ ሐተታ ፍሬ ነገር ሲጠቃለል፡ "ጌታ የተወለደበት ነው" ተብሎ የሚከበረውን ቀን፡ አጠራጣሪ የሚያደርግ፡ የስሕተት ጭብጥ መኖሩን የሚያመለክት ከመኾኑ ጋር፡ ወደሌላ የማስረጃ ፍለጋና ምርምር እንድናመራ የሚጋብዝ፡ አስተማማኝ ፍንጭንም ያበረክትልናል። ምርምራችንም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ተወልዶበታል" የሚባለው፡ የDecember (ዲሴምበር 'ታኅሣሥ') ወር፡ ቤተ ልሔም በምትገኝበት፡ በሰሜኑ ክፍለ ዓለም ክልል፡ ክረምትና በረዶ የሚጸናበት ጊዜ ስለኾነ፡ "ያ፡ የክረምትና የበረዶ ወራት፡ በእርግጥ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን ቀን የያዘ ነበር ወይ?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መቻል ይኾናል።

ይህን ችሎታ የሚያስገኝልን ደግሞ፡ ቀጥሎ ያለው የወንጌል ቃል ነው፡ *"በዚያም ወራት፡ ዓለሙ ኹሉ እንዲጻፍ፡ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች። ቄሬኔዎስ፡ በሶርያ አገር፡ ገዥ በነበረ ጊዜ፡ ይህ፡ የመጀመሪያ ጽሕፈት ኾነ። ኹሉም፡ እያንዳንዱ፡ ይጻፍ ዘንድ፡ ወደከተማው ሄደ። ዮሴፍም ደግሞ፡ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለነበረ፡ ከገሊላ፡ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ፡ ቤተ ልሔም ወደምትባል፡ ወደዳዊት ከተማ፡ ወደይሁዳ፡ ፀንሳ ከነበረችው፡ ከእጮኛው ማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ። በዚያም ሣሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፤ የበኵር ልጇንም ወለደች፤ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶች ማደሪያም፡ሥፍራ ስላልነበራቸው፡ በበረት አስተኛችው። በዚያም ምድር፡ መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ።"*

አውግስጦስ ቄሣር፡ ይህን ትእዛዝ ያስተላለፈው፡ *"አንቺ ቤተ ልሔም! የይሁዳ ምድር! ከይሁዳ ገዥዎች ከቶ አታንሺም! ሕዝቤን፡ እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን፡ ከአንቺ ይወጣልና!"* የሚለው፡ የእግዚአብሔር የትንቢት ቃል እንዲፈጸም ለማድረግ መኾኑ የታመነ ነው።[፻፳፰]

ይኹን እንጂ፡ አውግስጦስ ቄሣር፡ በዘመኑ እጅግ ሰፊ በነበረው ግዛቱ ውስጥ ይኖር የነበረው፡ ያ ኹሉ እልፍ አእላፋት ሕዝቡ፡ ዝናሙና በረዶው፡ በዚያ ክፍለ ዓለም በሚከፋበትና በሚበረታበት፡ በክረምቱ ወራት፡ ከያለበት እንዲንቀሳቀስ ያደረገውን፡ ያን የመሰለውን ትእዛዝ ያስተላልፋል ብሎ እንዴት ሊታሰብ ይችላል? አይቻልም።

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል::

## ስለስሕተቱ፥ ስሕተቱ መኖሩንም ስለማወቅና ስላለማወቅ::

ወራቱ: በእርግጥ ክረምት ከኾነ: ቄሣራዊዉን ትእዛዝ በመፈጸምና በማስፈጸም ረገድ: በእያንዳንዱ ዜጋና ቤተሰብ፤ በመንግሥቱ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞችም ላይ ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን እንግልትና ጫና: በድንግል ማርያምና በጠባቂዋ በዮሴፍ ላይ በደረሰው ችግር: በቀላሉ መረዳት ይቻላል::

ታዲያ: ልትወልድ እንደተቃረበችው: እንደእመቤታችንና እንደጠባቂዋ ዮሴፍ: ከመኖርያ ቀበሌያቸው ተነሥተው: እንደዛሬው እንኳ: ተሽከርካሪና መጓጓዣ ባልነበረበት ኹኔታ: ጓዛቸውን ጭነው ወይም ተሸክመው: ያን ያህል: ከዚያም ሊርቅ የሚችል የእግር መንገድ ጉዞ ስለሚያደርጉ ዜጎቹ: ያ መንግሥት አያስብምን? ለዜጎቹ የማያዝን እንኳ ቢኾን: ትእዛዙን ለማስፈጸም: መንግሥቱ ራሱ: የሚያደርገው ዝግጅትና ድርጅት እንዴት ሊከናወንለት ይችላል? አይቻልም:: ዛሬ: የመገናኛና የማጓጓዣ ዘዴዎች ተከናውነው በሚገኙበት ጊዜ እንኳ: የሕዝብ የምርጫ ሥርዓት የሚካኼደው: የወራቱ አየር ጠባይ: ተስማሚ መኾኑ በተረጋገጠበት: የበጋ ወራት እንደኾነ ይታወቃል::

የአይሁድ ሎሌዎችና የጲላጦስ ወታደሮች: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዘውና አሥረው: ወደሊቀ ካህናቱ ግቢ የወሰዱበት የምሽቱ ጊዜ: *"ብርድ ነበርና: አገልጋዮችና ሎሌዎች: የፍም እሳት አንድደው: ቆመው ይሞቁ ነበር፡ ጴጥሮስም ደግሞ: ከእነርሱ ጋር ቆሞ: ይሞቅ ነበር"* የሚለውን የመሰለ የወንጌላዊ አገላለጽ: በዚህ: በጌታ የልደት ጊዜ አልተወሳም:: ጌታ የተወለደበት ወራት: እንኳንስ የክረምት ዝናምና በረዶ ይቅርና: ብርድ እንኳ የነበረ መኾኑን: የሚያስረዳ: አንዳችም ምልክት የለም:: ቢኖርም እንኳ: ወራቱ: ምንም ዓይነት: የክረምት ምልክት የሌለው: እንዲያውም: ፍጹም በጋ መኾኑን የሚያረጋግጥ ኾኖ ይገኛል:: ይኸውም: ወንጌላዊው ሉቃስ: ስለልደቱ ኹኔታ፥ በጊዜው ስለነበረው: የአየሩ ጠባይና ስለተፈጸመው ተአምራዊ ድርጊት: በጻፈው ዜና ውስጥ: ቀደም ብሎ የተጠቀሰው፥ በተለይም: *"በዚያም ምድር: መንጋቸውን: በሌሊት ሲጠብቁ: በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ::"* የሚለው ቃልና ምንም ችግር ያልነበረበት: የሰብአ ሰገል የመዘዋወር ጉዞ: ለዚህ ምስክርነት ይበቃል:: ይህም: ወራቱ: በጋ እንጂ: ዝናምና በረዶ የሚወርድበት: ክረምት: ማለትም: የታኅሣሥ ወር ያለመኾኑን ያረጋግጣል::[፻፳፯]

ለዚህ ጉዳይ: ከወንጌላዊው ያለፈ: ሌላ ምስክር አያሻም::

"ቍር ወይም ብርድ ነበረ" ተብሎ የሚሰጥ የትርጓሜ ትችት ቢኖር እንኳ: ያ ቍር ወይም ብርድ: በአገራችን: በጥቅምትና በጥር ማታና ሌሊት የሚወርደውን የሚመስል መኾን ይኖርበታል:: የሌሊት ቀዝቃዛ ነፋስ: ወዲያና ወዲህ በሚነፍስበት፥ ዝግ ግድግዳ በሌለውና በፍርግርግ በተከለለ በረት ውስጥ፡ ብርድ የለም እንዴት ሊባል ይቻላል? ከዚህ የተነሣም: በበረቱ የነበሩ እንስሳት ሳይቀሩ: "በእስትንፋሳቸው አሟሟቁት" ተብሎ በተጨማሪ ሓተታ ቢተረጐም: አያስደንቅም::

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

እንግዲህ፡ በዚህ ኹሉ ማስረጃ፡ ያ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ወራት፡ ቤተ ልሔምን፥ መካከለኛው ምሥራቅንና መላውን አውሮጳን ባቀፈው በሰሜኑ ክፍለ ዓለም፡ የፀሓይ ብርሃንና ሙቀት የሚሰፍንበት፡ በእኛ፡ የክረምት ወራት፥ በእነርሱ ደግሞ፡ የሓጋይ ወይም የበጋ ወራት መኾኑ፡ አሌ ሊባል ከቶ አይቻልም።

የመስከረም ወር፡ በዚያ ክፍለ ዓለም፡ ተስማሚ የአየር ጠባይ የሚታይበት፡ የበጋው ወራት ማብቂያ ስለኾነ፡ በትክክል ሊታወቅ ያልተቻለው፥ ነገር ግን፡ በሰዎች፡ የምናልባትና የመላምት ውሳኔ፡ በDecember 25 (ዲሴምበር 'ታኅሣሥ' ፳፱) ቀን እንዲውል የተደረገው፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ ቀን፡ እውነተኛውና ትክክለኛው፡ በኢትዮጵያኑ የጊዜ አቆጣጠር፡ "መስከረም ፩ ቀን ነው!" ብለን መደምደም ይኖርብናል።

በዚህ፡ ኹለተኛው ቁም ነገር ይጠቃለላል።

### የኢትዮጵያውያኑ የዘመን አቆጣጠር፡ ከሌሎቹ የሚለይበት ባሕርይ።

*ጥያቄ፡- ቀደም አድርገህ እንደገለጽህልን፡ በይበልጥ፡ በአረማዊነት ባህል፥ በመጠኑም፡ በከዋክብት ሥነ እውቀት ላይ የተመሠረተው የምዕራባውያን የዘመን አቆጣጠር፡ ከኢትዮጵያውያኑ የዘመን አቆጣጠር፡ የሚለይበት ባሕርይና አኹን ያለበት ቀውስ የደረሰበት ለምን እንደኾነ፡ የተቻለህን ያህል ብታብራራልን!*

መልስ፡- ኢትዮጵያውያን፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው ላይ የመሠረቱትን፡ ይህን የጊዜ አቆጣጠር ሥርዓት፡ ምዕራባውያን፥ ኦርቶዶክሳውያን የተባሉት አብያተ ክርስቲያናት ጭምር፡ በአረማዊው፡ ዩልየስ ቄሣርና ጎርጎርዮስ (ግሬጎሪ) ፲፫ኛ በተባለው፡ በካቶሊካዊው ጳጳስ ስሞች እየሠየሙ፥ በየጊዜው እየለዋወጡና በመጨረሻ፡ ፰ ዓመታት ከ፲ ቀናት ያህል አክለውበት መቆየታቸው ይታወቃል። በዚህ የአቆጣጠራቸው ስልት፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ቀን፡ ከ፬ እስከ፯ ዓመታት ለሚደርስ ዘመን፡ ከፍ አድርገው እንዲጨምሩ በመገደዳቸው፡ ይህን፡ ሰው ሠራሽ ቀውስ አስተካክለው ለማስታረቅ አቅቷቸው፡ እነሆ፡ እስካኹን ሲባዝኑ ይገኛሉ። በዚህ፡ በእነርሱው አቆጣጠር፡ ጌታ፡ የተወለደው፡ "በ፬፥ በ፮ ወይም በ፯ ዓመተ ምሕረት ላይ ሳይኾን አይቀርም" ከማለት በስተቀር፡ እርግጠኛውን ቀን፡ በቁርጥ ሊወስኑ ሳይቻላቸው ቀርቷል።

ይህ ቀውስ የተፈጠረባቸው፡ የጌታን የልደት ዓመት፡ አንድ ብለው መቁጠር ከጀመሩ በኋላ፡ ያ፡ የዓመተ ምሕረት መነሻ ዘመን፡ በአረማዊነት ዘመናቸው፡ "ጁልያን" በሚል ስምና በተለያየ ስልት ይጠቀሙበት በነበረው የአቈጣጠር ሥርዓታቸው፡ በ፬፥ በ፮ ወይም በ፯ ዓመታት ላይ ውሎ ስላገኙት ነው።

## ምዕራፍ ፯፤ በዓል::
### የኢትዮጵያውያኑ የዘመን አቆጣጠር: ከሌሎቹ የሚለይበት ባሕርይ::

ሌላው: ይህን ችግር የፈጠረባቸው ምክንያት: የምዕራባውያን የጊዜ አቈጣጠር: እንደኢትዮጵያውያኑ: በአንድ መሠረት ላይ ታንጸና በአንድ በተስተካከለ ሥርዓት ተቀምሮ የሚመራ ባለመኾኑ ነው:: ይህንም: ከዚህ የሚከተለውን ማነጻጸሪያ ሓተታ በመመልከት መረዳት ይቻላል::

ኢትዮጵያውያን: "የእግዚአብሔር ገነት" ተተከላባት: አዳምና ሔዋን የተፈጠሩባት አገራቸው የምትገኘው: በምድር ማዕከል ወይም መቀነት ክልል ውስጥ ስለኾነ: የጊዜ አቈጣጠራቸው ሥርዓት: መዓልቷና ሌሊቷ: ዓመቱን ሙሉ: በ፲፪፥ በ፲፪ ሰዓታት: እኩል በተከፈለበት የአሠፋፈር ስልት ላይ ተመሥርቶ: የባሕረ ሓሳቡ ቅመራ: ሥርዓቱን ጠብቆ: ያለችግር ይካኼዳል:: ይኸውም: ወደኋላ: ወደረቂቃኑ ሳንኼድ: ከሣልሲት ተነሥተን: እስከዓመት ብንቈጥር እንኳ: ቀመሩ: የተስተካከለ ኾኖ እናገኘዋለን:: ማለትም: ፷ (ስድሳ) ሣልሲታት: ፩ (አንድ) ካልዕት (Second)፥ ፷ ካልዕታት: ፩ ደቂቃ፥ ፷ ደቂቃት: ፩ ሰዓት፥ ፳፬ ሰዓታት: ወይም ፷ ኬክሮስ: ፩ ዕለት ይኾናሉ:: ፩ዱ ዕለት ደግሞ: ፀሓይ እንድትሠለጥንበት የተፈጠረችበት: ፲፪ ሰዓታትን የያዘው: የብርሃን ጊዜ: "መዓልት"፥ ጨረቃ እንድትሠለጥንበት የተፈጠረችበት: ፲፪ ሰዓታትን የያዘው: የጨለማ ጊዜ: "ሌሊት" ይባላል::

የመዓልቱ የጊዜ አቆጣጠር: የተፈጥሮውን ሥርዓት በመከተል: "ከቀትር በፊት" እና "ከቀትር በኋላ" ተብሎ: ፀሓይ: ጮራዋን በምትፈነጥቅበት: በንጋቱ ፩ ሰዓት ይጀምርና: በምትጠልቅበት: በምሽቱ ፲፪ ሰዓት ያበቃል፤ የሌሊቱም ጊዜ: እንደዚሁ: እስከእኩለ ሌሊት ድረስ: "ከማታው"፥ ከእኩለ ሌሊት በኋላ ደግሞ: "ከሌሊቱ" እየተባለ: ጨረቃ ከምትታይበት: ወይም ጨለማው ከሚጀምርበት: ከምሽቱ: ፩ ሰዓት ይነሣና: ጎህ በሚቀድድበት: በንጋቱ ፲፪ ሰዓት ይቆማል::

በዚህ መሠረት የተደለደለችው: አንዲቱ ዕለት: ሰባት ስትኾን: ፯ቱ ዕለታት: ፩ ሳምንት ይኾናሉ::

የምዕራባውያኑ ግን: እንዲህ አይደለም:: ምዕራባውያን: የሰሜኑንና የደቡቡን የመሬት ዋልታ ተከትለው: በሰሜንና በደቡብ ክፍላተ ዓለማት: የሚኖሩ በመኾናቸው: ኢትዮጵያውያን: ክረምት፥ መፀው፥ በጋ፥ ጸደይ እንደሚሉት: የእነርሱም ዓመት: Winter (ዊንተር), Spring (ስፕሪንግ), Summer (ሰመር) Autumn (አተምን) በተባሉ: በአራት የተለያዩ ወራት ተከፋፍሎ: በክረምቱ: ሌሊታቸው: እስከ ፳ ሰዓታት የሚቀንስበት፥ በበጋው ወራት ደግሞ: መዓልታቸው: እስከ ፳ ሰዓታት የሚጨምርበት፥ እንዲያውም: ወደሰሜኑም ኾነ ወደደቡቡ የመሬት ዋልታ ጫፍ እየተጠጉ በኼዱ መጠን: የሚቀነሱት: ወይም የሚጨመሩት ሰዓታት እያደጉ ይኼዱና: ወደመጨረሻው ጽንፍ ላይ ሲደርስ: ከናካቴው: ፮ ወራት ሙሉ: ሌሊት ብቻ፥ ወይም መዓልት ብቻ ይኾናል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር: ማነው?

---

ይህም ማለት: ይህ ኹኔታ: በሰሜኑና በደቡቡ ክፍላተ ዓለም: በዓመቱ ውስጥ: እንዲህ ስለሚፈራረቅ: የክረምቱ ብርዳማ ጠባይ: ቀደም ብሎ እንደተገለጸው: የሰሜኑን ክፍል በሚያጠቃበት ጊዜ: በደቡቡ ክፍል ደግሞ: የበጋው ፀሓያማ ጠባይ ይሰፍናል ማለት ነው።

ይህ ብቻ ሳይኾን: በዓመት: ኹለት ጊዜያት: በየ፮ ወሩ: የሰዓት አቆጣጠራቸውን: እንደየክፍለ ዓለማቸው አቀማመጥ: በ፩ ሰዓት ያሳድጉታል፡ ወይም በ፩ ሰዓት ይቀንሱታል።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ: ፯ቱ የሳምንቱ ቀኖች: የእግዚአብሔር: የሥነ ፍጥረት ሥራው: በተራና በቅደም ተከተል የተካኼደባቸውንና በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገቡትን የዕለታት ስም እንደያዙ: የአዳምና ሔዋን ቋንቋ በኾነው: በግእዝ: "አሐዱ": "አንድ"፥ ወይም: "መጀመሪያ ቀን" ለማለት: "እሑድ"፥ ቀጥሎ: "ኹለት"፥ ወይም: "ኹለተኛ ቀን" ለማለት: "ሰኑይ": "ሰኞ"፥ ቀጥሎ: "ሦስተኛውን ቀን": "የሰኞ ማግሥት" ለማለት: "ማግሰኞ": ቀጥሎ: "አራት"፤ ወይም: "አራተኛ ቀን" ለማለት: "ረቡዕ"፥ ቀጥሎ: "አምስት"፥ ወይም: "አምስተኛ ቀን" ለማለት: "ሓሙስ"፥ በመጨረሻ: "የሥራ ማካተቻ"፤ ወይም: "የሰንበት መግቢያ"፥ ወይም: የሳምንቱ ጊዜ: የሚጠልቅበት ቀን" ለማለት: "ስድስተኛውን ቀን": "ዓርብ"፥ በሰንበት ጌታ: በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ: "ወደዘለዓለማዊነት ከመለወጧ በፊት: ቀድሞ የነበረችበትን ኹኔታ ለማስታወስ: "ሰባተኛዪቱን የሰንበት ቀን": "ቅዳሜ" ብለው ይጠርዋቸዋል።

ምዕራባውያን ግን: ለእነዚሁ የሳምንት ቀኖች: የሰጧቸውን የአረማውያን ጣዖታት አማልክቶቻቸውን ስም እንመልከት! Sunday: Sun's day (ሳንዴይ): ማለት: የፀሓይ ቀን፥ Mon'ay: Moon's day (ማንዴይ): የጨረቃ ቀን፥ Tuesday: Tui's day (ቲዩስዴ...): ማለት: የጦርነቱ አምላክ: የቲዩ ቀን፥ Wednesday: Woden's day (ዌድንስዴይ): ማለት: የታላቁ አምላክ: የዎደን ቀን፥ Thursday: Thor's day (ተርስዴይ): ማለት: የነጐድጓዱ አምላክ: የቶር ቀን፥ Friday: Frigg's day (ፍራይዴይ): ማለት: የታላቁ አምላክ: የዎደን ሚስት: የፍሪግስ ቀን፥ Saturday: Saturn's day (ሳተርዴይ): ማለት: የሰማዩ ኮከብ: የሳተርን ቀን።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ: ፴ ዕለታት: ፩ ወር ሲኾኑ፥ ፲፪ ወራት እና ፭ ዕለታት ተሩብ ደግሞ: ፩ ዓመት ይኾናሉ። ፭ቱ ዕለታት ተሩብ: "ጳጉሜ" ይባላሉ። "ጳጉሜ": የቃል ለቃል ትርጉሙ: "ተውሳክ": "ጭማሪ"፥ "ተረፍ": "ትርፍ" ማለት ነው። ፲፪ቱ የምዕራባውያን ወሮች ግን: ፳፰: ዕለታትን፥ በየአራት ዓመቱም: ፳፱ ዕለታትን ከያዘውና (February ፌብሩአሪ) ከሚባለው: ከአንደኛው ወር በቀር: እኩሌቶቹ: በ፴፥ የቀሩትም: በ፴፩ ዕለታት ተመድበው: ይህን በመሰለ የተዘበራረቀ መልክ ይቆጠራሉ።

## ምዕራፍ ፮፡ በዓል፡፡
### የኢትዮጵያውያኑ የዘመን አቆጣጠር፡ ከሌሎቹ የሚለይበት ባሕርይ፡፡

በኢትዮጵያውያን በኩል፡ ከመስከረም እስከነሐሴ ድረስ ያሉት፡ ፲፪ቱ ወሮቻቸውና ጳጉሜ፡ እያንዳንዳቸው የሚጠሩበት ስም፡ ከእግዚአብሔር ከተሰጣቸው፡ የተፈጥሮ ጸጋቸው ጋር የተያያዘው ገጽታቸውን የሚያሳይ ትርጉም ያለው ሲኾን፡ በኢትዮጵያውያን የወራት አመዳደብ መሠረት፡ ከSeptember (ሴፕቴምበር) መስከረም እስከAugust (ኦገሥት) ነሐሴ ድረስ ያሉት፡ የምዕራባውያኑ ወሮቻቸው ግን፡ እንደሳምንቱ ቀኖቻቸው ኹሉ፡ የተሠየሙት፡ በጣዖቶቻቸውና እንደአማልክት ይሰግዱላቸው በነበሩት ገዢዎቻቸው ስም ኾኖ ይገኛል፡፡

ይኸውም፡ መስከረምን ከኢትዮጵያውያን፡ August'ን (ኦገሥትን)፡ ነሐሴን ደግሞ፡ ከምዕራባውያን፡ ለምሳሌ ያህል ወስደን ብንመለከታቸው፡ "መስከረም"፡ በኢትዮጵያኛ፡ "ከረመ" ወይም፡ "ክረምትን አሳለፈ" ከሚለው ግሥ ወጥቶ፡ "ክረምቱ የሚያበቃበት፡ ማለትም፡ የዝናሙ ጠል አብቅቶ፡ የፀሓይ ብርሃን የሚፈነጥቅበት፡ የዓባይና የሌሎቹ ወንዞች ሙላት መጉደል የሚጀምርበትና ፍጥረቱ ኹሉ፡ ከተሸሸገበት በዓቱ እየወጣ፡ እርስ በርሱ የሚገናኝበት፡ አዲሱ ዓመት፡ የሚገባበት ማለት ነው፡፡ "መስከረም ጠባ!" የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ በምዕራባውያን ዘንድ ግን፡ August (ኦገሥት)፡ ስለወሩ ኹኔታ፡ ምንም ትርጉም የሌለው ኾኖ፡ እንደጣዖት ይመለክ ለነበረው፡ ለአረማዊው ርእሰ ነገሥት (Emperor)፡ ለአውግሥጦስ ቄሣር፡ በመታሰቢያነት የተሰጠ ወር መኾኑን ብቻ ያስረዳል፡፡

የኢትዮጵያውያን ዓመት የሚጀምረው፡ በ"መስከረም"፡ የሚያበቃውም፡ በ"ጳጉሜ" ሲኾን፡ የምዕራባውያኑ ግን፡ በእነርሱ January (ጃንዋሪ)፡ ማለትም፡ በ"ጥር" ይጀምርና፡ በDecember (ዲሴምበር)፡ ማለትም፡ በ"ታኅሣሥ" ይጨርሳል፡፡ ስሙን በመታሰቢያነት፡ January (ጃንዋሪ) ብለው፡ ለዓመቱ የመጀመሪያ ወር የሰጡለት፡ Janus (ጃኑስ)፡ ለሮማውያን፡ ታላቁ ጣዖታቸው እንደነበረ፡ ቀደም ብሎ ተመልክቷል፡፡

በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ፬ ዓመታት፡ ፩ ዐውደ ዘመን ይኾናሉ፡፡ ይህም፡ እያንዳንዱ ዓመት፡ ፫፻፷፭ ከሩብ ዕለታት፡ ወይም ከ፮ ሰዓታት፡ ወይም ከ፲፭ ኬክሮስ ያለው ኾኖ፡ "ዘመነ ማቴዎስ"፥ "ዘመነ ማርቆስ"፥ "ዘመነ ሉቃስ" እና "ዘመነ ዮሐንስ" ተብሎ ተሠይሟል፤ እነዚህ፡ የ፬ቱ ዓመታት ጳጉሜዎች ሰዓታት ሲደመሩ፡ ፩ ዕለት ይሞሉና፡ በ፬ኛው ዓመት፡ በዘመነ ዮሐንስ መግቢያ፡ ፮ ዕለታት በመኾን፡ የባሕረ ሓሳቡ ቅመራ ይከተታል፤[፲፰፯]

የዘመን አቆጣጠሩም ዐውድ፡ እንዲህ፡ በየአራት ዓመታቱ ይዘጋል፡፡

ስለዚህ፡ "የግሬጎሪ" ወይም "ግሬጎሪያን" ተብሎ የሚጠራው፡ የምዕራባውያን፡ የጊዜ አቆጣጠር ባህል፡ እንዲህ፡ ምስቅልቅሉ የወጣ በመኾኑ፡ በእርሱ ሰበብና ጠንቅ፡ ጽኑ የኾነው፡ ሃይማኖታዊና ተፈጥሮአዊ መሠረት ያለው፡ የኢትዮጵያ የዘመን አቈጣጠር ሥርዓት፡ ሊቃወስ ቀርቶ፡ ሊነካ እንኳ፡ ከቶ አይገባም፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

**የጌታን፡ የልደቱን ቀን ማናጋት፡ ያስከተለው ብርቱ ጠንቅ፡፡**

*ጥያቄ፡- የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ ቀን፡ ከእውነተኛው ዕለት፡ ከመስከረም ፩ ቀን፡ ወደ ታኅሣሥ ፳፰÷ ወይም፡ ፳፱ ቀን በመዛወሩ፡ እስካኹን ከገለጽህልን በቀር፡ ሌላ፡ ምን የባሰ ጠንቅን ያስከተለ ችግርን፡ በሃይማኖታችንና በምግባራችን፥ በአምልኮታችንና በሥርዓታችን ላይ አምጥቷል? ወይም፡ "ሊያመጣ ይችላል!" ብለህ ታስባለህ? ከሌለ፡ እስካኹን የሰማነው ስለሚበቃን፡ መልካም ይኾንልናል፣ ካለ ግን፡ ማወቁ፡ እንደሌላው ኹሉ፡ ይጠቅመናልና፡ ብትገልጽልን፡፡ ሳትገልጽልን ያለፍኸው አንዳች ነገር እንዳይኖር ብለን ነው፡ አኹን፡ ይህን ጥያቄ፡ መልሰን ያቀረብንልህ!*

መልስ፡- ይህን ጥያቄ በማቅረባችሁ፡ በውስጤ፡ ምን ያህል የእፎይታ ስሜት እንዳሰጠመኝ፡ አሟልቼ ልነግራችሁ ያዳግተኛል፤ ምክንያቱም፡ እጅግ ያሳዝነኝ፡ ያሳስበኝና ያስጨንቀኝ የነበረውን፥ ልገልጸውም ይገባኝ የነበረውን፡ ምናልባትም፡ ሳልገልጸው አልፌ ብኾን ኖሮ፡ የዘለዓለም ጸጸት ይኾንብኝ የነበረውን ከባድ ጉዳይ ስላስታወሳችሁኝ ነው፡፡

እዚህ ላይ፡ ጥያቄውን ራሳችሁ ካነሣችሁት ዘንድ፡ በኃለ መንፈሳዊ ቅንዓት ተነሣሥታችሁ ልታጤኑትና ለመልካም ፍሬ ልታበቁት የሚገባችሁ፡ አንድ፡ የተለየ፡ ታላቅ ቁም ነገር መኖሩን ልጠቁማችሁ እፈልጋለሁ፤ ይኸውም፡ እግዚአብሔር፡ በድንግል ማርያም የአምላክ እናትነትና በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ አርነት አውጥቶ፡ የቅዱስ ኪዳኑ አገር÷ ሕዝብና መንግሥት የመኾንን የክብር አክሊል፡ መልሶ ያቀዳጃቸውን፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ ዲያብሎስ፡ እንደገና ነጥቆ፡ የራሱ ተገዢዎች ለማድረግ፡ በዚኹ፡ የሥጋዌ ምሥጢረ መለኮት በተፈጸመባት ልዩ በዓል አማካይነት፡ ከፍተኛ የአጥቂነት በደሉን፡ እንዴት ባለ ረቂቅ ስልትና ዘዴ ፈጽሞ፡ ድልን እንደተቀዳጀ፡ በገሃድ የሚያሳየውን እውነታ፡ በግልጽ ማቅረብ ነው፡፡

እንግዴህ፡ በዚኹ ዕለት፡ ዲያብሎስ የተቀዳጃቸውን ኹለት ድሎች፡ በማስተዋል ተመልከቷቸው፡-

አንደኛ፡- እውነተኛዋ፡ የኢየሱስ ክርስቶስና የእናቱ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የልደት ቀን በመኾኗ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ለሃይማኖታቸውና ለምግባራቸው÷ ለአምልኳቸውና ለሥርዓታቸው፡ አንዷ፡ ዋና መሠረታቸው ያደረጓትን÷ ደግሞም፡ "ርእሰ ዐውደ ዓመታችን ናት!" ብለው፡ በመጀመሪያ፡ በቤተ ክርስቲያን፡ ቅዱስ ቍርባንን በመቀበል፡ በፍጹም መንፈሳዊ ሐሤት÷ ቀጥለው፡ በየቤታቸው፡ የመልከ ጼዴቅን በረከት በመሳተፍ፡ በታላቅ በዓላዊ ድምቀት ሊያከብሩዋት የሚገባቸውን፡ መስከረም ፩ ቀንን፡ ዲያብሎስ፡ ጊዜዋን፡ እርሱ ወደሚመለክበት፡ ወደ ታኅሣሥ ፳፰-፳፱ ቀን እንዲያዛውሩ ማድረጉ ነው፤

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል::

## የጌታን: የልደቱን ቀን ማናጋት: ያስከተለው ብርቱ ጠንቅ::

---

ኹለተኛ:- ዲያብሎስ: ያችኑ: ባዶ ኾና ያገኛትን: የተቀደሰችውን: መስከረም ፩ ቀንን: "ዓመቱን ሙሉ: ለእኔ ያላችሁን: በደም የታተመ: የአምልኮ ታማኝነታችሁን የምታረጋግጡባት: በነጻ ያገኘኋት: የእኔ ዕለት ስለኾነች: ከየቤታችሁ ሳትወጡ: ቀይ፡ ነጭ፥ ጥቍር ዶሮ፥ በግ፥ ፍሪዳ እያረዳችሁ: ደም አፍስሱልኝ! ጭዳ፡ ጨሌ፡ ቦረንትቻ፥ ቂጣ፥ ቆሎ፥ ርሚጦ እያላችሁ: መባ አቅርቡልኝ! በስሜ ተሰብስባችሁ፡ ቡና አፍልታችሁና ሣር ጐዝጕዛችሁ: ዕጣን ዐጢሳችሁና ቅቤ ተቀብታችሁ: እየበላችሁና እየጠጣችሁ: አወድሱኝ!" ብሎ: ኢትዮጵያውያን: በክርስቶስ ደም በከበረችው: የኢትዮጵያ ምድራቸው ላይ: አምልኮ ባዕድን እንዲፈጽሙ ማድረጉ ነው:: ለዚህ ባዕድ አምልኮ የሚታረዱትን: የእንስሳቱን የቀለም ዓይነት: "ቀይ፡ ነጭ፡ ጥቁር" ማለቱ: በክርስትና ጥምቀት ጊዜ: በሚጠመቀው ምእመን አንገት ላይ ሊታሠር የሚገባውን: የኢትዮጵያውያንን የሰንደቅ ዓላማ ቀለማት ማተብ: በግብፃውያን ሰንደቅ ዓላማ እንዲለወጥ የማከናወኑን ረቂቅ ዘዴ ፊ ስተውሉትና ይህን የማተብ ቀለማት ነገር በሚመለከት: ቀደም ብለን ከ ገያየንበት ሐተታ ጋር ልታስተያዩት ይገባል::

"ዐውደ ዓመት"፡ "ዕንቍጣጣሽ"፥ "የዘመን መለወጫ"፥ "ቅዱስ ዮሐንስ" እየተባለ: በግልና በአገር ዐቀፍ ደረጃ: ታላቅ በዓል ኾኖ በሚከበረው መስከረም ፩ ቀን: እየራሳችሁ: በቤተ ክርስቲያን ተገኝታችሁ: ለበዓሉ: ከተለመደውና ከሚጠበቀው መጠን ውስጥ: ከካህኑም፡ ከምእመኑም: ከወንዱም: ከሴቱም: ምን ያህሉ እንደመጣ፥ በየቤቱም: ስለበዓሉ: በባዕድ አምልኮ መልክ የሚካኼደውንና የሚፈጸመውን ድርጊት: ምን ዓይነት እንደኾነ: በቅርብ በማየትና በመከታተል: የዚህን እውነታ እርግጠኛነት: በቀላሉ ልትገነዘቡት ትችላላችሁ::

### ስለገና ዛፍ::

*ጥያቄ:- እዚህ ላይ: ተያይዞ ሊብራራ የሚገባ: ሌላ ዋና ነገር ስላለ: እንድናቀርበው ፍቀድልን! ይህም: የገና ዛፍን የሚመለከት ነው:: የክርስትናን እምነት የተቀበሉት አረማውያን: እውነተኛውን: የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ቀን: የጣዖትና የባዕድ አምልኮ ልማዳቸውን ወደሚፈጽሙበት ዕለት አዛውረው: በዚያን ዕለት እንዲከበር መወሰናቸውና ይህንኑ ውሳኔያቸውን በተግባር ማዋላቸው: እንኳንስ: የግብፃውያን የሃይማኖት መሰሎቻችንና የእኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ጭምር: የግብረ አበርነት መተባበር ታክሎበት ይቅርና: በራሳቸው: በአረማውያኑ ዘንድ ብቻም ቢኾን: ያለው አስፈላጊነትና ተገቢነት: በቀላሉ ሊገባን ይችል ይኾናል:: ለእኛ: በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር፥ አምልኮና ሥርዓት ለኖርነው: ኢትዮጵያውያን ግን: ይህን: ግብፃውያንን የሚጨምረውን: የአሕዛብን ውሳኔ ለመቀበል: በእርግጥ ይከብደናል::*

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
### "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*"ታዲያ፡ በዚያ፡ በጣያትና በባዕድ አምልኮ ኖረው፡ ወደክርስትና ሕይወት የገቡት ወገኖች፡ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የልደት በዓሉ ቀን ይኹን!" ብለው፡ በራሳቸው አቈጣጠር፡ በDecember 25 (ዲሴምበር ፳፭)፡ በየቦታው፡ የገና ዛፍ ብለው፡ ሸልመው በሚያከብሩበት ጊዜ፡ ስለዚሁ ሥርዓታቸው፡ ለራሳቸውና ለልጆቻቸው፥ ለሌላውም ለማስረዳት፡ ለእነርሱ፡ በቂ ምክንያት ይኖራቸው ይኾናል።*

*ለእኛ፡ ለኢትዮጵያውያኑ ግን፡ እንዲህ ብሎ ለማስረዳት፡ እጅግ ያስቸግራል፡ የእኹኑ የኢትዮጵያውያን የገና በዓል፡ የባዕዳኑን አቆጣጠር ተከትሎ፡ በታኅሣሥ ፳፰፡ ወይም፡ ፳፱ ቀን እንዲከበር ተደርጎም እንኳ፡ ከእነርሱ በዓል ጋር በአንድ ቀን፡ አብሮ ሊውል አለመቻሉ፡ ይኸው ይታያል፡ ስለዚህ፡ የበዓሉ ቀን፡ አኹን ባለው እየቀጠለም ቢኾን፡ ወደፊት፡ በአገር ደረጃ፡ ወደጥንታዊው ትክክለኛ ቀመሩ፡ ወደመስከረም ፩ ቀን እስከሚመለስበት ጊዜ ድረስ፡ ኢትዮጵያውያን፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችን ምክንያት፡ አውቀንም ኾነ፡ ሳናውቅ፡ ይህን ስሕተት፡ ከመፈጸም እንድንታቀብ በማሳሰብ፡ ስለገና ዛፍ ታሪክና ስለአምልኮ ጠንቁ የምትነግረን፥ እንደተለመደው፡ ቍም ነገር የተመላበት ማሳሰቢያ ምክርህ አይኖርምወይ? ካለ፡ ለመስማት፡ በጉጉት እንጠብቃለን።*

**መልስ፦** ባኹኑ ጊዜ፡ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን፥ ካለማወቅ የተነሣ ይመስላል፡ ኢትዮጵያዊዉን የልደት በዓል፡ በየቤታቸው፥ ሕዝባውያን በኾኑ ቦታዎች ሳይቀር፡ በምዕራባውያን ልማድ፡ በጥድ ዛፍ ሲያከብሩት ይታያል። ዳሩ ግን፡ ይህ ድርጊት፡ የሃይማኖት አምልኳችንን የሚነካ በመኾኑ፡ እንኳንስ ሊደረግ፡ ሊታሰብም የሚገባ አይደለም። እንዲህ እንዳይኾንም፡ ከአኹኑ፡ በብርቱ ሊነቃበት ያስፈልጋል። እናንተም፡ ይኸው፡ የእኔን የመሰለ ሥጋት ስላደረባችሁ፡ ነገሩን ልታነሡብኝ ችላችኋል።

በተለይ፡ ኢትዮጵያውያን ልጆች፡ ስለዛፉ በሚጠይቁበት ጊዜ፡ ጕዳዩ፡ ሃይማኖታችንንና አምልኳችንን የሚመለከት በመኾኑ፡ ስለሚሰጠው ምላሽ፡ ወላጆችም ኾኑ መምህራን፥ አረጋውያን ወንዶችም ኾኑ ሴቶች፡ በብርቱ ሊዘጋጁበት ያሻል። ኢትዮጵያውያን ልጆች፡ በቤታቸው፥ ወይም፡ በሕዝብ ቦታዎች ተሰናድቶ ስለሚያዩት፡ ስለገናው ዛፍ፡ ጥያቄያቸውን ሲያቀርቡ፡ ኢትዮጵያውያኑ፡ የሚሰጧቸው መልስ፡ ምን ሊኾን ነው? ምዕራባውያኑ፡ ለልጆቻቸው፡ "የክርስትናን ሃይማኖት ከመቀበላችን በፊት፡ በዛፍ እናመልክ ስለነበር ነው!" ብለው የሚሰጧቸውን መልስ የመሰለ ሊኾን ነው? ወይስ፡ ሌላ ምን ዓይነት ምክንያት ልናቀርብላቸው ነው? ከማፈር በስተቀር፡ ምንም የሚነገር ነገር ከቶ አይኖርም። ደፍሮ፡ ታሪኩን፡ ቀደም ብዬ በዘረዘርሁት መልክ የሚያብራራላቸው ቢኖር እንኳ፡ መቼም፡ የዘመኑ ልጆች፡ ንቁ ጠያቂዎች ናቸውና፡ "ታዲያ! እኛ፡ ለምንድር ነው፡ እንደፈረንጆቹ፡ በዚህ በዛፉ የምናከብረው?" ብለው፡ መልሰው ቢጠይቁን፡ የምንሰጣቸው፡ ምን መልስ ይኖረን ይኾን? ምንም አይኖረንም።

# ምዕራፍ ፲፮፤ በዓል::
## ስለገና ዛፍ::

እንግዲህ፡ ምዕራባውያን፡ የገና በዓላቸውን፡ በተጌጠ የጥድ ዛፍ የሚያከብሩት በምን ምክንያት መኾኑን፡ ኢትዮጵያውያን ልጆቻችን፡ በትክክል እንዲያውቁት ከማድረግ በቀር፡ ነገሩን እንደቀላልና እንደዋዛ በማየት፡ ወይም፡ "ልጆችን ያስደስታል!"፥ ወይም፡ "ከማን አንሼ!" በማለት፡ ደንን የሚያራቁት ይህን የመሰለውን ድርጊት መፈጸሙ፡ በሥጋም፡ በነፍስም፡ ከባድ ችግር ውስጥ መግባት መኾኑን አውቀን፡ በእኛ በኩል፡ በጊዜው፡ ተገቢውን ጥንቃቄ ልናደርግ ግድ ይኾንብናል::

ስለዚህ፡ ይህ ጉዳይ፡ ሃይማኖትንና አምልኮን የሚመለከት በመኾኑ፡ ወላጆችም፡ መምህራንም፡ ከዚያም በላይ፡ ማናቸውም ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት፡ ኹላችንም፡ እናንተና እኔ ጭምር፡ ለልጆቻችን፡ ልናሳውቃቸውና ልናስተምራቸው የሚገባን፡ እኛ፡ ኢትዮጵያውያን፡-

አንደኛ፡ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል የምናከብረው፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓት እንጂ፡ እንደባዕዳኑ፡ በጥድ ዛፍ አለመኾኑን በማብራራት፡ ይህን የመሰለው አጉል ባህል እንዳይለመድ፡ ለተተኪውም ትውልድ እንዳይተላለፍ መታገሉ፡ የእነርሱም ግዳጅ መኾኑን፡

ኹለተኛ፡ ጥንት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በኪዳን ልቦና፡ በመካከሉ፡ በኪዳን ኦሪት፡ በመጨረሻም፡ በኪዳን መንፈስ ቅዱስ፡ እስከዛሬ የኖርነው፡ ዛሬም እየኖርን ያለነው፡ ወደፊትም የምንኖረው፡ በዚህ ውድይታችን ላይ፡ ስለጽላትና ስለታቦት፡ የተሰጣችሁ ሓተታ እንደተጠበቀ ኾኖ፡ ያው፡ በእውነትና በመንፈስ፡ በምንፈጽመው፡ በአምልኮተ እግዚአብሔር ሥርዓታችንና ባህላችን ብቻ መኾኑን ነው::

## ስለሺሁ ዓመት::

*ጥያቄ፡-　　የኢትዮጵያውያንን የዘመን አቈጣጠር ሥርዓት በሚመለከት፡ የጀመርነውን ውይይት ከማብቃታችን በፊት፡ ይኸው፡ የእኛ የኾነው ሥርዓት፡ በራእየ ዮሓንስ ውስጥ፡ ስለተጠቀሰው፡ የ"ሺሁ ዓመት" ምሥጢርና ፍጻሜው፡ ምን ትርጓሜ እንዳለው፡ ከተነሣንበት ርእሰ ነገር ጋር አያይዘህ ብታስረዳን!?*

መልስ፡-　　የኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት፡ ትክክልና እውነተኛው መኾኑን ለመጨረሻ ጊዜ ለማረጋገጥ የሚያበቃው ከፍተኛ ነጥብ የሚገኘው፡ ስለዚሁ፡ የ"ሺሁ ዓመት" ምሥጢርና ፍጻሜው፡ የእኛው ሥርዓት ከሚሰጠው የትርጓሜ ሓተታ በመኾኑ፡ እዚህ ላይ፡ ይህን ጥያቄ በማንሣታችሁ፡ በነበረው ደስታዬ ላይ፡ ደስታን ጨምራችሁልኛል::
ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሓንስ፡ ስለዚሁ፡ የሺ ዓመቱ ምሥጢር፡ በራእይ አይቶ የጻፈውን ትንቢታዊ ቃል፡ ቀደም ብለን ሰምተነዋል::[፻፷፰]

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ኢትዮጵያውያን፡ እንዲህ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት የተረጋገጠውን፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት በመከተል፡ እስከዛሬ ጠብቀውት የኖሩትን፡ መሠረታዊዉን የጊዜ አቆጣጠር ስልት፡ ምዕራባውያን፡ ኦርቶዶክሳውያን የተባሉትን አብያተ ክርስቲያናት ጨምሮ፡ በአረማዊው፡ ዩልየስ ቄሣርና ግሬጎሪ ፲፫ኛ በተባለው፡ በካቶሊካዊው ጳጳስ ስሞች እየሠየሙ፡ በየጊዜው እየለዋወጡና በመጨረሻ፡ ፯ ዓመታት ከ፰ ቀናት ያህል አክለውበት መቆየታቸው፡ ቀደም ብሎ ተገልጿል፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው፡ በራእየ ዮሐንስ የተነገረው፡ የሺህ ዓመት ምሥጢር፡ እንደእነርሱ አቈጣጠር፡ "፩ ሺህኛው ዓመት ተፈጽሞ፡ ፪ ሺህኛው ዘመን በጀመረባት የጥር ወራቸው መግቢያ እኩለ ሌሊት ላይ በነበረችው፡ በዚያች፡ የመጀመሪያ ሰዓት ይከሠታል!" ብለው፡ በታላቅ ሥጋትና ፍርሃት፡ የመንፈስ ንቃትም፡ የጠበቁት፡ "የዓለሙ ፍጻሜ" ሳይደርስ አልፏል! ታዲያ! የዚህ ምክንያት፡ ምን ይኾን? እንደ፡ በሰውኛ ፍልስፍና ታስበውና ተቀምረው የታከሉት፡ ፯ ዓመታት ከ፰ ቀናት፡ በኢትዮጵያኑ አቈጣጠር ላይ መጨመራቸው፡ ስሕተት መኾኑን ለማጋለጥ ይኾን?

እንግዲህ፡ በዚህ ረገድ የሚጠበቀው፡ በእውነተኛዋ ሃይማኖት ላይ የጸናው፡ ዛሬ የሚሠራበትና ለሺሁ ዓመት ማብቂያ፡ ኹለት ዓመታት የቀረው፡ ይህ የኢትዮጵያውያን የጊዜ አቈጣጠር ሥርዓት ነው፡፡ ይኸው፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓት፡ የተመሠረተው፡ የቆመውና የተደመደመው፡ በእግዚአብሔር ቃልና አምልኮት ላይ ስለኾነ፡ ዕድሜውን ያገኘ ሰው፡ ይህ መለኮታዊ ምሥጢር ተገልጾ የተነገረበት፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" የሚለው መጽሐፍ ታትሞ ከወጣበት፡ ከ፩ሺ፱፻፺፫ ዓ. ም. በኋላ፡ ለ፯ ዓመታት ቆይቶ፡ በገባችው፡ በዚያች በ"ሺዋ ዓመት" ፍጻሜ የሚደርሰውን፡ የራእየ ዮሐንስን የምሥጢር ክሥተት፡ ሊያይ ይበቃል፡፡

### የጌታ የልደቱ ቀን፡ ወደተገቢ ቦታው ስለሚመለስበት መንገድ፡፡

*ጥያቄ፡- የኢትዮጵያውያንን የዘመን አቈጣጠር ሥርዓት በመከተል፡ ወደየነበሩበት የጥንት መደበኛ ቀኖቻቸው ሊመለሱ የሚገባቸውን በዓሎቻችንንና ጾሞቻችንን በሚመለከት፡ የመጨረሻ ማጠቃለያ የኾነ፡ አንድ ጥያቄን ለማቅረብ ፍቀድልን! ይኸውም፡ "በግብፃውያን ሃይማኖታዊ ተፅዕኖ ምክንያት፡ ለ፩ሺ፮፻ (አንድ ሺህ ስድስት መቶ) ዓመታት ያህል፡ እንዲህ ሥር ሰድዶ፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ዘንድ የኖረው፡ በተለይ፡ ይህ የተሳሳተ የልደት በዓል አከባበር፡ ወደነበረበት ጥንታዊና ኢትዮጵያዊ ሥርዓቱ እንዲመለስ ለማድረግ፡ የሚቻለው እንዴት ነው?" የሚለው ነው፡፡*

**መልስ፡-** መቼም፡ እንደምታውቁት፡ "ሃይማኖት"፡ ቀላል ነገር አይደለም፤ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ "ሃይማኖት ነው!" ብለን የያዝነው የህልውና አቋማችን፡ ከፈጣሪያችንና አምላካችን እግዚአብሔር ጋር፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ የሚያገናኘንና አንድ የሚያደርገን ኃይል ነው፡፡

## ምዕራፍ ፮፤ በዓል::
## የጌታ የልደቱ ቀን: ወደተገቢ ቦታው ስለሚመለስበት መንገድ::

የምናምነውና የምናመልከው እግዚአብሔር ደግሞ: እውነት እንጂ: ሓሰት ስለማይስማማው: ይህንኑ ሃይማኖታችንን: በሓሰት ሳይኾን: በእውነት፣ በተራ ግዴለሽነትና በቀላል ወላዋይነት ሳይኾን: በከፍተኛ ጥንቃቄና በፍጹም ታማኝነት ልንጠብቀው የሚገባን ታላቅ ጉዳይ ነው:: ይህ አባባሌ: እሙን ስለመኾኑ: በማናቸውም ሰብአዊ ፍጡር ዘንድ የታወቀ ነውና: በምንም አያከራክርም::

እንዲህ ከኾነ: አምላክ ሰው በኾነበት: በዚህ: በታላቁ የልደት ቀን ላይ የሚኖረን ሃይማኖታዊ አቋም: እግዚአብሔር በሚወድደውና በሚቀበለው እውነት ላይ የተመሠረተ ሊኾን ይገባል ማለት ነው፡ ከዚህ በቀር: በሌላው በሓሰቱ መንገድ: "ይቀጥል!" የሚል: እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ብዬ አልገምትም:: ባለማወቅ ሲሠራበት ለቆየው ስሕተት: ተጠያቂነቱ: በቀጥታ: አውቀው ያጠፉትን የሚመለከት ሲኾን: ይኹን እንጂ: ባላወቁት ዘንድ: በሕሊናም: በእግዚአብሔርና በሰውም በኩል: ከተጠያቂነቱ ነጻ እንደሚኾኑ: እውነቱን ካወቁት በኋላ ግን: ለማንም: ምንም ዓይነት ምክንያት በማቅረብ: ከተጠያቂነቱ ለማምለጥ: ከቶ እንደማይቻል: ማረጋገጡ አያዳግትም::

አኹን: ይኸው ጉዳይ: ሃይማኖትንና አምልኮን የሚነካ: እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷን ኢትዮጵያዊት: በኃላፊነት የሚያስጠይቅ ከመኾኑ የተነሣ: በግለሰብ ደረጃ እየተፈጸመ የሚቀይ እንጂ: በአኹኑ ጊዜ: በአገር ደረጃ: በሥራ ላይ ሊውል ይቻላል ብሎ ለማሰብ ያዳግታል:: በሥራ ላይ ሊውል የሚችለው: በኢትዮጵያ: ጸንቶ የኖረው: የእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት: በቅድሚያ: በምድራቱና በሕዝቡ መካከል: በይፋ መስፈን ሲጀምር ብቻ ይኾናል:: በዚያን ጊዜ: ይህም ኾነ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ: ያለማቋረጥ እየወረደ ላለው መከራ: ጠንቀኛ ምክንያት የኾኑት: ሌሎቹ ተመሳሳይ ጉዳዮች: ቤተ ክህነቱንና ቤተ ምልክናውን አጠቃልሎ በያዘው: በቤተ ሕዝቡ ታይተውና ተመክሮባቸው የሚወሰኑ ይኾናሉ::

*ጥያቄ:- ታዲያ: እስከዚያው: በተለይ: ስለጌታ የልደት ቀን: የኢትዮጵያውያን ውሳኔ: ምን ሊኾን ይገባል? በአሁኑ ዘመን ለምንገኝ ኢትዮጵያውያን: ያለን ምርጫ: የትኛው ነው? የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ ቀን: ለእኛም በዓላችን ኾና ልናከብራት የሚገባን ዕለት: ከኹለቱ ዕለታት: ማለትም: ከታኅሣሥ ፳፱ እና ከመስከረም ፩ዱ ቀን: የትኛዋ ናት?*

መልስ:- ቀደም ብዬ እንዳመለከትኋችሁ: ነገሩ: የቃል ኪዳን ሃይማኖትን የሚነካ ስለኾነ፣ በዚሁ ሃይማኖታችን አማካይነት አውቀነውና ተቀብለነው ባጸናነው: የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣናችን ተጠቅመን: እውነተኛዪቱና ትክክለኛዪቱ ዕለት የትኛዋ እንደኾነች: በእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ: መርጠንና ወስነን: እንደኛዪቱን መያዝ አለብን::

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ይህን ምርጫና ውሳኔ፡ በየግላችን እናደርግ ዘንድ፡ ከየፊታችን የሚቀርቡት እውነታዎች፡ ኹለት ናቸው:: ከእነዚህ እውነታዎች መካከል:

የመጀመሪያው:- "እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "በጽኑ ቀጠሮው፡ አንዲት ሰዓት እንኳ ሳያሳልፍ" ተወለደባት ወዳሰኘነውና "ዓመተ ምሕረት" ብለን ዓመቱን ወደምንጀምርበት፡ ወደቀንታዊው የዘመን አቆጣጠራችን፡ ተመልሰን፡ በእግዚአብሔር አምልኮ፥ ቃልና መንፈስ ተመሥርታ፤ ጸንታና ሕያው ኾና የኖረችው፡ ያቺ፡ የልደቱ ዕለት፡ "መስከረም ፩ ቀን" ናትና፡ አጽንተን፡ ልናከብር የሚገባን፡ እርሷን ነው!" የሚል ሲኾን:

ኹለተኛው ደግሞ:- "ይኼ፡ ከእግዚአብሔር ያገኘነው፡ ጥንታዊዉና መልካሙ ሥርዓታችን ተሠርዞ፡ በጣዖት አምልኮና በአረማውያን ባህል ላይ በተመሠረተው፡ በባዕዳኑ ሰብአዊ ዘዴ የተተካውን አሠራር ተቀብለን፡ ከወገኖቻችን መካከል፡ ብዙዎች እንዳደረጉት፡ እኛም፡ የቀረነው፡ ኢትዮጵያዊነታችንን ክደንና የቀን አቆጣጠራችንን ዘይቤ ለውጠን፥ በባዕድ አምልኮውም ተዘፍቀን፡ ወደዲያብሎስ ግዛትና ወደአሕዛቡ ሥርዓት፡ ጠቅለለን እንግባወይ?" የሚል ነው::

እንግዲህ፡ በውይይታችን ላይ፡ መላልሼ እንዳወሳሁት፡ ይህ ጉዳይ፡ ሃይማኖትንና አምልኮን የሚመለከት ስለኾነ፡ በተለይ፡ በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እንደማናቸውም ተራ ነገር፡ እንዲያው፡ በዝምታ፥ ወይም፡ በቸልታ፥ ወይም፡ በቆይታ፤ ወይም፡ በእይታ፡ ሊታለፍ የሚገባው አይደለምና፡ አኹን ለጊዜው፡ በየግላችሁ፡ ወደፊትም፡ በጊዜው፡ በቤተ ሕዝብ፥ በቤተ ክህነትና በቤተ ምልክናው አባልነታችሁ፡ የሚገባችሁን የመምረጥና የመወሰን ግዳጃችሁን እንድትፈጽሙ፡ ኃላፊነቱን፡ ከጽኑ [፻፷፱] አደራ ጋር፡ ለየራሳችሁ በመተው፡ የመልስ ቃሌን፡ በዚሁ እገታለሁ::

## ስለቅድስት ድንግል ማርያም የልደት ቀን::

*ጥያቄ:- የድንግል ማርያም፡ የልደቷ በዓል የሚውለው፡ "በግንቦት ፩ ቀን ነው!" ተብሎ፡ እስከዛሬ፡ በዚህ ቀን ሲከበር የቆየውን፡ አኹን፡ "የለም! ይህ ትክክል አይደለም፡ የእርሷም የልደት ቀን የሚውለው፡ 'መስከረም ፩ ቀን ነው!'" ከተባለ፡ እንዲህ ሊኾን የቻለበትን ምክንያት፡ ከዚህ ጋር አያይዘህ ብትገልጽልን?*

መልስ:- በማስተዋል እንድትመለከቷቸው፡ ምክንያቶቹን ባጭር አጠቃልዬ ላቅርብላችሁ:-

# ምዕራፍ ፳፥ በዓል።
## ስለቅድስት ድንግል ማርያም የልደት ቀን።

አንደኛ፡- በግብፃውያን ጳጳሳት፡ የውግዘት ቃል፡ በኢትዮጵያውያን ላይ፡ ጸንቶ እየሠራ ያለው የተአምረ ማርያም መጽሐፍ፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የልደት በዓል፡ "ግንቦት ፩ ቀን ይውላል" ብሎ፡ በዚሁ ወርና ቀን እንዲከበር አድርጓል። በዚሁም መጽሐፍ ውስጥ፡ "ቦ፡ እለ ይቤሉ፡ 'አመ ፀሡሩ ለመስከረም ልደታ'፡ ማለትም፡ "የእመቤታችን የልደቷን ቀን 'በመስከረም ዐሥር ነው!' የሚሉም አሉ፡" ተብሎ፡ ተጽፎ ዘወትር ሲነበብ ይሰማል። ከዚህም ጋር፡ ከእነርሱው፡ ከግብፃውያኑ ባገኘነው፡ "ስንክሳር" በተባለው መጽሐፍ፡ በመስከረም ፲ ቀን ምንባብ ውስጥ፡ "ወበዛቲ ዕለት፡ ቦ፡ እለ ይብሉ፡ ኮነ ልደታ፡ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ወላዲተ አምላክ፡ ወዝንቱ ጽሑፍ፡ ውስተ መጽሐፈ ግጻዌ፡ ዘቅዱስ አባ መቃርስ፡ ዘገዳመ አስቄጥስ፡ ወከማሁ፡ ካዕበ ጽሑፍ፡ ውስተ መጽሐፈ ግጻዌ፡ ዘላዕላይ ግብፅ፡ ከመ አመ ፲ወ፯ ለወርኀ ታኅሣሥ፡ ፀንሰታ፡ ለእግዝእትነ፡ ቅድስት ድንግል፡ ብዕሲት ሐና፡ ወወለደታ፡ አመ ፲ ለመስከረም፡" ማለትም፡ "በዚችም፡ በመስከረም ፲ ቀን፡ 'አምላክን የወለደች፡ እመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የተወለደችበት ነው!' የሚሉ አሉ፡ ይህም፡ የአስቄጥሱ ገዳም፡ ቅዱስ አባ መቃርስ፡ ባዘጋጀው፡ መጽሐፈ ግጻዌ ውስጥ ተመዝግቧል፡ እንዲሁም ደግሞ፡ በላዕላይ ግብፅ በሚገኝ፡ መጽሐፈ ግጻዌ ውስጥ፡ 'ቅድስት ድንግል እመቤታችንን፡ ቅድስት ሐና፡ በታኅሣሥ ወር፡ በ፲፯ኛው ቀን፡ እንደፀነሰቻትና በመስከረም ፲ ቀን እንደወለደቻት የሚያመለክት ቃል አለ፡" ተብሎ፡ ተመዝግቦ ይገኛል።

"ቦ፡ እለ ይቤሉ!" ማለትም፡ እንዲህ፡ "የሚሉ አሉ!" የተባልን፡ እኛው ኢትዮጵያውያኑ ነን፡ ሌላ፡ ማን ሊኾን ይችላል? የኢትዮጵያ አምላክ፡ ይህ እውነታ፡ በዚሁ፡ በእነርሱው የተአምረ ማርያምና የስንክሳር መጻሕፍት ውስጥ፡ በጽሑፍ ሠፍሮ፡ በግድ እንዲነበብ ያደረገው፡ ያለምክንያት አይደለም፡ ከጥንት ጀምሮ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት፡ ብነቢያቱ ያናገራቸው መለኮታውያን ቃላቱ፡ ዓለም በተቀበለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፈው እንዲገኙ እንዳደረገ ኹሉ፡ አኹን ደግሞ፡ በእነዚህ፡ በግብፃውያን መጻሕፍት ውስጥ፡ ይህንኑ ድንቅ ሥራውን መድገሙ መኾኑን አስተውሉት!

ይኸውም፡ ኢትዮጵያውያን፡ "የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የፅንሰቷ ወር፡ 'ታኅሣሥ'፡ የልደቷም፡ 'መስከረም' ነው!" ብለው አምነው፡ ሲያከብሩትና ሲሠሩበት የኖሩት፡ ዛሬም፡ እኛ፡ የቅዱሱ ቃል ኪዳን ልጆቿ ኢትዮጵያውያን፡ እያከበርነውና እየሠራንበት ያለነው፡ ይህ ሥርዓታቸው፡ እውነተኛውና ትክክለኛው፡ የእግዚአብሔሩ መኾኑን፡ በእነርሱው መጽሐፋዊ ማስረጃ ሳይቀር፡ አረጋግጦ በማሳወቅ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ እውነተኛው ሕያው ቅርስ ሳይደመሰስ፡ ደብዛውም ሳይጠፋ፡ እነሆ፡ ለምስክርነት ተርፎ፡ ዛሬ፡ ከእኛም ዘመን እንዲደርስ፡ ይኸው፡ አኹን በእኛ ውይይት እንደሚታየውም፡ እውነታው ተፈጽሞ፡ እንዲታወቅ ኾነ! ለዚህ ድንቅ ሥራው፡ እያቀረብንለት ያለነውን ምስጋና፡ እግዚአብሔር፡ የሚቀበለው ይኹን![፳]